እግዚአብሔር አብን እያመሰገናችሁ በቃልም
ሆነ በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየ
ሱስ ስም አድርጉት ።

### በቤተሰብ ውስጥ የክርስቲያን ግዴታ

18 ሚስቶች ሆይ! የጌታ ኢየሱስ በመሆና
ችሁ መታዘዝ ተገቢ ነገር ስለሆነ ለባሎቻችሁ
ታዘዙ ።
19 ባሎች ሆይ! ሚስቶቻችሁን ውደዱ ፤
ጨካኞችም አትሁኑባቸው ።
20 ልጆች ሆይ! ይህ ጌታን ደስ የሚያሰኝ
ስለሆነ ፥ በሁሉ ነገር ለወላጆቻችሁ ታዘዙ ።
21 ወላጆች ሆይ! ተስፋ እንዳይቈርጡ ልጆ
ቻችሁን በቍጣ አታስመርሩአቸው ።
22 አገልጋዮች ሆይ! ለምድራዊ ጌቶቻችሁ
በሁሉ ነገር ታዘዙ ፤ የምትታዘዙትም ሰውን
ደስ ለማሰኘትና ለታይታ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስን
በመፍራትና በልብ ቅንነት ይሁን ። 23 የምታደ
ርጉትን ሁሉ ለሰው ሳይሆን ለጌታ ኢየሱስ እን
ደምታደርጉት ዐይነት በትጋትና በደስታ አድር
ጉት ። 24 ጌታ ርስትን ዋጋ አድርጎ እንደሚሰጣ
ችሁ ታውቃላችሁ ፤ የምታገለግሉትም ጌታ የሆ
ነውን ክርስቶስን ነው ፤ 25 ክፉ የሚሠራም ስለ
ክፉ ሥራው ቅጣቱን ይቀበላል ፤ ምክንያቱም
በእግዚአብሔር ዘንድ አድልዎ የለም ።

## ምዕራፍ 4

1 ጌቶች ሆይ! እናንተም በሰማይ ጌታ እንዳ
ላችሁ ታውቃላችሁ ፤ ስለዚህ አገልጋዮቻችሁን
በቅንነትና በእኩልነት አስተዳድሩአቸው ።

### ምክር

2 እግዚአብሔርን ተግታችሁ በማመስገን
ባለማቋረጥ ጸልዩ ፤ 3 እግዚአብሔር ለምሥራቹ
ቃል በር እንዲከፍትልንና በእርሱ ምክንያት
እኔ ታስሬ የምገኝበትን የክርስቶስን ምስጢር
ማብሠር እንድችል ለእኛም ጸልዩ ። 4 እኔም
እንደሚገባኝ በግልጥ እንድናገር ጸልዩልኝ ።
5 በማንኛውም አጋጣሚ ጊዜ እየተጠቀማ
ችሁ በማያምኑት ሰዎች ዘንድ በጥበብ ኑሩ ።
6 ለእያንዳንዱ ሰው ተገቢውን መልስ መስጠት
እንድታውቁ ዘወትር ንግግራችሁ ለዛና ጣዕም
ያለው ይሁን ።

### የመጨረሻ ሰላምታ

7 ቲኪቆስ ስለ እኔ ጉዳይ ሁሉንም ነገር ይነ
ግራችኋል ፤ እርሱ ተወዳጅ ወንድም ፥ ታማኝ
አገልጋይና ከእኔም ጋር በጌታ ሥራ ተባባሪ
ነው ። 8 እርሱን ወደ እናንተ የላክሁበት ምክን
ያት ስለ እኛ ሁኔታ እንዲነግራችሁና ልባችሁ
ንም እንዲያጽናና ነው ። 9 ከእርሱም ጋር የእና
ንተ ወገን የሆነው የታመነውና የተወደደው
ወንድም አናሲሞስ ወደ እናንተ ይመጣል ፤ እነ
ርሱ በዚህ ስፍራ ስላለው ነገር ሁሉ ያስታውቁ
አችኋል ።
10 ከእኔ ጋር የታሰረው አርስጥሮኮስም ሰላ
ምታ ያቀርብላችኋል ፤ ወደ እናንተ በሚመጣ
በት ጊዜ እንድትቀበሉት ያሳሰብኋችሁ የበርና
ባስ የአጐቱ ልጅ ማርቆስም ሰላምታ ያቀርብ
ላችኋል ። 11 ኢዮስጦስ የተባለውም እያሱ ሰላ
ምታ ያቀርብላችኋል ። ስለ እግዚአብሔር መን
ግሥት ከእኔ ጋር አብረው ከሚሠሩት ሰዎች
መካከል አይሁዳውያን የሆኑት እነዚህ ብቻ
ናቸው ፤ እኔንም አጽናንተውኛል ።
12 የእናንተ ወገን የሆነው ፥ የኢየሱስ ክርስ
ቶስ አገልጋይ ኤጳፍራም ሰላምታ ያቀርብ
ላችኋል ፤ በመንፈሳዊ ሕይወት በማደግ ጸንታ
ችሁ እንድትቆሙና የእግዚአብሔርንም ሙሉ
ፈቃድ እንድትፈጽሙ እርሱ ሁልጊዜ ስለ እና
ንተ በጸሎቱ ይጋደላል ። 13 ስለ እናንተ ፥ በሎ
ዶቅያና በሂራፖሊስ ከተሞች ስላሉትም ሰዎች
በጣም እንደሚደክም እኔ ራሴ እመሰክርለታ
ለሁ ። 14 የተወደደው ሐኪም ሉቃስና ዴማስም
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።
15 በሎዶቅያ ላሉት ወንድሞች ፥ ለንምፋና
በቤትዋም ላለች[2*] ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅ
ርቡልኝ ። 16 ይህችን መልእክት እናንተ ካነበባ
ችሁ በኋላ በሎዶቅያ ሰዎች ዘንድ ባለችው
ቤተ ክርስቲያን እንድትነበብ አድርጉ ፤ እናን
ተም ከሎዶቅያ የሚላክላችሁን መልእክት አን
ብቡ ። 17 ለአርኪፖስም "በጌታ አገልግሎት
የተሰጠህን ሥራ በጥንቃቄ እንድትፈጽም" ብላ
ችሁ ንገሩልኝ ።
18 ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት እኔ
ጳውሎስ ነኝ ፤ እስራቴን አስታውሱ ።
ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን ።

---

2* 4፥15 ለንምፋና በቤትዋም ላለች ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "ለኒምፋስና በቤቱም ላለች" ይላሉ ።
3፥18 ፦ ኤፌ. 5፥22 ፤ 1ጴጥ. 3፥1 ። 3፥19 ፦ ኤፌ. 5፥25 ፤ 1ጴጥ. 3፥7 ። 3፥20 ፦ ኤፌ. 6፥1 ። 3፥21 ፦ ኤፌ. 6፥4 ።
3፥22-25 ፦ ኤፌ. 6፥5-8 ። 3፥25 ፦ ዘዳ. 10፥17 ፤ ኤፌ. 6፥9 ። 4፥1 ፦ ኤፌ. 6፥9 ። 4፥5 ፦ ኤፌ. 5፥16 ።
4፥7 ፦ ሐ.ሥ. 20፥4 ፤ 2ጢሞ. 4፥12 ። 4፥7-8 ፦ ኤፌ. 6፥21-22 ። 4፥9 ፦ ፊልሞና 10-12 ።
4፥10 ፦ ሐ.ሥ. 19፥29 ፤ 27፥2 ፤ ፊልሞና 24 ፤ ሐ.ሥ. 12፥12 ፥25 ፤ 13፥13 ፤ 15፥37-39 ። 4፥12 ፦ ቆላ. 1፥7 ፤ ፊልሞና 23 ።
4፥14 ፦ 2ጢሞ. 4፥10-11 ፤ ፊልሞና 24 ። 4፥17 ፦ ፊልሞና 2 ።

# የመጀመሪያው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

## መግቢያ

ተሰሎንቄ ፥ መቄዶንያ የተባለው የሮም ግዛት ዋና ከተማ ነበረች ፤ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ያቋቋመው ፊልጵስዩስን ትቶ ከሄደ በኋላ ነው ፤ ይሁን እንጂ የአይሁድን ሃይማኖት ሊቀበሉ ተቃርበው የነበሩት አረማውያን ጳውሎስ በሚያቀርበው የክርስትና መልእክት ተስበው ስለነበር አይሁዳውያን ቀንተው በጳውሎስ ላይ ተቃውሞ አስነሥተው ነበር ፤ ስለዚህም ጳውሎስ ተሰሎንቄን ለቆ ወደ ቤርያ ለመሄድ ተገደደ ፤ ዘግየት ብሎም ወደ ቆሮንቶስ እንደደረሰ የቅርብ ረዳቱ የነበረው ጢሞቴዎስ በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ስላለው ሁኔታ በዝርዝር ጸፈለት ።

ጳውሎስ የመጀመሪያውን መልእክት ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው ክርስቲያኖችን ለማበረታታ ትና ለማጽናናት ነበር ፤ ስለ እምነታቸውና ስለ ፍቅራቸው መልካም ወሬ በመስማቱ ያመሰግና ቸዋል ፤ እርሱ በመካከላቸው በተገኘበት ጊዜ ምን ዐይነት ሕይወት እንደኖረ ያስታውሳቸዋል ፤ ከዚያም የክርስቶስን ዳግም ምጽአት አስመልክቶ ስለተነሡት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል ፤ ከእነ ዚህም ጥያቄዎች ጥቂቶቹ ፦

"ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት የሞተ አማኝ ፥ የክርስቶስ መመለስ በሚያስገኘው የዘላለም ሕይ ወት ተካፋይ ይሆናልን? ክርስቶስ ተመልሶ የሚመጣው መቼ ነው?" የሚሉት ናቸው ፤ ጳው ሎስም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም "የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በተስፋ እየተጠባበቃችሁ እስከ ዚያ ድረስ በጸጥታ ሥራችሁን ሥሩ" በማለት ይመክራቸዋል ።

---

## ምዕራፍ 1

1 የእግዚአብሔር አብና የጌታ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ወገኖች ለሆኑ
ለተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ፤
ከጳውሎስ ፥ ከሲላስና ከጢሞቴዎስ የተላከ ፤
ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ።

### የተሰሎንቄ ሰዎች ሕይወትና እምነት

2 ሁል ጊዜ በጸሎታችን እያስታወስናችሁ
በእናንተ ምክንያት ዘወትር እግዚአብሔርን እና
መሰግናለን ። 3 በእምነታችሁ ምክንያት እንዴት
እንደምትሠሩ ፥ በፍቅራችሁ ምክንያት እንዴት
እንደምትደክሙና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ያላችሁም ተስፋ እንዴት የጸና እንደሆነ ፥ በአ
ምላካችንና በአባታችን ፊት ያለማቋረጥ እናስታ
ውሳለን ። 4 በእግዚአብሔር የተወደዳችሁ ወንድ
ሞች ሆይ! እግዚአብሔር እንደመረጣችሁ እና
ውቃለን ። 5 ምክንያቱም ወንጌላችንን ያበሠርን
ላችሁ በቃል ብቻ ሳይሆን በኀይልና በመንፈስ
ቅዱስ ፥ ስለ ወንጌልም እውነት እርግጠኞች
በመሆን ነው ፤ ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ
ለእናንተ ጥቅም ብለን እንዴት እንደኖርን ታው
ቃላችሁ ። 6 ምንም እንኳ ብዙ መከራ ቢደርስባ
ችሁም ከመንፈስ ቅዱስ በተገኘ ደስታ ቃሉን
ተቀብላችሁ እኛንና ጌታ ኢየሱስን የምትመስሉ
ሆናችኋል ። 7 ስለዚህ በመቄዶንያና በአካይያ
ለሚገኙት ምእመናን ሁሉ መልካም ምሳሌ
ሆናችኋል ። 8 የእግዚአብሔር ቃል ከእናንተ
ወጥቶ የተሰማው በመቄዶንያና በአካይያ ብቻ
ሳይሆን በእግዚአብሔር ያላችሁ እምነት በሁሉ
ቦታ ታውቆ ነበር ፤ በዚህ ምክንያት እኛ ስለ
ዚህ ጉዳይ ምንም መናገር አያስፈልገንም ።
9 ወደ እናንተ በመጣን ጊዜ እንዴት እንደተቀበ
ላችሁን ፥ ሕያውና እውነተኛ የሆነውን አምላክ
ለማገልገል ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር እን
ዴት እንደተመለሳችሁ እነርሱ ራሳቸው ይመሰ
ክራሉ ። 10 እንዲሁም እግዚአብሔር ከሞት ያስ
ነሣውን ፥ ከሚመጣው ቍጣ የሚያድነንን ፥
የልጁን የኢየሱስን ከሰማይ መምጣት እንዴት
እንደምትጠባበቁም ይመሰክራሉ ።

## ምዕራፍ 2

### የጳውሎስ የሐዋርያነት ሥራ በተሰሎንቄ

1 ወንድሞች ሆይ! የእኛ ወደ እናንተ መም
ጣት ፍሬቢስ እንዳልሆነ እናንተ ራሳችሁ ታው
ቃላችሁ ። 2 እናንተ እንደምታውቁት ከዚህ
ቀደም በፊልጵስዩስ በነበርንበት ጊዜ መከራና

---

1፥1 ፦ ሐ.ሥ. 17፥1 ። 1፥6 ፦ ሐ.ሥ. 17፥5-9 ። 2፥2 ፦ ሐ.ሥ. 16፥19-24 ፤ 17፥1-9 ።

ስድብ ደርሶብናል ፤ ነገር ግን ታላቅ ተቃውሞ
ቢደርስብንም እንኳ ፥ የእግዚአብሔርን የምሥ
ራች ቃል እንድናበሥር አምላካችን ድፍረት
ሰጥቶናል ። 3 ምክንያቱም እኛ የመከርናችሁ
በስሕተት ወይም በርኵስ ዓላማ ተመርተን አይ
ደለም ፤ እናንተን ለማታለል ያደረግነው ምንም
ነገር የለም ። 4 ይልቅስ እግዚአብሔር የምሥራ
ቹን ቃል ለእኛ በዐደራ የሰጠን በእኛ ተማምኖ
ስለሆነ እንናገራለን ፤ ይህንንም የምናደርገው
ልባችንን የሚመረምረውን እግዚአብሔርን ደስ
ለማሰኘት ብለን ነው እንጂ ሰውን ለማስደሰት
ብለን አይደለም ። 5 በመደለል ወይም የገንዘብ
ፍላጎት ኖሮን ከቶ እንዳልተናገርን እናንተ ራሳ
ችሁ ታውቃላችሁ ፤ እግዚአብሔርም ምስክራ
ችን ነው ። 6 የክርስቶስ ሐዋርያት እንደመሆና
ችን መጠን በሥልጣናችን ልንጫናችሁ ስን
ችል ፥ ከእናንተም ሆነ ከሌሎች ከማንም ክብ
ርን አልፈለግንም ። 7 ነገር ግን ለልጆችዋ እንደ
ምትጠነቀቅ ሞግዚት ገሮች ሆንላችሁ ። 8 እንዲ
ሁም በጣም ስለወደድናችሁ ከታላቁ ፍቅራችን
የተነሣ የእግዚአብሔርን የምሥራች ቃል ለእና
ንተ ማብሠር ብቻ ሳይሆን ፥ ሕይወታችንንም
እንኳ ልንሰጣችሁ ዝግጁዎች ነበርን ። 9 ወንድ
ሞች ሆይ! እንዴት እንደሠራንና እንደደከምን
ታውቃላችሁ ፤ የእግዚአብሔርን የምሥራች
ቃል ስናበሥራችሁ ፥ ከእናንተ በአንዱም ላይ
ሸክም እንዳንሆንበት ሌሊትና ቀን በመሥራት
እንደክም ነበር ።
10 በእናንተ በአማኞች መካከል በነበርንበት
ጊዜ እንዴት ባለ ቅድስናና ጽድቅ ፥ ነቀፋም
በሌለበት ሕይወት እንደኖርን እናንተ ምስክሮች
ናችሁ ፤ እግዚአብሔርም ምስክር ነው ፤
11 አባት ለልጆቹ እንደሚያደርገው ዐይነት
እኛም ለእናንተ ለእያንዳንዳችሁ እንዳደረግንላ
ችሁ ታውቃላችሁ ፤ 12 ዘወትር እየመከርናች
ሁና እያበረታታናችሁ ፥ መንግሥቱንና ክብሩን
እንድትካፈሉ የጠራችሁ አምላክ ደስ በሚሰኝ
በት ሁኔታ እንድትኖሩ ዐደራ እንዳልናችሁ
ታውቃላችሁ ።
13 ደግሞም ስለ እናንተ ሳናቋርጥ እግዚአብ
ሔርን የምናመሰግንበት ምክንያት አለን ፤ ይኸ
ውም ከእኛ የሰማችሁትን የእግዚአብሔርን
ቃል በተቀበላችሁ ጊዜ ፥ በእናንተ በአማኞች
የሚሠራውን ይህንን ቃል የተቀበላችሁት እንደ
ሰው ቃል ሳይሆን ልክ እንደ እግዚአብሔር
ቃል አድርጋችሁ ነው ፤ በእርግጥም የእግዚአብ
ሔር ቃል ነው ። 14 ወንድሞች ሆይ! እናንተም
በይሁዳ አገር የሚገኙትን በኢየሱስ ክርስቶስ
የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት የሆኑትን
መስላችኋል ፤ ምክንያቱም እነርሱ በአይሁዳው
ያን መከራ እንደተቀበሉ ሁሉ ፥ እናንተም በገዛ
ወገኖቻችሁ መከራ ተቀብላችኋል ። 15 አይሁዳ
ውያን ጌታ ኢየሱስንና ነቢያትን የገደሉ ፥ እኛ
ንም አሳድደው ከአገር ያስወጡ ናቸው ፤ እነ
ርሱ እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑና ሰዎችን ሁሉ
የሚጠሉ ናቸው ፤ 16 ምክንያቱም አረማውያን
የሚድኑበትን ቃል እንዳንናገር እንኳ ይከለክሉ
ናል ፤ በዚህ ዐይነት ኃጢአትን በኃጢአት ላይ
እየጨመሩ ይሄዳሉ ፤ ስለዚህ በመጨረሻ የእግዚ
አብሔር ቍጣ መጥቶባቸዋል ።

### ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች እንደገና ለመጐብኘት የነበረው ምኞት

17 ነገር ግን ወንድሞች ሆይ! በመንፈስ ሳይ
ሆን በሥጋ ለጥቂት ጊዜ ከእናንተ በመለየታችን
ስለ እናንተ ያለን ናፍቆት ብዙ ስለሆነ በዐይነ
ሥጋ ልናያችሁ ተመኘን ። 18 ወደ እናንተ
መምጣት ፈልገን ነበር ፤ በተለይም እኔ ጳው
ሎስ ወደ እናንተ ለመምጣት ደጋግሜ ሞክሬ
ነበር ፤ ነገር ግን ሰይጣን ከለከለን ። 19 ታዲያ
ተስፋችን ወይም ደስታችን ወይም ጌታችን ኢየ
ሱስ በሚመጣበት ጊዜ በፊቱ የምንመካበት
የድል አክሊላችን እናንተ ካልሆናችሁ ፥ ሌላ
ማን ነው? 20 በእርግጥ ክብራችንና ደስታችን
እናንተ ናችሁ ።

## ምዕራፍ 3

1 ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ መጠበቅ ባለመቻ
ላችን በአቴና ብቻችንን መቅረት መልካም ሆኖ
ታየን ። 2 ወንድማችንንና የክርስቶስን መልካም
ዜና በማብሠር ከእኛ ጋር የእግዚአብሔር አገል
ጋይ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልከንላችኋል ፤ የላ
ክንላችሁም እንዲያጸናችሁና በእምነት እንድት
በረቱ ይመክራችሁ ዘንድ ነው ፤ 3 ይህም በደረሰ
ባችሁ መከራ እንዳትናወጡ ያደርጋችኋል ፤
ይህ መከራ ለእኛ የተወሰነልን ዕጣ መሆኑን
እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ ። 4 እንዲያውም
ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ መከራ እንደሚ
ደርስብን አስቀድመን እንነግራችሁ ነበር ፤ እን
ደምታውቁትም መከራው መጥቶ አልፎአል ፤
5 በዚህ ምክንያት ከእንግዲህ ወዲህ መጠበቅ
ባለመቻሌ ፥ ስለ እምነታችሁ ማወቅ ፈልጌ
ጢሞቴዎስን ወደ እናንተ ላክሁት ፤ እርሱን የላ
ክሁትም ምናልባት ፈታኙ ፈትኖአችሁ ይሆ
ናል ፤ ሥራችንም ከንቱ ሆኖ ቀርቶአል በማለት
ፈርቼ ነው ።
6 አሁን ግን ጢሞቴዎስ ከእናንተ ዘንድ ወደ
እኛ መጥቶ ስለ እምነታችሁና ስለ ፍቅራችሁ
ደስ የሚያሰኝ ወሬ ነገረን ፤ እንዲሁም እናንተ
ዘወትር በመልካም እንደምታስታውሱንና እኛ

2፡14 ፦ ሐሥ. 17፡5 ። 2፡15 ፦ ሐሥ. 9፡23 ፡29 ፤ 13፡45 ፡50 ፤ 14፡2 ፡5 ፡19 ፤ 17፡5 ፡13 ፤ 18፡12 ።
3፡1 ፦ ሐሥ. 17፡15 ። 3፡6 ፦ ሐሥ. 18፡5 ።



እናንተን ለማየት የምንናፍቃችሁን ያህል እናን
ተም እኛን ለማየት እንደምትናፍቁ ነገረን ።
7 ስለዚህ ወንድሞች ሆይ! ምንም እንኳ እኛ
የምንገኘው በችግርና በመከራ ውስጥ ቢሆንም ፥
በእምነታችሁ ምክንያት በእናንተ ተጽናንተ
ናል ። 8 ምክንያቱም የእናንተ በጌታ ኢየሱስ
ጸንቶ መኖር ለእኛ ሕይወታችን ነው ። 9 እነሆ
አሁን ስለ እናንተ ምስጋና እናቀርባለን ፤ በእናን
ተም ምክንያት በእርሱ ፊት ስላለን ደስታ እግ
ዚአብሔርን እናመሰግናለን ። 10 ሌሊትና ቀን
በብርቱ የምንጸልየው በዐይነ ሥጋ እንድናያች
ሁና በእምነታችሁ የጐደለውን ለመሙላት እን
ድንችል ነው ።
11 አሁንም ራሱ አባታችን የሆነው አምላክና
ጌታችን ኢየሱስ ወደ እናንተ እንድንመጣ መንገ
ዳችንን ያቅናልን ። 12 እኛ የምናፈቅራችሁን
ያህል ፥ እርስ በርስ ያላችሁን ፍቅርና ለሌሎ
ችም ያላችሁን ፍቅር ጌታ ይጨምርላችሁ ፤ ያብ
ዛላችሁም ፤ 13 በዚህ ዐይነት ጌታችን ኢየሱስ
ከቅዱሳን ሁሉ ጋር በሚመጣበት ጊዜ አባታችን
በሆነው በአምላካችን ፊት ልባችሁ ነቀፋ የሌለበ
ትና ቅዱስ እንዲሆን ያበረታችኋል ።

## ምዕራፍ 4

### እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት

1 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ! እግዚአብሔርን
ለማስደሰት እንዴት መኖር እንደሚገባችሁ
ከእኛ ተምራችኋል ፤ አሁንም የምትኖሩት እን
ዲሁ ነው ፤ በጌታ በኢየሱስ ስም የምንለምናች
ሁና የምንመክራችሁም ከዚህ በፊት ካደረጋች
ሁት ይበልጥ እንድታደርጉ ነው ። 2 በጌታ ኢየ
ሱስ ስም ምን ዐይነት የመመሪያ ትምህርት እን
ደሰጠናችሁ ታውቃላችሁ ። 3 የእግዚአብሔር
ፈቃድ እናንተ እንድትቀደሱና ከዝሙት እንድ
ትርቁ ነው ። 4 ከእናንተ እያንዳንዱ የገዛ ሰውነ
ቱን በቅድስናና በክብር ጠብቆ መያዝን
ይወቅ ። 5 እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አረማ
ውያን የፍትወት ምኞት አይኑረው ። 6 በዚህ
ነገር ማንም ወንድሙን አይበድል ፥ ወይም አያ
ታልል ፤ ከዚህ በፊት እንደነገርናችሁና እንዳስ
ጠነቀቅናችሁ ፥ እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉ
ትን ጌታ ይቀጣቸዋል ። 7 ምክንያቱም እግዚአ
ብሔር የጠራን በቅድስና እንድንኖር ነው እንጂ
በርኵሰት እንድንኖር አይደለም ። 8 ስለዚህ
ይህን ምክር የሚቃወም ፥ የሚቃወመው ቅዱስ
መንፈሱን የሚሰጣችሁን እግዚአብሔርን እንጂ
ሰውን አይደለም ።
9 እርስ በርስ ስለ መዋደድ እናንተ ራሳችሁ
ከእግዚአብሔር ስለ ተማራችሁ ፥ ስለዚህ ጕዳይ
ማንም ሊጽፍላችሁ አያስፈልግም ። 10 በመላ
መቄዶንያ ያሉትንም ወንድሞች ሁሉ ትወድዳ
ላችሁ ፤ ሆኖም ወንድሞች ሆይ! አሁን የምን
መክራችሁ ይበልጥ እንድትወዱና ፥ 11 በጸጥታ
ለመኖር እንድትጣጣሩ ፥ የራሳችሁን ጕዳይ እን
ድታስቡ ፥ ከዚህ በፊት እንዳዘዝናችሁም በገዛ
እጃችሁ እንድትሠሩ ነው ። 12 በዚህ ዐይነት
በማያምኑት ሰዎች ዘንድ የተከበራችሁ ትሆናላ
ችሁ ፤ የማንም ጥገኛ ሳትሆኑ ራሳችሁን ችላ
ችሁ ትኖራላችሁ ።

### የሕያዋንና የሙታን ሁኔታ በጌታ መምጫ ጊዜ

13 ወንድሞች ሆይ! ተስፋ እንደሌላቸው
ሰዎች እንዳታዝኑ ፥ ስለ ሞቱት ሰዎች እውነ
ቱን እንድታውቁ እንወዳለን ። 14 ኢየሱስ እንደ
ሞተና ከሞትም እንደተነሣ እናምናለን ፤ ስለ
ዚህ በኢየሱስ አምነው የሞቱትን እግዚአብሔር
ከኢየሱስ ጋር ያመጣቸዋል ።
15 ከጌታ በተቀበልነው ቃል መሠረት የምንነ
ግራችሁ ይህ ነው ፤ ጌታ እስከሚመጣበት ጊዜ
ድረስ ሕያዋን ሆነን የምንገኝ የሞቱትን አንቀ
ድምም ። 16 የትእዛዝ ድምፅ ፥ የመላእክት
አለቃ ድምፅ ፥ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰ
ማል ፤ ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል ፤ በክርስ
ቶስ አምነው የሞቱትም አስቀድመው ይነ
ሣሉ ። 17 ከዚህ በኋላ እኛ በሕይወት የምንገ
ኘው ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር
በደመና እንነጠቃለን ፤ ለዘላለምም ከጌታ ጋር
እንሆናለን ። 18 ስለዚህ በዚህ ቃል እርስ በርሳ
ችሁ ተጽናኑ ።

## ምዕራፍ 5

### የጌታን መምጣት ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ

1 ወንድሞች ሆይ! ይህ ነገር ስለሚሆንበት
ዘመንና ጊዜ ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈል
ግም ። 2 ምክንያቱም የጌታ ቀን የሚመጣው
ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ ዐይነት መሆኑን እና
ንተ ራሳችሁ ደህና አድርጋችሁ ታውቃላችሁ ።
3 ሰዎች “ሁሉ ነገር ሰላምና ደህና ነው”
ሲሉ ፥ እርጉዝ ሴትን ምጥ እንደሚይዛት ዐይ
ነት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ፤ በምንም
ዐይነት አያመልጡም ። 4 እናንተ ግን ወንድ
ሞች ሆይ! በጨለማ ውስጥ አይደላችሁም ፤ ስለ
ዚህ ቀኑ እንደ ሌባ አይመጣባችሁም ። 5 ምክን
ያቱም እናንተ ሁላችሁም የብርሃን ሰዎች ፥ የቀ
ንም ሰዎች ናችሁ ፤ እኛ የሌሊት ወይም የጨ
ለማ ሰዎች አይደለንም ። 6 ስለዚህ እኛ እን
ንቃ ፥ ራስን በመግዛት በመጠን እንኑር እንጂ
እንደ ሌሎቹ አናንቀላፋ ። 7 ምክንያቱም የሚያ
ንቀላፉ ሰዎች በሌሊት ያንቀላፋሉ ፤ የሚሰክ
ሩም በሌሊት ይሰክራሉ ። 8 እኛ ግን የብርሃን

4፡15-17 ፦ 1ቆሮ. 15፡51-52 ። 5፡2 ፦ ማቴ. 24፡43 ፤ ሉቃ. 12፡39 ፤ 1ጴጥ. 3፡10 ። 5፡8 ፦ ኢሳ. 59፡17 ፤ ኤፌ. 6፡13-17 ።

ሰዎች ስለሆንን ራስን በመግዛት በመጠን እን
ኑር፤ እምነትንና ፍቅርን እንደ ጥሩር እንል
በስ፤ የደኅንነትን ተስፋ እንደ ራስ ቍር እንል
በስ፤ 9 እግዚአብሔር የጠራን ለቍጣ ሳይሆን
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ደኅን
ትን እንድናገኝ ነው። 10 ክርስቶስ ስለ እኛ የሞ
ተው በሕይወት ብንሆን ወይም ብንሞት ከእ
ርሱ ጋር አብረን እንድንኖር ነው። 11 ስለዚህ
አሁን በምታደርጉት ዐይነት አንዱ ሌላውን
በማነጽ እርስ በርሳችሁ ተረዳዱ።

### የመጨረሻ ምክርና ሰላምታ

12 ወንድሞች ሆይ! በእናንተ መካከል
በሥራ የሚደክሙትን፣ በጌታ ኢየሱስ አለቆቻ
ችሁንና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን እንድታከብሩ
አቸው እንለምናችኋለን፤ 13 በሥራቸው ምክንያ
ትም ለእነርሱ ታላቅ አክብሮትና ፍቅር ይኑራ
ችሁ፤ እናንተም እርስ በርሳችሁ በሰላም ኑሩ።
14 ወንድሞች ሆይ! "ሰነፎችን ገሥጹ፤ ፈሪ
ዎችን አደፋፍሩ፤ ደካሞችን ዕርዱ፤ ሰውን
ሁሉ ታገሡ" ብለን እንመክራችኋለን።
15 ማንም ሰው በክፉ ፋንታ ክፉ እንዳይመልስ
ተጠንቀቁ፤ ይልቅስ ከእናንተ እያንዳንዱ ለሌ
ላው መልካም ለማድረግ ይትጋ፤ እንዲሁም
ለሌሎች ሰዎች ሁሉ መልካም ለማድረግ ትጉ።
16 ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ 17 ሳታቋርጥ
ጸልዩ፤ 18 በሁሉ ነገር እግዚአብሔርን አመስ
ግኑ፤ ምክንያቱም በኢየሱስ ክርስቶስ ባላችሁ
ሕይወት እግዚአብሔር ከእናንተ የሚፈልገው
ይህን ነው።
19 የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አታዳፍኑ፤
20 የትንቢትን ስጦታ አትናቁ፤ 21 ሁሉን ነገር
ፈትኑ፤ መልካም የሆነውን ያዙ። 22 ከማናቸ
ውም ዐይነት ክፉ ነገር ራቁ።
23 ራሱ የሰላም አምላክ በሁሉ ነገር ይቀድሳ
ችሁ፤ መንፈሳችሁ፣ ነፍሳችሁ፣ ሥጋችሁ
በሙሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚመጣበት
ቀን ያለ ነቀፋ ተጠብቆ ይኑር። 24 የሚጠራ
ችሁ ታማኝ ስለሆነ ይህን ያደርገዋል።
25 ወንድሞች ሆይ! ለእኛም ጸልዩልን።
26 በወንድማማችነት ስሜት በመሳሳም ለአማ
ኞች ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልን። 27 ይህ መልእ
ክት ለአማኞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ ስም
ዐደራ እላችኋለሁ።
28 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ
ጋር ይሁን።

# ሁለተኛው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

# ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

## መግቢያ

ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የተነሣው ጥያቄ ሁከት እየፈጠረ በመሄዱ በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ችግር ተባባሰ፤ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው ሁለተኛው መልእክት "የጌታ መምጫ ቀን ቀርቦአል" በሚለው እምነት ላይ ያተኰረ ነበር፤ ጳውሎስም "ከክርስቶስ መምጣት በፊት 'የዐመፅ ሰው' በተባለው በክርስቶስ ተቃዋሚ መሪነት በዓለም ላይ ክፋትና ዐመፅ እየበዛ ይሄዳል" በማለት የእነርሱን እምነት ለማረም ይሞክራል።

ሐዋርያው አንባቢዎቹ "መከራና ሥቃይ ቢበዛባቸው እንኳ በእምነታቸው እንዲጸኑ፣ እርሱና ሌሎች የሥራ ተባባሪዎች እንደሚያደርጉት ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ለማግኘት ተግተው እንዲሠሩ፣ እንዲሁም መልካም ሥራን ከማድረግ እንዳይቈጠቡ" አጥብቆ ይመክራቸዋል።

---

## ምዕራፍ 1

1 አባታችን በሆነው በእግዚአብሔርና በጌታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሆነችው
ለተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፣
ከጳውሎስ፣ ከሲላስና ከጢሞቴዎስ የተላከ፤
2 ከእግዚአብሔር አብና ከጌታ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

### በክርስቶስ መምጫ ቀን የሚሆን ፍርድ

3 ወንድሞች ሆይ! በእናንተ ምክንያት
እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመሰግናለን፤
ማመስገንም ተገቢያችን ነው፤ የምናመሰግነ
ውም እምነታችሁ ይበልጥ እያደገና የእያንዳ
ንዳችሁ የእርስ በርስ ፍቅር እየጨመረ በመ
ሄዱ ነው። 4 በደረሰባችሁ ስደትና መከራ

1፡1 ፦ ሐ.ሥ. 17፡1።



ሁሉ በመጽናታችሁና በእምነት በመገኘታ
ችሁ፣ የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት
በሆናችሁት በእናንተ እንመካለን።
5 ይህም የሚያመለክተው የእግዚአብሔር
ፍርድ ቅን መሆኑን ነው፤ በዚህ ዐይነት በተቀ
በላችሁት መከራ ምክንያት ለእግዚአብሔር
መንግሥት የበቃችሁ ትሆናላችሁ። 6 እግዚአብ
ሔር ቅን ፈራጅ በመሆኑ መከራ በሚያመጡባ
ችሁ ላይ መከራ ያመጣባቸዋል። 7 አሁን
መከራ ለምትቀበሉትም ከእኛ ጋር ዕረፍትን
ይሰጣችኋል። ይህም የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ
ከኀያላን መላእክቱ ጋር ከሰማይ በሚወርድበት
ጊዜ ነው፤ 8 ከሰማይ የሚወርደውም በሚንበለ
በል እሳት ነው፤ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን
የማያውቁትንና ለጌታችን ለኢየሱስ ወንጌል የማ
ይታዘዙትን ይበቀላል። 9 እነርሱ ከጌታ ፊትና
ከኀያል ክብሩ ተለይተው በዘላለም ጥፋት ይቀ
ጣሉ። 10 የሚቀጡትም በቅዱሳኑ ሊከበር፣
በሚያምኑትም ሁሉ ዘንድና የእኛንም ምስክር
ነት ተቀብላችሁ ባመናችሁት በእናንተም ዘንድ
ሊደነቅ በሚመጣበት ጊዜ ነው።
11 ይህን በማሰብ ስለ እናንተ ሳናቋርጥ የምን
ጸልየው፣ እግዚአብሔር ለጥሪው ብቁዎች እን
ዲያደርጋችሁና መልካም ለማድረግ ያላችሁን
ፈቃድና የእምነት ሥራችሁን ሁሉ በኀይሉ
እንዲፈጽምላችሁ ነው። 12 እንዲሁም የጌታችን
የኢየሱስ ስም በእናንተ እንዲከበርና እናንተም
በአምላካችንና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ
መሠረት በእርሱ እንድትከበሩ እንጸልያለን።

## ምዕራፍ 2

### የዐመፅ ሰው

1 ወንድሞች ሆይ! ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ
ክርስቶስ መምጣትና እኛም ከእርሱ ጋር ስለመሰ
ብሰባችን ጉዳይ የምንለምናችሁ ይህን ነው፤
2 በትንቢት ወይም በስብከት እንደተነገረ፣
ወይም ከእኛ በመልእክት እንደተጻፈ አድርጋ
ችሁ "የጌታ ቀን ደርሶአል" በማለት በቶሎ በአ
እምሮአችሁ አትናወጡ፣ አትደንግጡም፤
3 ማንም ሰው በምንም ዐይነት አያታልላችሁ፤
ምክንያቱም አስቀድሞ የመጨረሻው ክሕደት
ሳይሆንና ገሃነም የሚገባው የዐመፅ ሰው የሆነው
ሳይገለጥ፣ ያ ቀን አይመጣም። 4 ይህ የዐመፅ
ሰው፣ አምላክ ከተባለውና ከሚመለከው ሁሉ
በላይ ራሱን ከፍ በማድረግ የሚቃወም ነው፤
"እግዚአብሔር ነኝ" እያለም በእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ እንኳ ለመቀመጥ ይደፍራል።
5 ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ ይህን ነገር ነግ
ሬአችሁ እንደነበር አታስታውሱምን? 6 በተወሰ
ነለት ጊዜ እስኪገለጥ ድረስ አሁን እንዳይገለጥ
የሚከለክለው ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ።
7 ምክንያቱም በስውር ይሁን እንጂ የዐመፅ
ኀይል አሁንም በመሥራት ላይ ነው፤ ይህም
የሚሆነው አሁን የሚከለክለው ከመንገድ እስኪ
ወገድለት ድረስ ነው። 8 በዚያን ጊዜ ጌታ ኢየ
ሱስ በአፉ እስትንፋስ የሚያጠፋውና፣ ግርማዊ
በሆነው መምጣቱ የሚደመስሰው የዐመፅ ሰው
ይገለጣል። 9 የዐመፅ ሰው የሚመጣው በሰይጣን
ኀይል አሳሳች ተአምራትንና ምልክቶችን፣ አስ
ደናቂ ነገሮችንም በማድረግ ነው፤ 10 እንዲሁም
በሚጠፉት ሰዎች ላይ ልዩ ልዩ ክፉ ማታለል
በማድረግ ነው፤ እነዚህ ሰዎች የሚጠፉትም
ለመዳን የሚያበቃቸውን እውነት ስላልወደዱ
ነው። 11 በዚህ ምክንያት በሐሰት እንዲያምኑ
እግዚአብሔር የስሕተትን ኀይል ይልክባቸ
ዋል። 12 ይህም የሚሆነው እውነትን አናምንም
ብለው በኀጢአት የሚደሰቱ ሁሉ እንዲፈረድባ
ቸው ነው።

### ለደኅንነት የተመረጡ ሰዎች

13 በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ!
እኛ ግን በእናንተ ምክንያት እግዚአብሔርን
ሁል ጊዜ ማመስገን ይገባናል፤ የምናመሰግነ
ውም እናንተ በመንፈስ ቅዱስ በመቀደሳችሁና
በእውነት በማመናችሁ ምክንያት እንድትድኑ
እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹ አድርጎ ስለመረ
ጣችሁ ነው። 14 እግዚአብሔር እኛ ባበሠርና
ችሁ የምሥራች ቃል አማካይነት ለዚህ የጠራ
ችሁ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር እን
ድትካፈሉ ነው። 15 ስለዚህ ወንድሞች ሆይ!
ጸንታችሁ ቁሙ፤ በቃላችንም ሆነ በመልእክታ
ችን የሰጠናችሁን ትምህርት ያዙ።
16 ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የወደ
ደን፣ በጸጋውም የዘላለም መጽናናትን፣ መል
ካም ተስፋንም የሰጠን አባታችን እግዚአብ
ሔር፣ 17 መልካም የሆነውን ሁሉ እንድታደር
ጉና እንድትናገሩ ልባችሁን ያጽናኑት፤ ብርታ
ትም ይስጡአችሁ።

## ምዕራፍ 3

### ጳውሎስ "ለእኛ ጸልዩልን" አለ

1 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ! በእናንተ ዘንድ
እንደሆነው ሁሉ የጌታ ቃል እንዲስፋፋና እን
ዲከበር ለእኛ ጸልዩልን፤ 2 እንዲሁም ቃሉን
ተቀብለው የሚያምኑት ሁሉም ስላልሆኑ ከዐመ
ፀኞችና ከክፉ ሰዎች እንድንድን ጸልዩልን።
3 ጌታ ግን ታማኝ ነው፤ እርሱ ያበረ
ታችኋል፤ ከሰይጣንም ይጠብቃችኋል፤ 4 የምና
ዝዛችሁን አሁንም ሆነ ወደፊት እንደምትፈጽ
ሙት በጌታ እንተማመንባችኋለን።

1፡9 ፦ ኢሳ. 2፡10። 2፡1 ፦ 1ተሰ. 4፡15-17። 2፡4 ፦ ዳን. 11፡36፤ ሕዝ. 28፡2። 2፡8 ፦ ኢሳ. 11፡4።
2፡9 ፦ ማቴ. 24፡24።

5 ጌታ ልባችሁን ወደ እግዚአብሔር ፍቅርና
ወደ ክርስቶስ ትዕግሥት ይምራው ።

### የመሥራት ግዴታ

6 ወንድሞች ሆይ! ሥራ ፈት ከሆነውና
ከእኛ በተቀበላችሁት ትምህርት መሠረት ከማ
ይኖር ክርስቲያን ሁሉ እንድትለዩ በጌታ በኢየ
ሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን ። 7 ምክንያ
ቱም የእኛን ምሳሌነት መከተል እንደሚገባ
ችሁ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ ፤ እኛ ከእና
ንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ ያለ ሥራ አልተቀመ
ጥንም ፤ 8 የማንንም እንጀራ በብላሽ አልበላ
ንም ፤ ይልቅስ ከእናንተ በማንም ላይ ሸክም
እንዳንሆንበት በማለት ሌሊትና ቀን በመድከ
ምና በመጣር እንሠራ ነበር ። 9 እንዲህም ያደረ
ግነው እናንተ የእኛን ምሳሌነት እንድትከተሉ
ብለን ነው እንጂ ከእናንተ ዕርዳታ ለማግኘት
ሥልጣን ሳይኖረን ቀርቶ አይደለም ። 10 ምክንያ
ቱም ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ "ሊሠራ
የማይወድድ አይብላ" የሚል ደንብ ሰጥተና
ችሁ ነበር ።
11 ይህን ያልንበት ምክንያት በመካከላችሁ
አንዳንድ ሥራ ፈቶች እንዳሉ በመስማታችን
ነው ፤ እነዚህ ሰዎች በማያገባቸው ነገር እየገቡ
ሌሎችን ከማወክ በቀር ምንም ሳይሠሩ የሚኖሩ
ናቸው ። 12 እንደእነዚህ ያሉ ሰዎች በሥርዓት
እንዲኖሩና ሠርተው የራሳቸውን ምግብ እንዲበ
ሉም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛቸዋ
ለን ፤ እናስጠነቅቃቸዋለንም ።
13 እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ! ደከምን
ብላችሁ መልካም ከመሥራት አትቦዝኑ ።
14 በዚህ መልእክት ያስተላለፍንላችሁን ምክር
የማይቀበል ሰው ቢኖር ፥ እንዲህ ያለውን ሰው
ልብ በሉት ፤ እንዲያፍርም ከእርሱ ጋር አትተ
ባበሩ ። 15 ሆኖም እንደ ወንድም ምከሩት እንጂ
እንደ ጠላት አትቍጠሩት ።

### የመጨረሻ ሰላምታ

16 የሰላም ጌታ ራሱ ሁል ጊዜና በሁሉ ነገር
ሰላምን ይስጣችሁ ፤ ጌታ ከሁላችሁም ጋር
ይሁን ።
17 ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት እኔ
ጳውሎስ ነኝ ፤ በእኔ መልእክት ሁሉ የሚገኘው
ምልክት ይህ ነው ። የምጽፈውም እንዲህ
ነው ።
18 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላች
ሁም ጋር ይሁን ።

# የመጀመሪያው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ጢሞቴዎስ

## መግቢያ

ጢሞቴዎስ የተባለው ወጣት ክርስቲያን ፥ ትውልዱ ከታናሽቱ እስያ ሲሆን በእናቱ አይሁ ዳዊ ፥ በአባቱ ደግሞ ግሪካዊ ነበር ፤ የጳውሎስ ጓደኛና በወንጌል ተልእኮውም የቅርብ ረዳቱ ነበር ፤ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የጻፈለት የመጀመሪያው መልእክት በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ያተኰረ ነበር ፤

ከሁሉ በማስቀደም መልእክቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተነሥቶ ስለነበረው የሐሰት ትምህ ርት የሚያስጠነቅቅ ነበር ፤ ይህም ዕንግዳ ትምህርት በከፊል የአይሁዳውያንን ፥ በከፊል ደግሞ የአረማውያንን አሳብ የያዘ ሲሆን "የሚታየው ዓለም በኃጢአት የተበከለ ስለሆነ ድኅነት ሊገኝ የሚችለው ልዩ በሆነ ምስጢራዊ ዕውቀትና ከአንዳንድ ምግቦችና ከጋብቻ በመጠበቅ ነው" በሚል አሳብ ላይ የተመሠረተ ነበር ። በተጨማሪም መልእክቱ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደ ርና የአምልኮ ሥርዓት ትምህርታዊ መመሪያ ፥ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ረዳቶቻ ቸው ሊኖራቸው ስለሚገባ ጠባይ መግለጫ የያዘ ነው ። በመጨረሻም ጢሞቴዎስ ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ እንዴት ሊሆን እንደሚችልና በተለያዩ ማኅበረ ምእመናን ዘንድ ስላለው ኀላፊነት ጳውሎስ የሰጠውን ምክር እናገኛለን ።



## ምዕራፍ 1

1 አዳኛችን በሆነው በእግዚአብሔርና ተስፋ
ችን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ የኢየ
ሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከሆነ ከጳውሎስ ፥
2 በእምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነው ለጢሞ
ቴዎስ ፥
ከአባታችን ከእግዚአብሔር ፥ ከጌታችንም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም
ይሁን ።

### ከሐሰተኛ ትምህርት መጠንቀቅ

3 ወደ መቄዶንያ ስሄድ ሳለሁ በደራ እንዳል
ሁህ በኤፌሶን ተቀመጥ ፤ እዚያ ያሉ አንዳንድ
ሰዎች ሐሰተኛ ትምህርት እንዳያስተምሩና ፥
4 ወደ ተረትና መጨረሻ ወደሌለው ወደ ትው
ልዶች ቈጠራ እንዳይመለሱ እዘዛቸው ፤ እነዚህ
ነገሮች ክርክርን ያመጣሉ እንጂ በእምነት ለሚ
ደረገው ለእግዚአብሔር ሥራ አይጠቅሙም ።
5 የዚህ ትእዛዝ ዓላማ ግን ከንጹሕ ልብ ፥ ከመ
ልካም ኅሊና ፥ ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ
ፍቅር ነው ። 6 አንዳንድ ሰዎች ከእነዚህ ነገሮች
ተለይተው ወደ ከንቱ ክርክር ተመልሰዋል ።
7 ይህንንም የሚያደርጉት የሙሴ ሕግ መምህ
ራን ለመሆን ፈልገው ነው ፤ ይሁን እንጂ የሚ
ናገሩትን አያውቁም ወይም እርግጠኞች ነን
የሚሉበትንም ነገር አያስተውሉም ።
8 ሰው በሚገባ ከሠራበት ፥ ሕግ መልካም
መሆኑን እናውቃለን ፤ 9 እንዲሁም ሕግ የተሠ
ራው ለደጋግ ሰዎች እንዳልሆነ እናውቃለን ፤
ሕግ የተሠራው ለዐመፀኞችና ለወንጀለኞች ፥
ለከሐዲዎችና ለኃጢአተኞች ፥ ቅድስና ለሌላቸ
ውና መንፈሳዊ ነገርን ለሚንቁ ፥ አባትንና እና
ትን ለሚገድሉና ለነፍሰ ገዳዮች ፥ 10 ለአመንዝ
ሮችና ግብረ ሥጋን ከወንዶች ጋር ለሚያደርጉ
ወንዶች ፥ ሰውን ለሚሸጡ ነጋዴዎችና ለውሸ
ተኞች ፥ በሐሰት ለሚምሉና የእውነተኛ ትምህ
ርት ተቃራኒ የሆነውን ነገር ሁሉ ለሚያደርጉ
ነው ፤ 11 ይህ እውነተኛ ትምህርት የሚገኘ
ውም የተመሰገነውን የእግዚአብሔርን ክብር
ከሚያበሥረው ወንጌል ነው ፤ ይህም ወንጌል
ለእኔ በዐደራ የተሰጠኝ ነው ።

### ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ያቀረበው ምስጋና

12 እኔን ለአገልግሎት በመሾም ታማኝ እንድ
ሆን ያበቃኝንና ብርታት የሰጠኝን ጌታችንን
ኢየሱስ ክርስቶስን አመሰግናለሁ ። 13 ምንም
እንኳ ከዚህ ቀደም ክርስቶስን የሰደብሁና ያሳደ
ድሁ ፥ ያዋረድሁም ብሆን ፤ እርሱ ምሕረት
አደረገልኝ ፤ ምክንያቱም ይህን ሁሉ ያደረግ
ሁት ባለማወቅና ባለማመን ስለነበረ ነው ።
14 ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለን ኅብረት ምክን
ያት ከሚገኘውም እምነትና ፍቅር ጋር የእግዚ
አብሔር ጸጋ ይበልጥ በዛልኝ ። 15 "ኢየሱስ ክር
ስቶስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደ ዓለም መጣ"
የሚለው ቃል ፥ እውነተኛና ሰው ሁሉ ሊቀበ
ለው የሚገባ ነው ፤ ከኃጢአተኞች ሁሉ የባስሁ
ኃጢአተኛ እኔ ነኝ ። 16 ነገር ግን ምሕረት ተደ
ረገልኝ ፤ ምሕረት የተደረገልኝም ፥ ኢየሱስ ክር
ስቶስ ወሰን የሌለውን ትዕግሥቱን ከሁሉ የባ
ስሁ ኀጢአተኛ በሆንሁት በእኔ ላይ በማሳየት
በእርሱ ለሚያምኑና የዘላለም ሕይወት ለሚያ
ገኙ ምሳሌ እንድሆን ነው ። 17 ስለዚህ ዘላለማዊ
ንጉሥ ለሆነው ፥ ለማይሞተው ፥ ለማይታየው
ለአንዱ አምላክ ክብርና ምስጋና ለዘላለም
ይሁን ፤ አሜን ።
18 ልጄ ጢሞቴዎስ ሆይ! ከዚህ ቀደም ስለ
አንተ በትንቢት በተነገረው መሠረት ይህን ትእ
ዛዝ በዐደራ እሰጥሃለሁ ፤ "ትንቢቱን በመከተል
መልካም ጦርነትን ተዋጋ ፤ 19 እምነትና መል
ካም ኅሊና ይኑርህ ፤" አንዳንድ ሰዎች ኅሊናቸ
ውን በመጣላቸው እምነታቸውን አጥፍተዋል ።
20 ከእነርሱ መካከል ሄሜኔዎስና እስክንድር ይገ
ኛሉ ፤ እነርሱ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ
ቃል ከመናገር መቈጠብን እንዲማሩ ለሰይጣን
አሳልፌ የሰጠኋቸው ናቸው ።

## ምዕራፍ 2

### የቤተ ክርስቲያን ጸሎት

1 ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ልመና ፥
ጸሎት ፥ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች ሁሉ እንዲደ
ረግ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ ። 2 በመንፈሳዊነ
ትና በመልካም ጠባይ እየተመራን በሰላምና
በጸጥታ እንድንኖር በተለይ ለነገሥታትና በሥል
ጣን ላይ ላሉ ሁሉ ጸልዩ ። 3 ይህም በአዳኛችን
በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ
ነገር ነው ። 4 ምክንያቱም የእግዚአብሔር
ፈቃድ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን እንዲ
ያውቁ ነው ። 5 እግዚአብሔር አንድ ነው ፤ በመ
ካከል ሆኖ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስታር
ቀውም አንድ ነው ፤ እርሱም ሰው የሆነው ኢየ
ሱስ ክርስቶስ ነው ። 6 ሰዎችን ሁሉ ከኃጢአት
ለመዋጀት ራሱን ቤዛ አድርጎ የሰጠ እርሱ
ነው ፤ ይህም ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ የእግዚአ
ብሔርን የማዳን ፍላጎት የሚያስረዳ ምስክርነት
ነው ። 7 እኔም እምነትንና እውነትን ለማብሠር
ሐዋርያና አስተማሪ ሆኜ ወደ አረማውያን የተላ
ክሁት በዚህ ምክንያት ነው ፤ ይህንንም ስል
እውነት እናገራለሁ እንጂ አልዋሽም ።
8 እንግዲህ በየስፍራው ያሉ ወንዶች ቍጣ
ንና ጥልን አስወግደው የተቀደሱ እጆቻቸውን
ወደ ላይ በማንሣት እንዲጸልዩ እፈልጋለሁ ።

1፥2 ፡- ሐ.ሥ. 16፥1 ። 1፥13 ፡- ሐ.ሥ. 8፥3 ፤ 9፥4-5 ። 2፥7 ፡- 2ጢሞ. 1፥11 ።

9 እንዲሁም ሴቶች ጠጕርን በመሠራት ወይም
በወርቅ ወይም በዕንቍ ወይም ውድ በሆነ
ልብስ ማጌጥ ሳይሆን፣ በማፈርና በትሕትና
ተገቢ የሆነ ልብስ ይልበሱ። 10 እግዚአብሔርን
እናመልካለን የሚሉ ሴቶች ማድረግ በሚገባ
ቸው ዐይነት በመልካም ሥራ ያጊጡ። 11 ሴት
በጸጥታና በመታዘዝ ትማር፤ 12 ሴት ወንድን
እንድታስተምር ወይም በወንድ ላይ ሥልጣን
እንዲኖራት አልፈቅድም፤ እርስዋ ዝም ማለት
ይገባታል። 13 ምክንያቱም በመጀመሪያ የተፈ
ጠረ አዳም ነው፤ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች።
14 ደግሞም የተታለለችውና የእግዚአብሔርን
ሕግ ያፈረሰችው ሴት ናት እንጂ የተታለለው
አዳም አይደለም። 15 ነገር ግን ሴት በእምነትና
በፍቅር በቅድስናም ብትጸናና በትሕትና ብት
ኖር ልጅ በመውለድ ትድናለች።

## ምዕራፍ 3

### የቤተ ክርስቲያን መሪዎች (ኤጲስ ቆጶሳት)

1 አንድ ሰው "የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመ
ሆን ቢፈልግ ክቡር ሥራን ይመኛል" የሚለው
ቃል እውነተኛ ነው። 2 ስለዚህ የቤተ ክርስቲ
ያን መሪ እንዲህ መሆን ይገባዋል፣ "ነቀፋ የሌ
ለበት፣ አንዲት ሚስት ብቻ ያገባ፣ በመጠን
የሚኖር፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዓት የሚሠራ፣
እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር ችሎታ ያለው፣
3 የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ገር፣ ሰላማዊ
የሆነ፣ ገንዘብን የማያፈቅር፣ 4 የገዛ ራሱን ቤተ
ሰብ በደንብ ማስተዳደር የሚችል፣ ልጆቹ በአ
ክብሮት የሚታዘዙለትና የተከበረ።" 5 ሰው
የገዛ ራሱን ቤተሰብ ማስተዳደር የማይችል
ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ማስተ
ዳደር እንዴት ይችላል! 6 በትዕቢት ተነፍቶ
ዲያብሎስ እንደ ተፈረደበት እንዳይፈረድበት፣
አዲስ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን መሪ አይ
ሁን። 7 በነቀፋና በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ እን
ዳይወድቅ፣ በማያምኑ ሰዎች ዘንድ መልካም
ስም እንዲኖረው ያስፈልጋል።

### ስለ ዲያቆናት

8 እንዲሁም ዲያቆናት የተከበሩና በቃላቸው
የሚታመኑ፣ ብዙ የወይን ጠጅ የማይጠጡ፣
ለገንዘብ የማይስገበገቡ መሆን አለባቸው፤ 9 እን
ዲሁም የእምነትን ምስጢር በንጹሕ ኅሊና
የሚጠብቁ መሆን ይገባቸዋል፤ 10 እነርሱም
በመጀመሪያ ይፈተኑ፤ ከዚያም በኋላ ነቀፋ የሌ
ለባቸው ሆነው ከተገኙ በዲቁና ሥራ ያገል
ግሉ። 11 እንዲሁም ሚስቶቻቸው መልካም
ጠባይ ያላቸውና ሰውን የማያሙ፣ በመጠን
የሚኖሩ፣ በሁሉም ነገር ታማኞች መሆን ይገባ
ቸዋል። 12 ዲያቆናት እያንዳንዳቸው የአንዲት
ሚስት ባል መሆን ይገባቸዋል፤ ልጆቻቸውንና
ቤተሰቦቻቸውንም በመልካም ይዞታ ማስተዳ
ደር አለባቸው። 13 በዲቁና ሥራ መልካም አገ
ልግሎት የሚያበረክቱ ከፍ ያለ ማዕርግ ያገ
ኛሉ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላለውም እምነት
የመናገር ድፍረት ይኖራቸዋል።

### ታላቁ ምስጢር

14 ይህን መልእክት ስጽፍልህ በፍጥነት ወደ
አንተ መጥቼ እንደማይህ ተስፋ በማድረግ
ነው። 15 ብዘገይም በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ
መካከል፣ ሰዎች እንዴት መኖር እንደሚገባ
ቸው እንድታውቅ ጽፌልሃለሁ፤ ይህም ቤተሰብ
የእውነት ዐምድና መሠረት የሆነው የሕያው
እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው። 16 የሃይማ
ኖታችን ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤ እር
ሱም ስለ ክርስቶስ ሲነገር፣

"ሰው በመሆን የተገለጠ፤
እውነተኛነቱ በመንፈስ የታወቀ፤
ለመላእክት የታየ፤
ለሕዝቦች ሁሉ የተሰበከ፤
በዓለም ያሉ ሰዎች ያመኑበት፤
በክብር ወደ ሰማይ የወጣ" የሚል
ነው።

## ምዕራፍ 4

### ሐሰተኞች መምህራን

1 መንፈስ ቅዱስ ግን በግልጥ እንዲህ ይላል፣
"በኋለኛው ዘመን አንዳንድ ሰዎች አሳሳች መና
ፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት በመከተል ሃይ
ማኖትን ይክዳሉ።" 2 እንዲህም ዐይነቱ ትምህ
ርት የሚመነጨው በግብዝነት ሐሰትን ሲናገሩ
በጋለ ብረት እንደተተኰሰ ያህል ሆኖ የደነዘዘ
ኅሊናቸው ከማይወቅሳቸው ሰዎች ነው። 3 እን
ደእነዚህ ያሉት ሰዎች ጋብቻን ይከለክላሉ፤
የሚያምኑና እውነትን የሚያውቁ ሰዎችም እግ
ዚአብሔርን እያመሰገኑ እንዲመገቡት የፈጠረላ
ቸውን ምግብ "አትብሉ" እያሉ ይከለክላሉ።
4 ዳሩ ግን እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ
መልካም ነው፤ ከምስጋና ጋር ከተመገቡት
ምንም የሚጣል ነገር የለም። 5 ምክንያቱም
በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ይሆ
ናል።

### የክርስቶስ መልካም አገልጋይ ስለመሆን

6 ይህን ትምህርት ለአማኞች ብታስገነዝብ፣
የእምነትን ቃልና መልካም ትምህርትን እየተ
መገብህ ያደግህ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም
አገልጋይ መሆንህን ታስመሰክራለህ። 7 የመበለ
ቶችን ተረት ከሚመስል ምንም ጥቅም ከሌለው
ከዓለማዊ አፈ ታሪክ ራቅ፤ በመንፈሳዊ ነገርም

2፡9 ፦ 1ጴጥ. 3፡3 ። 2፡13 ፦ ዘፍ. 2፡7፤21-22 ። 2፡14 ፦ ዘፍ. 3፡1-6 ። 3፡2-7 ፦ ቲቶ 1፡6-9 ።



ራስህን አለማምድ። 8 ምክንያቱም በሰውነት
ማጠንከሪያ ትምህርት ራስን ማለማመድ ጥቅሙ
ጥቂት ነው፤ ራስን በመንፈሳዊ ነገር ማለማ
መድ ግን ለአሁንና ለሚመጣው ሕይወት ተስፋ
ስላለው ለሁሉ ነገር ይጠቅማል። 9 ይህም አባ
ባል ሰው ሁሉ ሊቀበለው የሚገባ እውነተኛ
ነገር ነው። 10 እኛም የምንታገለውና[1*] በሥራ
የምንደክመው ለዚሁ ነው፤ ምክንያቱም እኛ
ተስፋችንን የጣልነው ሰዎችን ሁሉ ይልቁንም
የሚያምኑትን ሁሉ በሚያድን በሕያው አምላክ
ነው።

11 እነዚህን ነገሮች እዘዝ፣ አስተምርም፤
12 ወጣት በመሆንህ ማንም አይናቅህ፤ ይልቅስ
በንግግር፣ በኑሮ፣ በፍቅር፣ በእምነትና በንጽ
ሕና ለአማኞች መልካም ምሳሌ ሁን። 13 እኔ
እስክመጣ ድረስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለሕዝብ
በማንበብ፣ በመስበክና በማስተማር ትጋ።
14 ትንቢት በተነገረልህ ጊዜና የቤተ ክርስቲያን
ሽማግሌዎችም እጃቸውን በጫኑብህ ጊዜ የተሰ
ጠህን በአንተ ያለውን መንፈሳዊ ስጦታ አትዘ
ንጋ። 15 መሻሻልህን ሰዎች ሁሉ እንዲያዩ፣
በእነዚህ ነገሮች ትጋ፤ እነዚህንም ነገሮች
በሥራ ላይ በማዋል ሰውነትህን በሙሉ ለእነ
ርሱ ስጥ። 16 ለራስህና ለማስተማር ሥራህ ተጠ
ንቀቅ፤ በእነዚህም ነገሮች ጽና፤ ምክንያቱም
ይህን ስታደርግ ራስህንና የሚሰሙህንም ታድና
ለህ።

## ምዕራፍ 5

### ስለ መበለቶች የተሰጠ ምክር

1 ሽማግሌን እንደ አባትህ አድርገህ ምከረው
እንጂ አትገሥጸው፤ ወጣቶች ወንዶችን እንደ
ወንድሞች፣ 2 አሮጊቶችን እንደ እናቶች አድር
ገህ ተመልከታቸው፤ እንዲሁም ወጣት ሴቶችን
እንደ እኅቶች አድርገህ በፍጹም ንጽሕና ተመ
ልከታቸው።

3 በእርግጥ መበለቶች የሆኑትን ሴቶች አክብ
ራቸው። 4 ማንኛይቱም መበለት፣ ልጆች
ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሩአት፣ እነዚህ ልጆች
አስቀድመው ለቤተሰዎቻቸው የመጠንቀቅን፣
ለወላጆቻቸውና ለአያቶቻቸው ብድር የመመለ
ስን መንፈሳዊ ግዴታ ይማሩ፤ ምክንያቱም ይህ
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው። 5 በእ
ርግጥ መበለት የሆነችና ብቻዋን የምትኖር፣
ተስፋዋን በእግዚአብሔር አድርጋ ሌሊትና ቀን
የእግዚአብሔርን ዕርዳታ በመለመን በጸሎት
ጸንታ ትኖራለች። 6 የዚህን ዓለም ደስታ ብቻ
የምትወድ መበለት ግን በቁሟ የሞተች ናት።
7 ያለ ነቀፋ እንዲኖሩም ምከራቸው። 8 ለራሱ
ዘመዶች፣ ይልቁንም ለቅርብ ቤተ ሰዎቹ የማያ
ስብ ሃይማኖቱን የካደ ነው፤ እንዲያውም ከማያ
ምን ሰው እንኳ የባሰ ክፉ ነው።

9 ከስልሳ ዓመት በታች የሆነችን መበለት
በመበለቶች መዝገብ አትጻፍ፤ ደግሞም አንድ
ባል ብቻ ያገባች እንድትሆን ያስፈልጋል።
10 እንዲሁም ልጆችን በሚገባ በማሳደግ፣ እንግ
ዳን በመቀበል፣ የቅዱሳንን እግር በማጠብ፣
የተቸገሩትን በመርዳትና ማንኛውንም በጎ ሥራ
ሁሉ በማከናወን በመልካም ሥራዋ ሁሉ የተመ
ሰከረላት መሆን አለባት።

11 በዕድሜአቸው ያልገፉትን መበለቶች ግን
በመበለቶች መዝገብ አትጻፋቸው፤ ምክንያቱም
እነርሱ ሥጋዊ ምኞታቸው አሸንፎአቸው ለክር
ስቶስ ያላቸው ፍቅር ሲቀንስ፣ ባል ማግባት
ይፈልጋሉ። 12 በመጀመሪያ ለክርስቶስ የገቡትን
ቃል በማፍረሳቸውም ይፈረድባቸዋል። 13 ከዚ
ህም በላይ ሥራ መፍታትንና በየሰው ቤት መዞ
ርን ይማራሉ፤ ሥራ መፍታት ብቻ ሳይሆን
ሰውን የሚያሙ፣ በሰው ነገር የሚገቡና መና
ገር የማይገባቸውን የሚናገሩ ይሆናሉ። 14 ስለ
ዚህ በዕድሜአቸው ያልገፉ መበለቶች እንዲያ
ገቡ፣ ልጆችን እንዲወልዱ፣ ቤታቸውንም
በሚገባ እንዲያስተዳድሩ እመክራለሁ፤ በዚህ
ዐይነት ጠላት የሚሳደብበትን ምክንያት
ያጣል። 15 ምክንያቱም ከዚህ በፊት አንዳንድ
መበለቶች ሰይጣንን ለመከተል ከእምነት መን
ገድ ወጥተዋል። 16 አማኝ የሆነች ሴት በቤትዋ
መበለቶች ቢኖርዋት የቤተ ክርስቲያን ሸክም
እንዳይሆኑ እርስዋ ትርዳቸው፤ በዚህ ዐይነት
ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ረዳት የሌላቸውን መበ
ለቶች መርዳት ትችላለች።

17 ቤተ ክርስቲያንን በደንብ የሚያስተዳ
ድሩ፣ ይልቁንም የምሥራቹን ቃል በመስበክና
በማስተማር የሚደክሙ ሽማግሌዎች እጥፍ
ክብር ይገባቸዋል፤ 18 ምክንያቱም መጽሐፍ
"እህል የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር!"
እንዲሁም "ለሠራተኛው ደመወዝ ይገባዋል"
ይላል። 19 ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ካልመሰ
ከሩበት በቀር በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ላይ
የሚቀርበውን ክስ አትቀበል። 20 ሌሎች እንዲ
ፈሩ ኃጢአት የሚሠሩትን በሰዎች ሁሉ ፊት
ገሥጽ።

21 በምታደርገው ነገር ሁሉ አንዱን ከሌላው
ሳታበላልጥ ወይም ለማንም ሳታዳላ ይህን ምክ
ሬን ሁሉ እንድትፈጽም በእግዚአብሔርና በኢ
የሱስ ክርስቶስ፣ በተመረጡትም መላእክት ፊት
ዐደራ እልሃለሁ። 22 እጆችህን በመጫን ማን
ንም ለመሾም አትቸኩል፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር
በኃጢአት አትተባበር፤ ራስህን በንጽሕና
ጠብቅ።

[1*] 4፡10 የምንታገለው ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "የምንሰደበው" ይላሉ።

5፡18 ፦ ዘዳ. 25፡4፤ ማቴ. 10፡10፤ ሉቃ. 10፡7 ። 5፡19 ፦ ዘዳ. 17፡6፤ 19፡15 ።

23 ስለ ሆድህ ሕመምና ስለ ዘወትር ደዌህ
ምክንያት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ ከእን
ግዲህ ወዲህ ውሃ ብቻ አትጠጣ ።
24 የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአት ግልጥ ነው ፤
ቀድሞአቸውም ወደ ፍርድ ይሄዳል ፤ የሌሎች
ሰዎች ኃጢአት ግን ከኋላቸው ይከተላቸዋል ።
25 እንዲሁም መልካም ሥራ ግልጥ ነው ፤
ግልጥ ያልሆነውም እንኳ ተሰውሮ አይቀርም ።

## ምዕራፍ 6

### ለአገልጋዮች የተሰጠ ምክር

1 የእግዚአብሔር ስምና ትምህርቱም እንዳይ
ሰደብ አገልጋዮች ሁሉ ፥ ጌቶቻቸው መከበር
እንደሚገባቸው አድርገው ያስቡ ። 2 ጌቶቻቸው
አማኞች የሆኑ አገልጋዮች በጌታ ኢየሱስ ወን
ድሞቻቸው ስለሆኑ አይናቁአቸው ፤ ይልቅስ
ከአገልግሎታቸው ጥቅም የሚያገኙ ጌቶቻቸው
አማኞችና የተወደዱ ወንድሞቻቸው ስለሆኑ
ከበፊት ይበልጥ ያገልግሉአቸው ። ማስተማርና
መምከር የሚገባህ ይህን ነው ።

### ሐሰተኛ ትምህርትና እውነተኛ ሀብት

3 ከእውነተኛ የሃይማኖት ትምህርት ጋር
ተስማሚ የሆነውን ፥ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስ
ቶስን ንጹሕ ቃል ትቶ ፥ የተለየ ትምህርት የሚ
ያስተምር ማንም ሰው ቢኖር ፤ 4 በትዕቢት የተ
ወጠረና ምንም የማያውቅ ነው ፤ ነገር ግን ስለ
ቃላት የመከራከርና የመጨቃጨቅ ክፉ ምኞት
አድሮበታል ፤ ይህም የሚያስከትለው ቅንአትን ፥
ጠብን ፥ ስድብን ፥ መጥፎ ጥርጣሬን ፥ 5 አእም
ሮአቸው በረከሰና እውነት በጠፋባቸው ሰዎች
የሚደረግ የማያቋርጥ ክርክርን ነው ፤ እንዲህ
ያሉት ሰዎች ሃይማኖት የሀብት ማግኛ ዘዴ
መስሎ ይታያቸዋል ።
6 በእርግጥ “ያለኝ ይበቃኛል” የሚል
ሰው ፥ ፍጹም መንፈሳዊነትን ስለሚያተርፍበት
ሃይማኖት የሀብት ምንጭ ነው ። 7 ምክንያቱም
ወደዚህ ዓለም ምንም ይዘን አልመጣንም ፤ ከዚ
ህም ዓለም ይዘነው የምንሄድ ምንም ነገር
የለም ። 8 የምንበላውንና የምንለብሰውን ካገኘን
ይበቃናል ። 9 ሀብታሞች ለመሆን የሚፈልጉ
ግን በፈተና ይወድቃሉ ፤ ሰዎችን በሚያበላሽና
በሚያጠፋ ከንቱና አደገኛ በሆነ በብዙ ምኞት
ወጥመድም ይያዛሉ ። 10 ምክንያቱም የገንዘብ
ፍቅር የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው ፤ አንዳንድ
ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት በመመኘት ከእምነት
ርቀዋል ፤ ልባቸውንም በሐዘን ጦር ወግተዋል ።

### ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ
### የሰጠው ምክርና ትእዛዝ

11 የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! አንተ ግን
ከዚህ ሁሉ ሽሽ ፤ ጽድቅን ፥ መንፈሳዊነትን ፥
እምነትን ፥ ፍቅርን ፥ በትዕግሥት መጽናትን ፥
ገርነትን ተከታተል ። 12 የእምነትን መልካም
ጦርነት ተዋጋ ፤ በብዙ ምስክሮች ፊት በመል
ካም መታመን መስክረህ የተጠራህበትን የዘላ
ለም ሕይወት ያዝ ። 13 ለሁሉ ነገር ሕይወት
በሚሰጠው በእግዚአብሔርና በጴንጤናዊው
ጲላጦስ ፊት በመልካም መታመን በመሰከረው
በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት አዝዛለሁ ። 14 ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሚገለጥበት ቀን ድረስ
ይህን ትእዛዝ ያለ ስሕተትና ያለ ነቀፋ ጠብቅ ።
15 የክርስቶስም መገለጥ ፥ የተባረከና ብቻውን
ገዥ የሆነ ፥ የነገሥታት ንጉሥ ፥ የጌቶች ጌታ
በወሰነው ቀን ይሆናል ፤ 16 እርሱ ብቻ የማይ
ሞት ነው ፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብር
ሃን ይኖራል ፤ እርሱን ከቶ ማንም አላየውም ፤
ማንም ሊያየውም አይችልም ፤ ክብርና ኀይል
ለዘላለም ለእርሱ ይሁን ፤ አሜን ።
17 የዚህ ዓለም ሀብታሞች እንዳይታበዩ
ወይም ተስፋቸውን በሚጠፋ ሀብት ላይ እንዳያ
ደርጉ እዘዛቸው ፤ እንዲሁም ተስፋቸው እኛን
ደስ እንዲለን ሁሉን ነገር አትረፍርፎ በሚሰ
ጠን በእግዚአብሔር ላይ እንዲሆን እዘዛቸው ።
18 ደግሞም መልካም ሥራ እንዲሠሩ ፥ በመል
ካም ሥራ ሀብታሞች እንዲሆኑ ፥ ለመለገሥና
ያላቸውንም ለማካፈል ዝግጁዎች እንዲሆኑ እዘ
ዛቸው ። 19 በዚህ ዐይነት እውነተኛውን ሕይ
ወት ለማግኘት መሠረቱ ጽኑ የሆነውን ሀብት
በሚመጣው ዘመን ለራሳቸው ያከማቻሉ ።
20 ጢሞቴዎስ ሆይ! በዐደራ የተሰጠህን
ጠብቅ ፤ ዕውቀት ሳይሆን “ዕውቀት” ስለሚመ
ስለው ነገር ከከንቱ ልፍለፋና ክርክር ራቅ ።
21 አንዳንዶች እንዲህ ዐይነቱ ዕውቀት አለን
በማለት ከእምነት መንገድ ወጥተዋል ።
ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን ።

6፡13 ፦ ዮሐ. 18፡37 ።

# ሁለተኛው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ጢሞቴዎስ

### መግቢያ

ይህ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የጻፈው ሁለተኛው መልእክት ፥ ጳውሎስ የቅርብ ረዳቱና የሥራ ተባባሪው ለሆነው ለወጣቱ ጢሞቴዎስ የሰጠውን ምክር የያዘ ነው ፤ አብዛኛውም የመከረው በትዕግሥት ስለ መጽናት ነው ፤ ጢሞቴዎስ የምክርና የማበረታቻ ቃል ያገኘው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በታማኝነት እንዲመሰክር ፥ የምሥራቹን ቃልና የብሉይ ኪዳንን ትምህርት አጥብቆ እንዲይዝና ምንም እንኳ መከራና ተቃውሞ ቢበዛበት በማስተማርና በወንጌል ሰባኪነት ሥራው እንዲተጋ ነበር ።

ጢሞቴዎስ በተለይ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ከሞኝነትና ከከንቱ ክርክር እንዲርቅ ነበር ፤ ምክንያቱም እንዲህ ዐይነቱ ነገር የሚሰሙትን ከማጥፋት በቀር ሌላ የሚሰጠው ጥቅም የለውም ።

በዚህ ሁሉ ጢሞቴዎስ ማስታወስ የነበረበት የጳውሎስን ሕይወትና የኑሮ ዓላማ በተለይም እምነቱን ፥ ትዕግሥቱን ፥ ፍቅሩን ፥ መጽናቱንና በስደት የደረሰበትን መከራ በምሳሌነት ስለመከተሉ ነበር ።

---

## ምዕራፍ 1

1 በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው የሕይወት
ተስፋ መሠረት በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየ
ሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ የተ
ላከ ፥
2 ለተወደድኸው ልጄ ለጢሞቴዎስ ፥
ከእግዚአብሔር አብና ከጌታችንም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም ለአንተ
ይሁን ።

### ለጢሞቴዎስ የተሰጠ ምክር

3 ዘወትር ሌሊትና ቀን አንተን በጸሎቴ ሳስ
ታውስ ፥ እንደ አባቶቼ በንጹሕ ኅሊና የማገለግ
ለውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ። 4 እንባህን
አስታውሳለሁ ፤ ስለዚህ በጣም ደስ እንዲለኝ
አንተን ለማየት እመኛለሁ ። 5 በአንተ ያለውን
እውነተኛ እምነት አስታውሳለሁ ፤ እንዲህ ዐይ
ነቱ እምነት በመጀመሪያ በአያትህ በሎይድና
በእናትህ በኤውኒቄ የነበረ ነው ፤ በአንተም እን
ዳለ ተረድቻለሁ ። 6 በዚህ ምክንያት እጆቼን
በአንተ ላይ በጫንሁ ጊዜ የተሰጠህንና የእግዚአ
ብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣው አሳስብሃለሁ ።
7 ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጠን የኀይልና
የፍቅር ፥ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍ
ርሃት መንፈስ አይደለም ።
8 እንግዲህ ስለ ጌታችን ለመመስከር አት
ፈር ፤ ስለ እርሱ በታሰርሁት በእኔም አትፈር ፤
ነገር ግን እግዚአብሔር በሚሰጥህ ኀይል መጠን
ስለ ወንጌል ከእኔ ጋር የመከራ ተካፋይ ሁን ።
9 እርሱ እኛ ስላደረግነው መልካም ሥራ ሳይ
ሆን በራሱ ፈቃድና በጸጋው አዳነን ፤ ለቅድስ
ናም ጠራን ፤ ይህንንም ጸጋ ከዘመናት በፊት
በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ሰጠን ። 10 ይህም
ጸጋ አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመምጣቱ
አሁን ተገለጠ ። እርሱ የሞትን ኀይል ደምስሶ
በወንጌል አማካይነት ሞት የሌለበትን ዘላለማዊ
ሕይወት ገለጠልን ።
11 እኔም የዚህ ወንጌል አብሣሪ ፥ ሐዋርያ ፥
አስተማሪ ሆኜ ተሾሜአለሁ ። 12 ይህን መከራ
የምቀበለውም በዚህ ምክንያት ነው ፤ ነገር ግን
አላፍርበትም ፤ ምክንያቱም ማንን እንዳመንሁ
ዐውቃለሁ ፤ የሰጠኝንም ዐደራ እስከዚያ ቀን
ድረስ መጠበቅ እንደሚችል ተረድቻለሁ ።
13 ከእኔ የተማርኸውን ንጹሕ ቃል እንደ ምሳሌ
አድርገህ በኢየሱስ ክርስቶስ ባለን ኅብረት ምክ
ንያት የሚገኘውን እምነትና ፍቅር አጥብቀህ
ያዝ ። 14 በእኛ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማ
ካይነት የተሰጠህን መልካም ዐደራ ጠብቅ ።
15 በእስያ ያሉት ሁሉ እንደከዱኝ ታውቃ
ለህ ፤ ከእነርሱም መካከል ፊጌሉስና ሄርሞገ
ኔስ ይገኛሉ ። 16 ጌታ ለኦኔሲፎሮ ቤተሰቦች
ምሕረትን ይስጥ ፤ ምክንያቱም እርሱ ብዙ

1፡2 ፦ ሐ.ሥ. 16፡1 ። 1፡5 ፦ ሐ.ሥ. 16፡1 ። 1፡11 ፦ 1ጢሞ. 2፡7 ።

ጊዜ አጽናንቶኛል ፤ በመታሰሬም አላፈረም ።
17እንዲያውም ወደ ሮም በመጣ ጊዜ በትጋት
ፈልጎ አገኘኝ ፤ 18በመጨረሻው ቀን ጌታ
ምሕረትን ይስጠው ፤ በኤፌሶን በነበርሁበት
ጊዜ ምን ያህል እንዳገለገለኝ አንተ ራስህ
ደኅና አድርገህ ታውቃለህ ።

## ምዕራፍ 2

### የክርስቶስ መልካም ወታደር በመሆን መከራ መቀበል

1እንግዲህ ልጄ ሆይ! በኢየሱስ ክርስቶስ
በሚገኘው ጸጋ በርታ ። 2በብዙ ምስክሮች ፊት
ከእኔ የተማርኸውን ትምህርት ሌሎችን ለማስተ
ማር ችሎታ ላላቸውና ለታመኑ ሰዎች አስተላ
ልፍ ።

3አንተም የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ወታ
ደር በመሆን መከራን በትዕግሥት ተቀበል ።
4በወታደርነት የሚያገለግል ሰው የጦር አዛዡን
ለማስደሰት ዝግጁ መሆን አለበት እንጂ ወታደ
ራዊ ባልሆነ ኑሮ አይጠመድም ። 5እንዲሁም
በሩጫ የሚወዳደር ሰው በደንቡ መሠረት ካል
ተወዳደረ የአሸናፊነት ሽልማት አያገኝም ።
6በሥራ የሚደክም ገበሬ ፥ ከሥራው ከሚገ
ኘው ፍሬ የመጀመሪያውን ማግኘት ይገባዋል ።
7ጌታ በሁሉ ነገር ማስተዋልን ስለሚሰጥህ እኔ
የምለውን ልብ ብለህ ተመልከት ።

8ከሞት የተነሣውንና የዳዊት ዘር የሆነውን
ኢየሱስ ክርስቶስን አስታውስ ፤ እኔ የማበሥረው
የምሥራች ቃል ይኸው ነው ። 9በዚህም የም
ሥራች ቃል ምክንያት እንደ ወንጀለኛ እስከ
መታሰር ደርሼ መከራ እቀበላለሁ ፤ የእግዚአብ
ሔር ቃል ግን አይታሰርም ። 10ስለዚህ እነር
ሱም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሚገኘ
ውን ደኅንነትና ዘላለማዊ ክብርን እንዲያገኙ ፥
እግዚአብሔር ለመረጣቸው ሰዎች ስል ሁሉን
ነገር እታገሣለሁ ። 11እንዲህ የሚለው ቃል
የተረጋገጠ ነው ፥

“ከእርሱ ጋር ከሞትን ፥
ከእርሱ ጋር በሕይወት እንኖራለን ።
12 በትዕግሥት ጸንተን ከተገኘን ፥
ከእርሱ ጋር እንነግሣለን ።
ከካድነው ፥ እርሱም ይክደናል ።
13 እኛ እምነታችንን ብንክድ ፥
እርሱ ግን ራሱን መካድ ስለማይችል
ታማኝ ሆኖ ይኖራል ።”

### ትጉህ ሠራተኛ

14ይህን ነገር አስገንዝባቸው ፤ በቃላት ምክ
ንያት እንዳይከራከሩም በእግዚአብሔር ፊት አስ
ጠንቅቃቸው ፤ ምክንያቱም ይህ የቃላት ክርክር
የሚሰሙትን ሰዎች ያጠፋል እንጂ ለምንም
አይጠቅምም ። 15እውነተኛውን የእግዚአብሔር
ቃል በትክክል በማስተማር በሥራው እንደማያ
ፍር ሠራተኛ ሆነህ ፥ ፈተናን ማለፍህ በእግዚአ
ብሔር ፊት የተረጋገጠ እንዲሆንልህ ትጋ ።
16ዓለማዊና ከንቱ ከሆነ ልፍለፋ ራቅ ፤ ምክንያ
ቱም እንዲህ ዐይነቱ ልፍለፋ ሰዎች ከእግዚአብ
ሔር እንዲርቁ ያደርጋቸዋል ፤ 17የእነርሱ ንግ
ግር እንደማይድን ቍስል ይቦረቡራል ፤ ከእነር
ሱም መካከል ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ይገኛሉ ።
18እነዚህ ሰዎች “የሙታን ትንሣኤ ገና ድሮ
ሆኖአል” እያሉ በመከራከር ከእውነት መንገድ
ወጥተዋል ፤ የአንዳንዶችንም ሰዎች እምነት
ያናውጣሉ ። 19ነገር ግን “ጌታ የራሱ የሆኑትን
ያውቃል ፤” እንዲሁም “የጌታን ስም የሚጠራ
ሁሉ ከክፋት ይራቅ” የሚል ማኅተም ያለበት
የማይነቃነቅ የእግዚአብሔር መሠረት ጸንቶ
ይኖራል ።

20በትልቅ ቤት ውስጥ ከወርቅና ከብር የተ
ሠሩ ዕቃዎች ብቻ ሳይሆኑ ከእንጨትና ከሸክላ
ዐፈር የተሠሩ ዕቃዎችም ይገኛሉ ፤ ከእነርሱም
አንዳንዶቹ ለተከበረ አገልግሎት ፥ አንዳንዶቹም
ለተዋረደ አገልግሎት ይውላሉ ። 21ከእነዚህ
ክፉ ነገሮች ተለይቶ ንጹሕ ሆኖ የሚኖር ሰው ፥
ለተከበረ አገልግሎት የሚውል ዕቃ ይሆናል ፤
ምክንያቱም ለማንኛውም መልካም አገልግሎት
የተዘጋጀ ፥ ለጌታው የተቀደሰና ጠቃሚ ዕቃ
ነው ።

22ከወጣቶች ክፉ ምኞት ሽሽ ፤ በንጹሕ
ልብ ጌታን ከሚጠሩ ሰዎች ጋር ሆነህ ጽድ
ቅን ፥ እምነትን ፥ ፍቅርን ፥ ሰላምን ተከታ
ተል ። 23 ጠብን እንደሚያመጣ ዐውቀህ ከሞኝነ
ትና ከከንቱ ክርክር ራቅ ። 24የጌታ ኢየሱስ አገ
ልጋይ የሆነ ሰው ፥ በሁሉም ዘንድ ገር ፥ የማስ
ተማር ችሎታ ያለውና ትዕግሥተኛ መሆን አለ
በት እንጂ መጣላት አይገባውም ፤ 25ምናልባት
እግዚአብሔር ንስሓ የመግባትና እውነትንም
የማወቅ ዕድል ስለሚሰጣቸው ፥ ተቃዋሚዎች
ንም በገርነት የሚያርም መሆን አለበት ፤
26በዚህ ዐይነት ወደ ልቡናቸው ተመልሰው ፥
ዲያብሎስ ፈቃዱን እንዲፈጽም እነርሱን ከያዘ
በት ወጥመድ ያመልጣሉ ።

## ምዕራፍ 3

### በመጨረሻ ቀኖች የሚሆኑ ክፉ ነገሮች

1በመጨረሻ ቀኖች የሚያስጨንቅ ጊዜ እን
ደሚመጣ ዕወቅ ፤ 2ሰዎች ራሳቸውን የሚወ
ድዱ ፥ ለገንዘብ የሚስገበገቡ ፥ ትምክሕተኞች ፥

2፡12 ፦ ማቴ. 10፡33 ፤ ሉቃ. 12፡9 ። 2፡19 ፦ ዘኍ. 16፡5 ።



ትዕቢተኞች ፥ ተሳዳቢዎች ፥ ለወላጆቻቸው የማ
ይታዘዙ ፥ ውለታቢሶች ፥ ሃይማኖተቢሶች ፥
3ፍቅር የሌላቸው ፥ ከሰዎች ጋር በምንም የማ
ይስማሙ ፥ የሰው ስም የሚያጠፉ ፥ ራሳቸውን
የማይቈጣጠሩ ፥ ጨካኞች ፥ መልካም የሆነውን
ነገር የሚጠሉ ፥ 4ከዳተኞች ፥ ጥንቃቄ የሌላ
ቸው ፥ በትዕቢት የተነፉ ፥ እግዚአብሔርን ከመ
ውደድ ይልቅ ሥጋዊ ደስታን የሚወድዱ ይሆ
ናሉ ። 5እንዲሁም ሃይማኖት ያላቸው ይመስ
ላሉ ፤ ነገር ግን የሃይማኖትን ኀይል ይክዳሉ ፤
ከእነዚህም ሰዎች ራቅ ። 6ምክንያቱም እነዚህ
ሰዎች በየቤቱ ሾልከው እየገቡ ብዙ ኃጢአት
የተከመረባቸውንና በልዩ ልዩ ፍትወት የሚ
መሩ ፥ መንፈስ ደካማ የሆኑ ሴቶችን እንደሚያ
ጠምዱት ሰዎች ናቸው ። 7እንዲህ ዐይነቶቹ
ሴቶች ሁል ጊዜ ይማራሉ ፤ ነገር ግን እውነትን
ወደ ማወቅ መድረስ አይችሉም ። 8ኢያኔስና
ኢያንበሬስ ሙሴን እንደተቃወሙት ፥ እነዚህ
ሰዎች አእምሮአቸው የተበላሸና በእምነትም
ነገር ውድቀት የደረሰባቸው ስለሆነ እውነትን
ይቃወማሉ ። 9የኢያኔስና የኢያንበሬስ ሞኝነት
እንደተገለጠ ፥ የእነዚህም ሰዎች ሞኝነት በሰው
ሁሉ ፊት ስለሚገለጥ አይሳካላቸውም ።

### የመጨረሻ ምክር

10አንተ ግን ትምህርቴን ፥ አኗኗሬን ፥ ዓላማ
ዬን ፥ እምነቴን ፥ ትዕግሥቴን ፥ ፍቅሬን ፥ ጽና
ቴን ተከትለሃል ፤ 11እንዲሁም የስደቴና የመከ
ራዬ ተካፋይ ሆነሃል ፤ በአንጾኪያና በኢቆንዮን
በልስጥራንም የደረሰብኝን ነገርና በትዕግሥት
የተቀበልሁትንም ስደት ታውቃለህ ፤ ጌታ ግን
ከሁሉም አዳነኝ ። 12የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታ
ዮች ሆነው በመንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚፈ
ልጉ ሁሉ ስደት ይገጥማቸዋል ። 13ነገር ግን
ክፉዎች ሰዎችና አስመሳዮች ፤ ሰዎችን እያሳሳ
ቱና ራሳቸውም እየተሳሳቱ በክፋት ላይ ክፋት
እየጨመሩ ይሄዳሉ ፤ 14አንተ ግን በተማርኸ
ውና በተረዳኸው እውነት ጽና ፤ ምክንያቱም
የተማርኸው ከማን እንደሆነ ታውቃለህ ፤ 15እን
ዲሁም ቅዱሳት መጻሕፍትን ከልጅነትህ ጀምሮ
ዐውቀሃል ፤ እነዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት በኢየ
ሱስ ክርስቶስ በሚገኘው እምነት ወደ ደኅንነት
ሊያደርስ የሚችል ጥበብ ያላቸው ናቸው ።
16ቅዱስ መጽሐፍ በሙሉ በእግዚአብሔር መን
ፈስ መሪነት የተጻፈ ነው ፤ እርሱ እውነትን
ለማስተማር ፥ የተሳሳቱትን ለመገሠጽ ፥ ስሕተ
ትን ለማረምና ለትክክለኛ ኑሮ የሚበጀውን
መመሪያ ለመስጠት ይጠቅማል ። 17የሚጠቅመ
ውም የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም እንዲሆንና
ማንኛውንም መልካም ሥራ ለመሥራት ብቁ
ሆኖ እንዲገኝ ነው ።

## ምዕራፍ 4

1በእግዚአብሔር ፊት ፥ እንዲሁም በሚገለጥ
በትና መንግሥቱን በሚያቋቁምበት ጊዜ በሕያ
ዋንና በሙታን ላይ በሚፈርደው በኢየሱስ ክር
ስቶስ ፊት ዐደራ እልሃለሁ ፤ 2ቃሉን ስበክ
ቢመችም ባይመችም በማንኛውም ጊዜ ተግተህ
ሥራ ፤ እያስረዳህ እየገሠጽህና እየመከርህ በትዕ
ግሥትና በማስተማር ጽና ። 3ምክንያቱም
ሰዎች ንጹሑን ቃል ለመስማት የማይፈልጉበት
ጊዜ ይመጣል ፤ ነገር ግን ለወሬ በመጐምጀት
እነርሱ ራሳቸው የሚወድዱትን ነገር የሚነግሩ
አቸውን አስተማሪዎች ይሰበስባሉ ። 4እውነትን
መስማት ትተው ተረትን መስማት ይወድዳሉ ።
5አንተ ግን በሁሉ ነገር ራስህን ተቈጣጠር ፤
መከራን በመቀበል ጽና ፤ የወንጌል ሰባኪነትን
ሥራ ፈጽም ፤ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደ
መሆንህ መጠን የሚገባህን ተግባር ሁሉ አድ
ርግ ።

6እኔ ግን መሥዋዕት ለመሆን ተቃርቤአ
ለሁ ፤ ከዚህ ዓለም ተለይቼ የምሄድበት ጊዜም
ደርሶአል ፤ 7ጦርነትን በመልካም ተዋግቻለሁ ፤
ሩጫን እስከ መጨረሻው ሮጫለሁ ፤ ሃይማኖትን
ጠብቄአለሁ ። 8ከእንግዲህ ወዲህ የጽድቅ አክ
ሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል ፤ ይህንንም አክ
ሊል ቅን ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያን ቀን ይሰ
ጠኛል ፤ ይህንንም ለእኔ ብቻ ሳይሆን የእርሱን
መገለጥ ለሚወድዱ ሁሉ ይሰጣቸዋል ።

### ስለ ግል ጉዳዮች

9በፍጥነት ወደ እኔ እንድትመጣ ይሁን ፤
10ዴማስ ይህን ዓለም ወዶ ተለይቶኛል ፤ ወደ
ተሰሎንቄም ሄዶአል ፤ ቄርቂስ ወደ ገላትያ ፥
ቲቶም ወደ ድልማጥያ ሄደዋል ። 11ከእኔ ጋር
ያለው ሉቃስ ብቻ ነው ፤ ማርቆስ ለአገልግሎት
ስለሚጠቅመኝ ከአንተ ጋር አብሮ ይምጣ ።
12ቲኪቆስን ወደ ኤፌሶን ልኬዋለሁ ። 13ስት
መጣ በጢሮአዳ በካርፑስ ዘንድ የተውሁትን
ካባ ይዘህልኝ ና ፤ መጻሕፍቱንም ይልቁንም
የብራና መጻሕፍቱን አምጣልኝ ።

14የናስ አንጥረኛው እስክንድር ብዙ ክፉ
ነገር አደረገብኝ ፤ ጌታ እንደ ሥራው ይከፍለ
ዋል ። 15እርሱ እኛ የምንናገረውን በብርቱ ስለ
ተቃወመ አንተም ራስህ ከእርሱ ተጠንቀቅ ።

3፡8 ፦ ዘጸ. 7፡11 ። 3፡11 ፦ ሐ.ሥ. 13፡14-52 ፤ 14፡1-7 ፣ 8-20 ። 4፡10 ፦ ቆላ. 4፡14 ፤ ፊልሞና 24 ፤ 2ቆሮ. 8፡23 ፤
ገላ. 2፡3 ፤ ቲቶ 1፡4 ። 4፡11 ፦ ቆላ. 4፡14 ፤ ፊልሞና 24 ፤ ሐ.ሥ. 12፡12 ፣ 25 ፤ 13፡13 ፤ 15፡37-39 ፤ ቆላ. 4፡10 ።
4፡12 ፦ ሐ.ሥ. 20፡4 ፤ ኤፌ. 6፡21-22 ፤ ቆላ. 4፡7-8 ። 4፡13 ፦ ሐ.ሥ. 20፡6 ። 4፡14 ፦ 1ጢሞ. 1፡20 ፤ መዝ. 62፡12 ፤
ሮም 2፡6 ።

¹⁶በተከሰስሁበት ነገር የመጀመሪያ መከላከ
ያዬን ባቀረብሁ ጊዜ ሁሉም ተለዩኝ እንጂ
ከእኔ ጋር ሆኖ የረዳኝ ማንም አልነበረም ፤ ይህ
ንንም ነገር እግዚአብሔር እንደ በደል አድርጎ
አይቍጠርባቸው ። ¹⁷ነገር ግን የምሥራቹ ቃል
በእኔ አማካይነት በሙሉ እንዲነገርና አረማውያ
ንም ሁሉ እንዲሰሙት ጌታ ከእኔ ጋር ሆኖ አበ
ረታኝ ፤ ከአንበሳም አፍ ድኛለሁ ። ¹⁸ጌታ ከማ
ንኛውም ክፉ ነገር ያድነኛል ፤ በሰማይ ላለው
መንግሥቱም ያበቃኛል ፤ ለእርሱ ለዘላለም
ክብር ይሁን ፤ አሜን ።

### የመጨረሻ ሰላምታ

¹⁹ለጵርስቅላና ለአቂላ ፥ ለአኔሲፎርም ቤተሰ
ዎች ሰላምታ አቅርብልኝ ። ²⁰ኤራስጦስ በቆሮ
ንቶስ ቀርቶአል ፤ ጥሮፊሞስ ስለታመመ በሚሊ
ጢን ትቼዋለሁ ። ²¹ክረምት ሳይደርስ ወደ እኔ
እንድትመጣ ይሁን ።

ኤውቡሉስ ፥ ጱዴስ ፥ ሊኖስ ፥ ቅላዲያና
አማኞችም ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡልሃል ።

²²ጌታ ከመንፈስህ ጋር ይሁን ።

ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን ።

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

# ወደ ቲቶ

## መግቢያ

ቲቶ ከአረማዊነት ወደ ክርስትና የተለወጠ ሲሆን ጳውሎስን በወንጌል ተልእኮው በቅርብ የሚረዳ የሥራ ተባባሪው ነበር ፤ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በዕድሜ አነስተኛ ለሆነው የሥራ ተባባሪው ለቲቶ ሲሆን ፥ ቲቶ በዚያን ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ሥራ በመቈጣጠር በቀርጤስ ይገኝ ነበር ። መልእክቱ የሚያተኵረው በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ነው ፦

አንደኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተለይ በቀርጤስ ሰዎች ጠባይ አንጻር ምን ዐይነት ጠባይ ሊኖራቸው እንደሚገባ ለቲቶ ማሳሰቢያ ተሰጥቶታል ፤ ሁለተኛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ቡድኖች ማለትም በዕድሜ የገፉ ወንዶችን ፥ በዕድሜ የገፉ ሴቶችን ፥ ወጣቶች ወንዶችንና አገልጋዮችን እንዴት ማስተማር እንደሚገባው ለቲቶ ምክር ተሰጥቶታል ፤ በመጨረሻም ስለ ክርስቲያናዊ ጠባይ በተለይም በሰላምና በወዳጅነት ስለመኖር ፥ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥላቻን ፥ ክርክርንና መለያየትን ስለማስወገድ ለቲቶ ምክርና መመሪያ ተሰጥቶታል ።

---

## ምዕራፍ 1

¹የእግዚአብሔር አገልጋይና የኢየሱስ ክርስ
ቶስ ሐዋርያ ከሆነው ፥ የእግዚአብሔርን ምር
ጦች በእምነት ለመርዳትና የሃይማኖትንም እው
ነት እንዲያውቁ ለማድረግ ከተሾመው ከጳው
ሎስ ፤

²ይህም ሃይማኖት በዘላለም ሕይወት ተስፋ
ላይ የተመሠረተ ነው ፤ የማይዋሸው አምላክ
ይህን ሕይወት ለመስጠት ከዘመናት በፊት ቃል
ገባልን ። ³ዘመኑም በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር
በቃሉ ገለጠው ፤ ይህ ቃል ለእኔ በዐደራ ስለ
ተሰጠኝ በአዳኛችን በእግዚአብሔር ትእዛዝ
መሠረት አበሥረዋለሁ ።

⁴የጋራችን በሆነው እምነት እውነተኛ ልጄ
ለሆነው ለቲቶ ፤

ከእግዚአብሔር አብና ከአዳኛችንም ከኢየ
ሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይሁን ።

### የቲቶ ሥራ በቀርጤስ

⁵አንተን በቀርጤስ የተውሁበት ምክንያት
የጐደለውን በማሟላት እንድታደራጅና ባዘዝሁ
ህም መሠረት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን
በየከተማው እንድትሾም ነው ። ⁶የቤተ ክርስቲ
ያን ሽማግሌ ፥ የማይነቀፍና የአንዲት ሚስት
ባል የሆነ ፥ ስድ በመሆንና ባለመታዘዝ ምክን
ያት የማይወቀሱ አማኞች ልጆች ያሉት ሰው
መሆን ይገባዋል ። ⁷ኤጲስ ቆጶስ የእግዚአብሔ
ርን ሥራ በዐደራ የተቀበለ ስለሆነ የማይነቀፍ
መሆን አለበት ፤ እንዲሁም የማይኰራ ፥
የማይቈጣ ፥ የማይሰክር ፥ የማይጨቃጨቅ ፥ ለገ
ንዘብ የማይስገበገብ መሆን አለበት ። ⁸ይልቅስ





እንግዳ ተቀባይ ፥ መልካም የሆነውን ነገር የሚ
ወድድ ፥ ራሱን የሚቈጣጠር ፥ ትክክለኛ ፥ መን
ፈሳዊና በመጠን የሚኖር ይሁን ። ⁹የታመነው
ንና ከእውነተኛው ትምህርት ጋር ተስማሚ የሆ
ነውን ቃል መያዝ አለበት ፤ በዚህ ዐይነት በን
ጹሕ ቃል ሌሎችን መምከርና ይህን ቃል የሚ
ቃወሙትን ሰዎች መገሠጽ ይችላል ።

¹⁰ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ፥ ይልቁንም ከአ
ይሁድ ወገን የሆኑቱ የማይታዘዙ ፥ በከንቱ የሚ
ለፈልፉና የሚያታልሉ አሉ ። ¹¹እነዚህን
ሰዎች ዝም ማሰኘት ይገባል ፤ ምክንያቱም እነ
ርሱ በሚያሳፍር ሁኔታ ለገንዘብ በመስገብገብ
የማይገባውን ነገር እያስተማሩ ቤተሰቦችን
በሙሉ ያናውጣሉ ። ¹²ከእነርሱ አንዱ የሆነው
የገዛ ራሳቸው ነቢይ “የቀርጤስ ሰዎች ሁልጊዜ
ውሸታሞች ፥ ጨካኞች ፥ አውሬዎች ፥ ሥራ
ፈቶችና ሆዳሞች ናቸው” ብሎአል ። ¹³ይህም
ምስክርነት እውነት ነው ፤ ስለዚህ በእምነት
ጤናማዎች እንዲሆኑ ፥ ¹⁴የአይሁዳውያንን
ተረት እንዳይከተሉና እውነትን የሚቃወሙትን
ሰዎች ምክር እንዳይሰሙ በብርቱ ገሥጻቸው ።
¹⁵ለንጹሖች ፥ ሁሉ ነገር ንጹሕ ነው ፤ ለርኩሶ
ችና ለማያምኑ ሰዎች ግን ንጹሕ የሆነ ምንም
ነገር የለም ፤ እንዲያውም አእምሮአቸውም ሆነ
ኅሊናቸው የረከሰ ነው ። ¹⁶“እግዚአብሔርን
እናውቃለን” ይላሉ ፤ በሥራቸው ግን ይክዱ
ታል ፤ ምክንያቱም እነርሱ አስጸያፊዎች ፥ የማ
ይታዘዙና ምንም መልካም ሥራ ማድረግ የማይ
ችሉ ናቸው ።

## ምዕራፍ 2

### ስለ ንጹሕ ትምህርት

¹አንተ ግን ከንጹሕ ትምህርት ጋር ተስ
ማሚ የሆነውን ቃል አስተምር ፤ ²በዕድሜ
የገፉ ወንዶች ፥ በመጠን የሚኖሩ ፥ ክብራቸ
ውን የሚጠብቁ ፥ ጠንቃቆች ፥ በእምነትና በፍ
ቅር በትዕግሥትም ጤናማዎች እንዲሆኑ ምከራ
ቸው ። ³እንዲሁም በዕድሜ የገፉ ሴቶች ሑም
ቶችና ክብራቸውን የሚጠብቁ ፥ የሰው ስም
የማያጠፉ ወይም የመጠጥ ተገዦዎች የማይሆኑ
እንዲሆኑ ምከራቸው ፤ ይልቅስ መልካም የሆነ
ውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ ። ⁴ወጣት ሴቶ
ችም ፥ ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን እንዲወዱ ፥
⁵ጠንቃቆችና ንጹሖች ፥ በቤት የሚሠሩ ፥
ደጎች ፥ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ያስ
ተምሩአቸው ። እንዲህ ካደረጉ የእግዚአብሔ
ርን ቃል የሚነቅፍ አይኖርም ።

⁶እንዲሁም ጐልማሶች ራሳቸውን በመቈጣ
ጠር እንዲኖሩ ምከራቸው ። ⁷አንተም መልካም
የሆነውን እያደረግህ በሁሉ ነገር ምሳሌ ሁንላ
ቸው ፤ በትምህርትም እውነተኛነትን ፥ ቁምነገ
ረኛነትን ፥ ⁸የማይነቀፍ ጤናማ ንግግርን ግለጥ
ላቸው ፤ በዚህ ዐይነት ተቃዋሚዎች በእኛ ላይ
የሚናገሩት ክፉ ነገር ሲያጡ ያፍራሉ ።

⁹አገልጋዮችም ለጌቶቻቸው እንዲታዘዙ ፥
በሁሉም ነገር እንዲያስደስቱአቸው ፥ ክፉ
ቃል እንዳይመልሱላቸው ፥ ¹⁰ገንዘባቸውንም
እንዳይሰርቁአቸው ምከራቸው ፤ ይልቅስ የአዳ
ኛችን የእግዚአብሔር ትምህርት በሁሉ ነገር
እንዲከበር ሁልጊዜ ፍጹም ታማኝነትን
ያሳዩ ።

¹¹እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ የሚያድንበ
ትን ጸጋውን ገልጦአል ፤ ¹²ይህም ጸጋ ኃጢአ
ተኛነትንና ሥጋዊ ምኞትን እንድንክድና
ራስን በመቈጣጠር ፥ በቅንነት ፥ በመንፈሳዊ
ነት በዚህ ዓለም እንድንኖር ያስተምረናል ።
¹³በዚህ ዐይነት የተባረከውን ተስፋችንን እን
ጠብቃለን ፤ ይህም የምንጠባበቀው ተስፋ የታ
ላቁ አምላካችን ፥ የአዳኛችን የኢየሱስ ክርስ
ቶስ የክብር መገለጥ ነው ። ¹⁴ክርስቶስ ከዐ
መፃ ሁሉ ሊያድነንና መልካም ሥራ ለመሥ
ራት ትጉሆችና ለእርሱ የተለየን ንጹሕ
ሕዝብ እንድንሆን ያነጻን ዘንድ ስለ እኛ
ራሱን አሳልፎ ሰጠ ።

¹⁵እንግዲህ እነዚህን ነገሮች አስተምር ፥
በሙሉ ሥልጣንም ምከር ፥ ገሥጽም ፤ ማንም
አይናቅህ ።

## ምዕራፍ 3

### ክርስቲያናዊ ተግባር

¹ሰዎች ሁሉ ፥ ለገዦዎችና ለባለሥልጣኖች
በትሕትና እንዲታዘዙ ፥ መልካም ሥራን ሁሉ
ለመሥራት ዝግጁዎች እንዲሆኑ ፥ ²በማንም
ላይ ክፉ ነገር እንዳይናገሩ አሳስባቸው ፤ ይል
ቅስ ከሰው ጋር የማይጣሉና ገሮች ፥ ፍጹም
ትሕትናን ለሰው ሁሉ የሚያሳዩ ይሁኑ ፤ ³ምክ
ንያቱም እኛም ከዚህ በፊት አስተዋይነት የጐደ
ለን ሞኞች ፥ የማንታዘዝ እምቢተኞች ፥ የምንሳ
ሳት ተላላዎች ፥ ለልዩ ልዩ ፍትወትና ሥጋዊ
ደስታ የተገዛን ፥ በተንኰልና በምቀኝነት የምን
ኖር ፥ የተጠላንና እርስ በርሳችንም የምንጣላ
ነበርን ። ⁴ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር
ደግነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ ፥ ⁵እኛ በሠራ
ነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን በምሕረቱ አዳነን ፤
ያዳነንም በአዲስ ልደት መታጠብና በመንፈስ
ቅዱስ አማካይነት በተገኘው መታደስ ነው ።
⁶እግዚአብሔር በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ
አማካይነት መንፈሱን በብዛት አፈሰሰልን ።

7 ይህንንም ያደረገው በእርሱ ጸጋ ጸድቀን በተ
ስፋ የምንጠባበቀውን የዘላለም ሕይወት እንድን
ወርስ ነው ። 8 ይህ የነገርሁህ ሁሉ የታመነ
ነው ።

በእግዚአብሔር ያመኑ ሰዎች ለመልካም
ሥራ እንዲተጉ ይህን የነገርሁህን ሁሉ በጥብቅ
እንድታስገነዝብ እፈልጋለሁ ፤ ይህም ነገር መል
ካምና ለሰው ጠቃሚ ነው ። 9 ነገር ግን ከከንቱ
ክርክር ፥ ከትውልዶች ቈጠራ ፥ ከጭቅጭቅ ፥
በሙሴ ሕግ ምክንያት ከሚነሣው ጠብ ራቅ ፤
ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ጥቅም የሌላቸውና
ዋጋቢሶች ናቸው ። 10 መለያየት የሚያመጣውን
ሰው አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ከመከርከው
በኋላ ከእርሱ ራቅ ። 11 እንዲህ ያለው ሰው የተ
በላሸና ኃጢአትን በመሥራት በራሱ ላይ የፈ
ረደ መሆኑን ዕወቅ ።

### የመጨረሻ ምክር

12 አርጤማስን ወይም ቲኪቆስን ወደ አንተ
በምልክበት ጊዜ ፥ አንተ ወደ ኒቆጵልዮን ወደ
እኔ ለመምጣት ትጋ ፤ ምክንያቱም እኔ ክረም
ቱን እዚያ ለማሳለፍ ወስኛለሁ ። 13 ሕግ ዐዋ
ቂው ዜማስና አጵሎስ ጕዞአቸውን እንዲጀ
ምሩ አድርጋቸው ፤ በሚያስፈልግም ነገር
ሁሉ ዕርዳቸው ። 14 የእኛም ሰዎች ደግሞ
ያለ ፍሬ እንዳይቀሩና የኑሮን ችግር ማቃለል
እንዲችሉ ፥ መልካም ሥራን መሥራት
ይማሩ ።

15 ከእኔ ጋር ያሉት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡል
ሃል ፤ በእምነት ምክንያት ለሚወድዱን ሰላምታ
አቅርብልን ።

ጸጋ ከሁላችሁም ጋር ይሁን ።

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

# ወደ ፊልሞና

## መግቢያ

ፊልሞና ታዋቂ ክርስቲያን ሲሆን ፥ የቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን አባል እንደሆነ ይገመታል ፤ ፊልሞና አናሲሞስ የሚባል አገልጋይ ነበረው ፤ ይህም አገልጋይ ከጌታው ኰብልሎ በሄደበት ጊዜ በእስር ቤት ከነበረው ከጳውሎስ ጋር ተገናኘ ፤ በጳውሎስም አማካይነት አናሲሞስ የክርስትናን እምነት ተቀበለ ፤ ጳውሎስ ወደ ፊልሞና የጻፈው መልእክት ፊልሞና ተመልሶ ወደ እርሱ በመምጣት ላይ ካለው አገልጋዩ ጋር እንዲታረቅ የሚያሳስብ ነበር ፤ በተጨማሪም አሁን አናሲሞስ ክርስቲያን ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲህ እንደ ክርስቲያን ወንድም እንዲቀበለው እንጂ እንደ ባሪያ እንዳይቈጥረው ይነግረዋል ።

---

1 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ከሆነው ከጳ
ውሎስና ከወንድማችን ከጢሞቴዎስ ፥
ለተወደደው ወንድማችንና የሥራ ተባባሪያ
ችን ለሆነው ለፊልሞና ፥ 2 በቤቱም ለሚሰበሰቡ
ምእመናን ፥ ለእኅታችን ለአፍብያ ፥ እንዲሁም
ከእኛ ጋር የክርስቶስ ወታደር ለሆነው ለአ
ርኪፖስ ፥
3 ከአባታችን ከእግዚአብሐር ፥ ከጌታችንም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ።

### የፊልሞና ፍቅርና እምነት

4 በጸሎቴ አንተን እያሰብሁ ሁል ጊዜ አምላ
ኬን አመሰግናለሁ ፤ 5 ምክንያቱም ቅዱሳንን እን
ደምትወድና በጌታ በኢየሱስ እንደምታምን
ሰምቻለሁ ፤ 6 የክርስቶስ በመሆናችን ያለን መል
ካም ነገር ሁሉ በይፋ ይታወቅ ዘንድ እምነት
ህን ለሌሎች በማካፈል እንድትተጋ እጸልያ
ለሁ ። 7 ወንድሜ ሆይ! በአንተ ምክንያት የክር
ስቲያኖች ልብ ስለታደሰ ፤ ፍቅርህ ታላቅ ደስ
ታና መጽናናት ሰጥቶኛል ።

### የአናሲሞስ ወደ ፊልሞና መመለስ

8 ስለዚህ ሁላችንም የክርስቶስ በመሆናችን
አንተ ማድረግ የሚገባህን እንድታደርግ ለማዘዝ
ድፍረት በኖረኝ ነበር ፤ 9 ነገር ግን በማዘዝ ፈንታ
በፍቅር እለምንሃለሁ ፤ ምክንያቱም እኔ የኢየሱስ
ክርስቶስ አምባሳደርና አሁንም ስለ እርሱ እስ
ረኛ የሆንሁ ጳውሎስ ነኝ ፤ 10 የምለምንህም በእ
ስር ቤት ሳለሁ በመንፈስ ስለወለድሁት ልጄ ስለ
አናሲሞስ ጉዳይ ነው ፤ 11 አናሲሞስ ከዚህ በፊት

---

3፥12 ፦ ሐ.ሥ. 20፥4 ፤ ኤፌ. 6፥21-22 ፤ ቆላ. 4፥7-8 ፤ 2ጢሞ. 4፥12 ። 3፥13 ፦ ሐ.ሥ. 18፥24 ፤ 1ቆሮ. 16፥12 ።
2 ፦ ቆላ. 4፥17 ። 10 ፦ ቆላ. 4፥9 ።



አይጠቅምህም ነበር ፤ አሁን ግን ለአንተም ሆነ
ለእኔ ጠቃሚ ነው ።
12 እነሆ እርሱን ወደ አንተ መልሼ ልኬዋ
ለሁ ፤ እርሱን ወደ አንተ ስልከውም የገዛ ራሴን
ልብ እንደላክሁ አድርጌ እቈጥረዋለሁ ። 13 በወ
ንጌል ምክንያት እዚህ ታስሬ ሳለሁ ፥ በአንተ
ምትክ ሆኖ እንዲያገለግለኝ እርሱ ከእኔ ጋር
ቢሆን ደስ ባለኝ ነበር ፤ 14 ነገር ግን የአንተ
መልካም ሥራ በግዴታ ሳይሆን በውዴታ እንዲ
ሆን ብዬ ፥ አንተን ሳላስፈቅድ ምንም ማድረግ
አልፈለግሁም ።
15 አናሲሞስ እስከ አሁን ለጥቂት ጊዜ የተለ
የህ ፥ ምናልባት ከእንግዲህ ወዲህ ሁል ጊዜ ከአ
ንተ ጋር እንዲኖር ይሆናል ። 16 ከእንግዲህ
ወዲህ ከአንተ ጋር የሚኖረውም እንደ ባሪያ
ሳይሆን ከባሪያ የበለጠ ሆኖ እንደ ተወዳጅ ወን
ድም ነው ፤ እርሱ ለእኔ ተወዳጅ ወንድም
ነው ፤ ይሁን እንጂ እርሱ በአገልግሎቱም ስለ
ሚጠቅምህና በክርስቶስ ወንድምህ ስለሆነ ለአ
ንተ ይበልጥ ተወዳጅ ነው ።
17 በጋራ እምነታችን ምክንያት እንደ ወን
ድም አድርገህ ከቈጠርኸኝ ፥ ልክ እንደ እኔ አድ
ርገህ ተቀበለው ። 18 ያደረሰብህ በደል ቢኖር
ወይም ዕዳ ቢኖርበት ፥ ዕዳውን በእኔ ላይ አድር
ገው ። 19 እነሆ እኔ ጳውሎስ “ዕዳውን እከፍልሃ
ለሁ” ብዬ በገዛ እጄ ፈርሜአለሁ ፤ ሆኖም በክርስ
ቶስ ያመንኸው በእኔ አማካይነት ስለሆነ አንተ
ራስህ እንኳ የእኔ ባለዕዳ መሆንህን እኔ ላስታው
ስህ አያስፈልግም ። 20 እንግዲህ ወንድሜ ሆይ!
ይህን መልካም ነገር እንድታደርግልኝ በጌታ እለ
ምንሃለሁ ፤ እባክህ ልቤን በክርስቶስ አድስልኝ ።
21 ይህን የጻፍሁልህ እንደምትታዘዘኝ በመተ
ማመን ነው ፤ እንዲያውም እኔ ከምጠይቅህ
በላይ እንደምታደርግ ዐውቃለሁ ። 22 እግዚአብ
ሔር ጸሎታችሁን ሰምቶ ወደ እናንተ እንድ
መጣ እንደሚያደርገኝ ተስፋ ስላለኝ ፥ የማርፍ
በት ቤት አዘጋጅልኝ ።

### የመጨረሻ ሰላምታ

23 በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት ከእኔ ጋር
የታሰረው ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብልሃል ፤
24 እንዲሁም የሥራ ተባባሪዎቼ የሆኑት ማር
ቆስ ፥ አርስጥሮኮስ ፥ ዴማስ ፥ ሉቃስ ሰላምታ
ያቀርቡልሃል ።
25 የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ
ጋር ይሁን ።

# ወደ ዕብራውያን

# የተላከ መልእክት

## መግቢያ

ይህ መልእክት የተጻፈው ከባድ ተቃውሞ ስለደረሰባቸው እምነታቸውን ሊተው ወደተቃረቡ ክርስቲያኖች ነበር ፤ ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስ ፥ እግዚአብሔር በማያዳግም ሁኔታ ራሱን በእውነተኛ መንገድ የገለጠበት እንደሆነ በማሳየት ፥ እነዚህ ክርስቲያኖች በእምነታቸው እንዲጸኑ ያበረታታቸዋል ፤ ይህንንም በሚያደርግበት ጊዜ ሦስት እውነቶችን አጕልቶ ያሳያል ፦

1. በተቀበለው መከራ አማካይነት ለአብ እውነተኛ ታዛዥ የሆነው ኢየሱስ ዘላለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ፤ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑም ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ፥ ከመላእክትና ከራሱ ከሙሴም እንኳ እጅግ የላቀ ነው ።
2. ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን ካህናት እጅግ የላቀ ዘላለማዊ ካህን መሆኑን እግዚአብሔር ራሱ አውቆአል ።
3. በኢየሱስ በኩል አማኙ ከኃጢአት ፥ ከፍርሃትና ከሞት ይድናል ፤ ኢየሱስ ሊቀ ካህን እንደ መሆኑ መጠን በዕብራውያን ሃይማኖት ሥርዓቶችና የእንስሳት መሥዋዕት እንደ ጥላ ይታይ የነበረው ድኅነት እውነተኛ እንዲሆን አድርጎታል ።

ጸሐፊው በእስራኤል ታሪክ ዝነኞች የሆኑ ሰዎችን እምነት እንደ ምሳሌ በመጠቀም (ም. 11) አንባቢዎቹ በእምነታቸው እንዲጸኑ ያሳስባቸዋል ፤ እንዲሁም በም. 12 አንባቢዎቹ ዐይኖቻቸውን በኢየሱስ ላይ በማተኰር በእምነታቸው እንዲጸኑና ማንኛውም ዐይነት መከራና ሥቃይ ቢደርስባቸው እንዲታገሡ ይመክራቸዋል ፤ በመጨረሻም የምክርና የማስጠንቀቂያ ቃል በመስጠት ይደመድማል ።

---

23 ፦ ቆላ. 1፥7 ፤ 4፥12 ። 24 ፦ ሐ.ሥ. 12፥12 ፣25 ፤ 13፥13 ፤ 15፥37-39 ፤ 19፥29 ፤ 27፥2 ፤ ቆላ. 4፥10 ፣14 ፤
2ጢሞ. 4፥10 ፣11 ።

## ምዕራፍ 1

### እግዚአብሔር በልጁ አማካይነት እንደ ተናገረ

1 እግዚአብሔር በቀድሞ ዘመናት በተለያየ
መንገድ፥ በነቢያት አማካይነት ለአባቶቻችን
ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር፤ 2 አሁን ግን በእነዚህ
በመጨረሻ ቀኖች ሁሉን ነገር ወራሽ ባደረገው
በልጁ አማካይነት ለእኛ ተናገረን፤ ዓለምንም
ሁሉ የፈጠረው በእርሱ ነው። 3 እርሱ የእግዚአ
ብሔር ክብር ነጸብራቅ ነው፤ እርሱ በባሕርዩ
ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ትክክል ነው።
ሥልጣን ባለው ቃሉ ዓለምን ሁሉ ደግፎ ይዞ
አል፤ ሰዎችንም ከኃጢአት ካነጻ በኋላ በሰ
ማይ፥ በኀያሉ እግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ
አል።

### የእግዚአብሔር ልጅ ከመላእክት በላይ ነው

4 ለእርሱ የተሰጠው ስም ከመላእክት ስም
በላይ እንደ መሆኑ መጠን የእግዚአብሔር ልጅ
ከመላእክት በላይ ነው። 5 ምክንያቱም እግዚአ
ብሔር ከመላእክት መካከል፥
"አንተ ልጄ ነህ፥ ዛሬ ወልጄሃለሁ"
ወይም፥
"እኔ አባት እሆነዋለሁ፤ እርሱም ልጄ
ይሆናል"
ያለው አንድም የለም።
6 እግዚአብሔር የበኵር ልጁን ልኮ ወደ ዓለም
ሲያስገባ፥
"የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ
ይስገዱለት" ይላል።
7 ስለ መላእክቱ ግን፥
"መላእክቱን ነፋስ፥
አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል
ያደርጋል" ይላል።
8 ስለ ልጁ ግን፥
"አምላክ ሆይ! ዙፋንህ ለዘላለም
ይኖራል፤
መንግሥትህን በጽድቅ
ታስተዳድራለህ፤
9 ጽድቅን ወደድህ፥ ዐመፃንም ጠላህ፤
በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር
አምላክህ መረጠህ፤
ከጓደኞችህም ይበልጥ ደስታን እንደ
ዘይት አፈሰሰልህ" ይላል።
10 እንዲሁም፥
"ጌታ ሆይ! አንተ በመጀመሪያ ምድርን
ፈጠርህ፤
ሰማይም የእጅህ ሥራ ነው፤
11 እነርሱ ሁሉ ይጠፋሉ፤
አንተ ግን ትኖራለህ፤
እነርሱ እንደ ልብስ ያረጃሉ።
12 እንደ መጐናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ፤
እንደ ልብስም ይለወጣሉ።
አንተ ግን ሁልጊዜ ያው ነህ፤
ከቶም አታረጅም" ይላል።
13 እግዚአብሔር ከመላእክቱ መካከል፥
"ጠላቶችህን ከሥልጣንህ ሥር
እስካደርግልህ ድረስ፥
በቀኜ ተቀመጥ" ያለው አንድም
የለም።
14 ታዲያ፥ መላእክት የሚድኑትን ለማገል
ገል የሚላኩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑ
መንፈሶች አይደሉምን?

## ምዕራፍ 2

### የደኅንነት ትልቅነት

1 ስለዚህ ከሰማነው ነገር ተንሸራተን እንዳን
ወድቅ፥ ስለ ሰማነው ነገር በጣም መጠንቀቅ
አለብን። 2 በመላእክት አማካይነት የተነገረው
ቃል እርግጠኛ ሆኖአል፤ ይህንንም ቃል የሚተ
ላለፍና ለዚህም ቃል የማይታዘዝ ተገቢውን
ቅጣት ይቀበላል፤ 3 ታዲያ እኛ ይህን ታላቅ
ደኅንነት ችላ የምንል ከሆንን እንዴት እናመል
ጣለን? ይህን ደኅንነት በመጀመሪያ ያበሠረው
ጌታ ራሱ ነው፤ የሰሙትም ሰዎች ይህንኑ አረ
ጋግጠውልናል። 4 እግዚአብሔር ምልክቶችን፥
ድንቅ ነገሮችን፥ ልዩ ልዩ ተአምራትን በማድረ
ግና እንደ ፈቃዱ በታደሉት የመንፈስ ቅዱስ
ስጦታዎች አማካይነት ምስክርነታቸውን አጽን
ቶአል።

### የደኅንነት መሪ

5 እግዚአብሔር ወደ ፊት የሚመጣውን፥
ይህን የምንነጋገርበትን ዓለም ለመላእክት አላስ
ገዛም እኮ። 6 እንዲያውም በቅዱሳት መጻሕፍት
በአንድ ስፍራ እንዲህ ተብሎአል፥
"አንተ እርሱን ታስበው ዘንድ ሰው
ምንድን ነው?
ለእርሱስ ትጠነቀቅለት ዘንድ የሰው
ልጅ ምንድን ነው?
7 ለጥቂት ጊዜ ከመላእክት አሳነስኸው፤
የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንህለት፥
[በእጆችህም ሥራ ላይ ሾምኸው፤]
8 ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር
አደረግህለት።"
ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር ሲያደርግ፤ በሥል
ጣኑ ሥር ሳያደርግለት ያስቀረው ምንም ነገር



የለም። ነገር ግን አሁን ሁሉ ነገር በእርሱ
ሥልጣን ሥር እንደሆነ ገና አላየንም። 9 አሁን
ግን ከመላእክት ለጥቂት ጊዜ ዝቅ ብሎ የነበረ
ውን፥ የሞትን መከራ በመቀበሉ ምክንያት የክ
ብርና የምስጋና ዘውድ የጫነውን ኢየሱስን እና
ያለን፤ እርሱ በእግዚአብሔር ጸጋ ስለሁላችን
ሞቶአል። 10 ሁሉ ነገር ለእግዚአብሔርና በእግ
ዚአብሔር የተፈጠረ ነው፤ ብዙ ልጆችን ወደ
ክብር ለማምጣት ብሎ ወደ ደኅንነት የሚመራ
ቸውን ኢየሱስን በመከራ ፍጹም ሊያደርገው
ተገባው።
11 ሰዎችን ቅዱሳን የሚያደርጋቸውና በእ
ርሱ ቅዱሳን የሆኑትም ሰዎች የአንድ አባት
ልጆች ናቸው፤ በዚህ ምክንያት ኢየሱስ እነር
ሱን "ወንድሞቼ" ብሎ ለመጥራት አያፍርም።
12 ስለዚህም በቅዱሳት መጻሕፍት
"ስምህን ለወንድሞቼ አበሥራለሁ፥
በማኅበርም መካከል በዜማ
አመሰግንሃለሁ" ይላል፤
13 እንዲሁም "እምነቴን በእርሱ ላይ እጥላ
ለሁ" ይላል፤
እንዲሁም "እነሆኝ እኔና እግዚአብሔር የሰ
ጠኝ ልጆች" ይላል።
14 ስለዚህ ልጆች ሥጋና ደም ያላቸው
ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን፥ ኢየሱስም
እንደ እነርሱ ሰው ሆነ፤ ይህን ያደረገውም
በሞቱ አማካይነት በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን
ዲያብሎስን ለመሻር ነው። 15 እንዲሁም ሞትን
በመፍራት ምክንያት ዕድሜ ልካቸውን በባር
ነት ይገዙ የነበሩትን ለመዋጀት ነው። 16 ምክ
ንያቱም የኢየሱስ ፍላጎት መላእክትን ለመር
ዳት ሳይሆን፥ የአብርሃምን ዘር ለመርዳት አስቦ
ነው፤ 17 ስለዚህ በሁሉ ነገር ወንድሞቹን መም
ሰል ተገባው፤ በዚህ ዐይነት የሰዎችን ኃጢአት
ለመደምሰስ ብሎ እግዚአብሔርን ለማገልገል
ታማኝና መሐሪ ሊቀ ካህናት ሆነ። 18 እርሱ
ራሱ በተፈተነ ጊዜ መከራን ስለተቀበለ፥ የሚፈ
ተኑትን መርዳት ይችላል።

## ምዕራፍ 3

### ኢየሱስ ከሙሴ በላይ ነው

1 የእግዚአብሔርን ጥሪ የተቀበላችሁ ቅዱሳን
ወንድሞቼ ሆይ! የእምነታችን ሐዋርያና ሊቀ
ካህናት የሆነውን ኢየሱስን አስቡ። 2 ሙሴ በእ
ግዚአብሔር ቤት ሁሉ ታማኝ እንደነበረ፥ ኢየ
ሱስም ለሾመው ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበር።
3 ቤትን የሚሠራ ከቤቱ ይልቅ የበለጠ ክብር
እንዳለው ሁሉ፥ ኢየሱስም ከሙሴ ይልቅ የበ
ለጠ ክብር የተገባው ሆኖ ተገኝቶአል። 4 በእር
ግጥ ቤት ሁሉ ሠሪ አለው፤ ሁሉን ነገር የሠራ
ግን እግዚአብሔር ነው። 5 ወደፊት መባል ለሚ
ገባው ነገር ምስክር እንዲሆን ሙሴ በእግዚአብ
ሔር ቤት ሁሉ እንደ አገልጋይ ሆኖ ታማኝ
ነበር። 6 ክርስቶስ ግን በእግዚአብሔር ቤት
ታማኝ የሆነው እንደ ልጅ ሆኖ ነው፤ ቤቱም
እኛ ነን፤ ቤቱ የምንሆነውም የምንተማመንበ
ትን ነገርና የምንመካበትን ተስፋ አጽንተን ብን
ይዝ ነው።

### የእግዚአብሔር ሕዝብ ዕረፍት ያገኛል

7 ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚለው፥
"ዛሬ ድምፁን ስትሰሙ፥
8 በበረሓ በተፈታተናችሁኝ ጊዜ
እንዳመፃችሁት ዐይነት
ልባችሁን እልኸኛ አታድርጉ፤
9 እዚያ አባቶቻችሁ ተፈታተኑኝ፥
ተገዳደሩኝም፤
አርባ ዓመት ያደረግሁትንም አዩ"
ይላል እግዚአብሔር።
10 "ስለዚህ ያንን ትውልድ ተቈጥቼ፥
'ልባቸው ዘወትር ይሳሳታል፤
መንገዴንም አላወቁም' አልሁ።"
11 ደግሞም፥
"'እኔ ወደምሰጣቸው የዕረፍት ቦታ ከቶ
አይገቡም' ብዬ
በቍጣዬ ምያለሁ።"
12 ወንድሞቼ ሆይ! ከእናንተ ማንም ከሕያው
እግዚአብሔር የሚያርቅ ክፉና የማያምን ልብ
እንዳይኖረው ተጠንቀቁ። 13 ይልቅስ ከእናንተ
በኃጢአት ተታሎ እልኸኛ እንዳይሆን "ዛሬ"
የተባለው ጊዜ እስካለ ድረስ በየቀኑ በመመካከር
ተረዳዱ። 14 ምክንያቱም በመጀመሪያ የነበረንን
የእምነት ሁኔታ እስከ መጨረሻ አጽንተን ከያ
ዝን፥ ከክርስቶስ ጋር ወራሾች እንሆናለን።
15 ይህም "ዛሬ ድምፁን ስትሰሙ፥
በዚያ እንዳመፃችሁት ዐይነት
ልባችሁን እልኸኛ አታድርጉ"
ተብሎ እንደተነገረው ነው።
16 ለመሆኑ እነዚያ ድምፁን ሰምተው
ያመፁ እነማን ነበሩ? እነርሱ ሙሴ እየመራ
ቸው ከግብጽ የወጡት ሁሉ አልነበሩምን?
17 እግዚአብሔርን አርባ ዓመት ሙሉ ሲያስቈ
ጡት የኖሩ እነማን ነበሩ? እነዚያ ኃጢአት
የሠሩና ሬሳቸው በበረሓ ወድቆ የቀረው አይደ
ሉምን? 18 ደግሞስ እነዚያን ያልታዘዙትን ካል
ሆነ በቀር "ወደ ዕረፍቴ አትገቡም" ብሎ የማ
ለባቸው እነማን ነበሩ? 19 እንግዲህ ሊገቡ ያል
ቻሉት ባለማመናቸው ምክንያት መሆኑን እናያ
ለን።

1፡5 ፦ መዝ. 2፡7፤ 2ሳሙ. 7፡14፤ 1ዜ.መ. 17፡13። 1፡6 ፦ ዘዳ. 32፡43። 1፡7 ፦ መዝ. 104፡4።
1፡8-9 ፦ መዝ. 45፡6-7። 1፡10-12 ፦ መዝ. 102፡25-27። 1፡13 ፦ መዝ. 110፡1። 2፡6-8 ፦ መዝ. 8፡4-6።

2፡12 ፦ መዝ. 22፡22። 2፡13 ፦ ኢሳ. 8፡17-18። 3፡2 ፦ ዘኍ. 12፡7። 3፡7-11 ፦ መዝ. 95፡7-11።
3፡15 ፦ መዝ. 95፡7-8። 3፡16-18 ፦ ዘኍ. 14፡1-35።

## ምዕራፍ 4

1 ስለዚህ እርሱ ወደሚሰጠን የዕረፍት ቦታ
ለመግባት የተቀበልነው ተስፋ ገና የጸና ስለ
ሆነ፥ ከእናንተ ማንም ወደዚህ የዕረፍት ቦታ
የመግባት ዕድል ሳያገኝ እንዳይቀር ሁላችንም
በመፍራት እንጠንቀቅ። 2 ምክንያቱም መልካ
ሙን ዜና እነርሱ እንደሰሙት እኛም ሰምተነ
ዋል፤ ነገር ግን እነርሱ የሰሙትን ቃል በእም
ነት ስላልተቀበሉት አልጠቀማቸውም። 3 እግዚ
አብሔር

"እኔ ወደምሰጣቸው የዕረፍት ቦታ ከቶ
አይገቡም ብዬ
በቍጣዬ ምያለሁ" እንዳለው፥

እኛ ያመንን ወደዚያ እግዚአብሔር ወደሚሰ
ጠን ወደ ዕረፍት ቦታ እንገባለን፤ እንግዲህ የእ
ግዚአብሔር ሥራ ዓለም ከመፈጠሩ ጀምሮ
ተጠናቆአል ማለት ነው፤ 4 ምክንያቱም ስለ ሰባ
ተኛው ቀን በአንድ ስፍራ "እግዚአብሔር
ከሥራ ሁሉ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ" ተብሎ
ተጽፎአል። 5 እንዲሁም በዚሁ ስፍራ ላይ እን
ደገና

"እኔ ወደምሰጣቸው የዕረፍት ቦታ ከቶ
አይገቡም" ይላል።

6 እነዚያ መልካሙን ዜና በመጀመሪያ የሰሙት
ባለመታዘዛቸው ምክንያት እግዚአብሔር ወደ
ሚሰጣቸው የዕረፍት ቦታ አልገቡም፤ ሆኖም
ወደዚያ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው አንዳንዶች
ነበሩ። 7 ይህም አስቀድሜ እንደጠቀስሁት፥

"ዛሬ ድምፁን ስትሰሙ፥
ልባችሁን እልኸኛ አታድርጉ"

ሲል፥ እግዚአብሔር ከብዙ ዘመን በኋላ በዳ
ዊት አማካይነት በተናገረው ቃል "ዛሬ"
ተብሎ የተጠራውን ቀን በመወሰኑ ተረጋግጦ
አል።

8 ኢያሱ የእግዚአብሔርን የዕረፍት ቦታ ሰጥ
ቶአቸው ቢሆንማ ኖሮ፥ እግዚአብሔር እንደገና
"ዛሬ" በማለት ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር።
9 እንግዲህ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሰንበትን ዕረ
ፍት የመሰለ ዕረፍት ገና ይቀረዋል፤ 10 ምክንያ
ቱም እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፥ እንዲ
ሁም እግዚአብሔር ወደሚሰጠው የዕረፍት ቦታ
የሚገባ ከሥራው ያርፋል። 11 ስለዚህ ማንም
የእነዚያን ሰዎች አለመታዘዝ ተከትሎ እንዳይወ
ድቅ፥ ወደ እግዚአብሔር የዕረፍት ቦታ ለመግ
ባት እንትጋ።

12 የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ
ነው፤ ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ ስለታም
ነው፤ ነፍስንና መንፈስን፥ ጅማትንና ቅልጥ
ምን እስኪለያይ ድረስ የሚቈራርጥ ነው፤
በልብ ውስጥ የተሰወረውንም አሳብና ምኞት
መርምሮ የሚፈርድ ነው። 13 ከእግዚአብሔር
ፊት የሚሰወር ምንም ፍጥረት የለም፤ በእርሱ
ዐይን ፊት፥ ሁሉ ነገር ግልጥና ዕርቃኑን ሆኖ
የሚታይ ነው፤ እኛም መልስ መስጠት የሚገ
ባን በእርሱ ፊት ነው።

### ኢየሱስ ታላቅ ሊቀ ካህናት ነው

14 እንግዲህ ወደ ሰማይ የወጣ ታላቅ ሊቀ
ካህናት ስላለን እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ፤
እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ነው።
15 ምክንያቱም እኛ ያለን ሊቀ ካህናት፥ በድካ
ማችን ሊራራልን የሚችል ነው፤ እርሱ በሁሉ
ነገር እንደ እኛ ተፈተነ፤ ሆኖም፥ ምንም
ኃጢአት አልሠራም። 16 እንግዲህ ምሕረት እን
ድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን
ጸጋ እንድናገኝ፥ ጸጋ ወደሚገኝበት ወደ እግዚ
አብሔር ዙፋን በመተማመን እንቅረብ።

## ምዕራፍ 5

1 እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት ከሰዎች መካከል
ተመርጦ የኃጢአትን ስርየት የሚያስገኝ መባ
ንና መሥዋዕትን ለማቅረብ እግዚአብሔርን
በሚመለከት ነገር ስለ ሰዎች ተወክሎ ይሾ
ማል። 2 እርሱ ራሱ በደካማነት የተያዘ ስለሆነ
ደንቆሮዎችንና ስሕተተኞችን በርኅራኄ ሊመለ
ከታቸው ይችላል። 3 እርሱ ራሱም በደካማነት
የተያዘ ስለሆነ የኃጢአት ይቅርታን የሚያስገኝ
መሥዋዕትን ማቅረብ የሚገባው ለሕዝቡ ብቻ
ሳይሆን ለራሱም ጭምር ነው። 4 እንደ አሮን
ከእግዚአብሔር የተጠራ ካልሆነ በቀር ማንም
ይህን ክብር በገዛ ራሱ አይወስድም።

5 እንዲሁም ክርስቶስ ሊቀ ካህናት የመሆንን
ክብር በገዛ ራሱ አልወሰደም፤ ነገር ግን እርሱ
ሊቀ ካህናት የመሆንን ክብር ያገኘው፥

"አንተ ልጄ ነህ፥
እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ" ካለው
ከእግዚአብሔር ነው።

6 በሌላም ስፍራ እግዚአብሔር፥

"እንደ መልከ ጼዴቅ የክህነት ሹመት
አንተ ለዘላለም ካህን ነህ" ይላል።

7 ኢየሱስ ሰው ሆኖ በዚህ ምድር በኖረበት
ጊዜ ከሞት ሊያድነው ወደሚችል አምላክ በታ
ላቅ ጩኸትና በብዙ እንባ ጸሎትንና ልመናን
አቀረበ፤ በትሕትና በመታዘዙም እግዚአብሔር
ጸሎቱን ሰማው። 8 ምንም እንኳ የእግዚአብ
ሔር ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘ
ዝን ተማረ። 9 ፍጹም ሆኖ ከተገኘም በኋላ



ለሚታዘዙት ሁሉ የዘላለም ደኅንነት ምክንያት
ሆነላቸው። 10 እግዚአብሔርም በመልከ ጼዴቅ
የክህነት ሹመት ሊቀ ካህናት አድርጎ ሾመው።

### ሰዎች እንዳይሳሳቱ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

11 ስለዚህ ጉዳይ የምንናገረው ብዙ ነገር
አለ፤ ነገር ግን የማስተዋል ችሎታችሁ አነስ
ተኛ ስለሆነ ለማስረዳት አስቸጋሪ ነው።
12 እስከ አሁን በነበረው ጊዜ እናንተ አስተማሪ
ዎች መሆን በተገባችሁ ነበር፤ ነገር ግን የእግ
ዚአብሔርን ቃል የመጀመሪያ ትምህርት ሌላ
ሰው እንደገና እንዲያስተምራችሁ ያስፈልጋል፤
የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ
ምግብ አይደለም። 13 ምክንያቱም ወተት የሚ
ጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ የጽድቅን ትምህርት
አልተለማመደም። 14 ጠንካራ ምግብ የሚያስፈ
ልጋቸው ግን መልካሙንና ክፉውን የመለየት
ልምድ ያላቸው ትላልቅ ሰዎች ናቸው።

## ምዕራፍ 6

1 እንግዲህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀ
መሪያ ትምህርት ትተን፥ ፍጹም ወደሆነው
ትምህርት እንለፍ፤ ከሞተ ሥራ ንስሓ የመግባ
ትንና በእግዚአብሔር የማመንን መሠረት እንደ
ገና አንመሥርት፤ 2 እንዲሁም የጥምቀትን፥
የእጅ መጫንን፥ ከሞት የመነሣትን፥ የዘላለም
ፍርድን ትምህርት እንደገና አንመሥርት።
3 ይልቅስ ወደፊት እንሂድ፤ እግዚአብሔር ቢፈ
ቅድልን ይህንን እናደርጋለን።

4 ከመንገድ የወጡትን ሰዎች ወደ ንስሓ
መመለስ እንዴት ይቻላል! እነዚህ ሰዎች እኮ
ከዚህ በፊት ብርሃን በርቶላቸው ነበር፤ ሰማያዊ
ውንም ስጦታ ቀምሰው ነበር፤ የመንፈስ ቅዱ
ስም ተካፋዮች ሆነው ነበር፤ 5 የእግዚአብሔ
ርን መልካም ቃልና የሚመጣውን ዓለም ኀይል
ቀምሰው ነበር፤ 6 ከዚህ ሁሉ በኋላ ከመንገድ
ከወጡ፥ እነርሱን ወደ ንስሓ መመለስ አይቻ
ልም፤ ምክንያቱም እነርሱ የእግዚአብሔርን
ልጅ እንደገና ይሰቅሉታል፤ ያዋርዱታልም።

7 ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን
ዝናም የጠጣች መሬት፥ ተክል ለተከለባት
ሰው ጥቅም የምትሰጥ በመሆንዋ እግዚአብሔር
ይባርካታል። 8 እሾኽና አሜከላ ብታበቅል ግን
ጥቅመቢስ ትሆናለች፤ ለመረገምም ቀርባለች፤
መጨረሻዋም በእሳት መቃጠል ነው።

9 ወዳጆች ሆይ! ምንም እንኳ እንዲህ ብንና
ገር እናንተ ከደኅንነታችሁ የሚገኝ የተሻለ በረ
ከት እንዳላችሁ እናውቃለን። 10 እግዚአብሔር
ቅን ፈራጅ ነው፤ ሥራችሁንና በፊትም ሆነ
አሁን ቅዱሳንን በመርዳት ስለ ስሙ ያሳያችሁ
ትን ፍቅር አይረሳም። 11 እናንተ ሁላችሁም
በተስፋ የምትጠባበቁትን ነገር እስክትጨብጡ
ድረስ ትጋታችሁን እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ
እንመኛለን፤ 12 የምንመኘውም በእምነትና በት
ዕግሥት ጸንተው በተስፋ የተሰጣቸውን ነገር
የሚወርሱትን ሰዎች እንድትመስሉ እንጂ ዳተ
ኞች እንድትሆኑ አይደለም።

### የእግዚአብሔር ተስፋ እርግጠኛነት

13 እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው
ጊዜ፥ የሚምልበት ከእርሱ የበለጠ ሌላ ማንም
ስለሌለ እንዲህ ሲል በራሱ ማለ፥ 14 "በእርግጥ
እባርክሃለሁ፤ ዘርህንም አበዛዋለሁ።" 15 አብር
ሃም በትዕግሥት ጠብቆ ተስፋ የተደረገለትን
ነገር አገኘ። 16 ሰዎች ሲምሉ ከራሳቸው በሚበ
ልጥ ስም ይምላሉ፤ ንግግራቸውንም በመሐላ
በማጽናት በመካከላቸው ያለውን ክርክር ሁሉ
ያስወግዳሉ። 17 በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር
ውሳኔው የማይለወጥ መሆኑን ለማስረዳት
ፈልጎ፥ ለተስፋው ወራሾች ተስፋውን በመሐላ
አጸናላቸው። 18 በዚሁ ዐይነት እግዚአብሔር
የማይለወጡትንና የማይዋሽባቸውን፥ ሁለቱን
ነገሮች፥ ማለትም ተስፋውንና መሐላውን ሰጥ
ቶናል፤ በእነዚህም በሁለቱ ነገሮች አማካይነት
በፊታችን ያለውን ተስፋ አጥብቀን መያዝ እን
ድንችል መጠጊያ ለማግኘት ወደ እርሱ የሸሸን
እኛ፥ ብርቱ መጽናናትን እናገኛለን። 19 ይህ
ተስፋ ለሕይወታችን እንደማይነቃነቅ አስተማ
ማኝ መልሕቅ ነው፤ እርሱም መጋረጃውን
አልፎ ወደ መቅደስ ይገባል። 20 ወደዚህም
መቅደስ ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ የክህነት
ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት ሆኖ፥ ስለ እኛ
ቀድሞ ገብቶአል።

## ምዕራፍ 7

### ካህኑ መልከ ጼዴቅ

1 መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥና የልዑል
እግዚአብሔር ካህን ነው፤ ይህ መልከ ጼዴቅ
አብርሃም ነገሥታትን አሸንፎ ሲመለስ በመን
ገድ ተገናኝቶ ባረከው። 2 አብርሃምም ካያዘው
ነገር ሁሉ ዐሥራት አውጥቶ ሰጠው፤ (የስሙ
ትርጓሜ አንደኛው "የጽድቅ ንጉሥ" ሌላው
"የሳሌም ንጉሥ" ወይም "የሰላም ንጉሥ"
ማለት ነው።) 3 መልከ ጼዴቅ አባትና እናት
ወይም የትውልድ ሐረግ የለውም፤ ለዘመኑ
መጀመሪያ፥ ለሕይወቱም መጨረሻ የለውም፤
ይህ መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ልጅ ምሳሌ
በመሆን ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።

4 ይህ ሰው እንዴት ታላቅ እንደሆነ ተመል
ከቱ! የነገድ አባት የሆነው አብርሃም እንኳ

4፥3 ፦ መዝ. 95፥11። 4፥4 ፦ ዘፍ. 2፥2። 4፥5 ፦ መዝ. 95፥11። 4፥7 ፦ መዝ. 95፥7-8። 4፥8 ፦ ዘዳ. 31፥7፤
ኢያሱ 22፥4። 4፥10 ፦ ዘፍ. 2፥2። 5፥3 ፦ ዘሌ. 9፥7። 5፥4 ፦ ዘፀ. 28፥1። 5፥5 ፦ መዝ. 2፥7። 5፥6 ፦ መዝ. 110፥4።
5፥7 ፦ ማቴ. 26፥36-46፤ ማር. 14፥32-42፤ ሉቃ. 22፥39-46።

5፥12-13 ፦ 1ቆሮ. 3፥2። 6፥8 ፦ ዘፍ. 3፥17-18። 6፥14 ፦ ዘፍ. 22፥16-17። 6፥19 ፦ ዘሌ. 16፥2።
6፥20 ፦ መዝ. 110፥4። 7፥1-2 ፦ ዘፍ. 14፥17-20።

በምርኮ ካገኘው ነገር ዐሥራት አውጥቶ
ሰጠው ። 5 እነዚያ በክህነት ሥራ ላይ የሚመደ
ቡት የሌዊ ዘሮች ከሕዝቡ ዐሥራት እንዲቀበሉ
በሙሴ ሕግ ታዘዋቸዋል ፤ ታዲያ እኮ ይህም
ሕዝብ የአብርሃም ዘርና የእነርሱም ወንድም
ነው ። 6 ምንም እንኳ ያ መልከ ጼዴቅ የሌዋው
ያን ዘር ባይሆንም ፥ ከአብርሃም ዐሥራትን ተቀ
በለ ፤ የተስፋ ቃል የተሰጠውን አብርሃምንም
ባረከው ። 7 ቡራኬን ከሚቀበል ይልቅ ፥ ቡራ
ኬን የሚሰጥ እንደሚበልጥ ጥርጥር የለውም ።
8 በአንድ በኩል ዐሥራት የሚቀበሉት ሟች የሆ
ኑት ሌዋውያን ናቸው ፤ በሌላ በኩል ግን ዐሥ
ራት የሚቀበለው ሕያው ሆኖ እንደሚኖር የተ
መሰከረለት መልከ ጼዴቅ ነው ። 9 እንግዲህ
ዐሥራትን መቀበል የሚገባው ሌዊ ራሱ በአብር
ሃም አማካይነት ዐሥራትን ሰጥቶአል ማለት
ነው ፤ 10 ምክንያቱም መልከ ጼዴቅ አብርሃምን
በተገናኘው ጊዜ ሌዊ ከአባቱ ከአብርሃም ገና
አልተወለደም ነበር ።
11 እንግዲህ ለሕዝቡ ሕግ የተሰጠው በሌዊ
ክህነት መሠረት ነው ፤ ይህ ክህነት ፍጹም
ቢሆን ኖሮ ፥ የአሮን የክህነት ሹመት ሳይሆን ፥
የመልከ ጼዴቅ የክህነት ሹመት ያለው ሌላ
ካህን መምጣት ባላስፈለገም ነበር ፤ 12 ምክንያ
ቱም ክህነት ሲለወጥ ፥ ሕጉም እንዲለወጥ ያስፈ
ልጋል ። 13 ይህ ሁሉ የተነገረለት ካህን ከሌላ
ነገድ ነው ፤ ከዚህ ነገድ ማንም ወደ መሠዊ
ያው ቀርቦ ያገለገለ የለም ። 14 ጌታችን ከይሁዳ
ነገድ መሆኑ የታወቀ ነው ፤ ሆኖም ሙሴ ስለ
ካህናት ሲናገር የይሁዳን ነገድ አስመልክቶ የተ
ናገረው ምንም ነገር የለም ።

### ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ካህን ነው

15 ይህ ነገር በጣም ግልጥ ሆኖ የሚገኘው
እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ሌላ ካህን ሲመጣ
ነው ፤ 16 እርሱ ካህን የሆነው በሥጋዊ ሕግ
መሠረት ሳይሆን በማይሻር ሕይወት ኀይል
ነው ፤ 17 ምክንያቱም “እንደ መልከ ጼዴቅ
የክህነት ሹመት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ”
ተብሎ ተመስክሮለታል ። 18 የቀድሞው ትእ
ዛዝ ደካማና የማይጠቅም ስለሆነ ተሽሮአል ፤
19 ምክንያቱም በሙሴ ሕግ ምንም ነገር
ፍጹም ሊሆን አልቻለም ፤ አሁን ግን ወደ
እግዚአብሔር የምንቀርብበት የተሻለ ተስፋ
መጥቶአል ።
20 ከዚህም በቀር ይህ ክህነት ያለ መሐላ
የሆነ አይደለም ፤ እነዚያ ከዚህ በፊት ካህናት
የሆኑት ያለ መሐላ ነው ፤ 21 እርሱ ግን ካህን
የሆነው በመሐላ ነው ፤ ምክንያቱም ፥

“ጌታ ‘አንተ ለዘላለም ካህን ነህ’ ብሎ
ምሎአል ፤
አይጸጸትም” ተብሎ ተነግሮለታል ።

22 በዚህ መሐላ ምክንያት ኢየሱስ ለተሻለው
ኪዳን ዋስ ሆኖአል ።
23 በሞት ምክንያት አንድ ካህን ሳይለወጥ
በሥራው ላይ ለዘላለም መኖር ስለማይችል ፥
የቀድሞዎቹ ካህናት ቍጥራቸው ብዙ ነበር ፤
24 እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ ክህነቱ
የማይለወጥ ነው ። 25 ስለዚህ እነርሱን ለማማ
ለድ ለዘላለም ሕያው ሆኖ ስለሚኖር ፥ በእርሱ
አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን
ሁሉ በፍጹም ሊያድናቸው ይችላል ።
26 እንግዲህ የሚያስፈልገንን የሚያዘጋጅልን
ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ነው ፤ እርሱ ቅዱስ
የሆነ ፥ ያለ ነቀፋ የሆነ ፥ ንጹሕ የሆነ ፥ ከኃጢ
አተኞች የተለየ ፥ ከሰማያት በላይ ከፍ ያለ
ነው ። 27 እርሱ እኮ እንደ ሌሎቹ ሊቃነ ካህ
ናት በመጀመሪያ ስለ ራሱ ኃጢአት ፥ በኋላም
ስለ ሕዝቡ ኃጢአት በየቀኑ መሥዋዕት ማቅረብ
አያስፈልገውም ፤ ምክንያቱም ራሱን መሥዋ
ዕት አድርጎ ባቀረበ ጊዜ ይህን ነገር በማያዳግም
ሁኔታ ፈጽሞታል ። 28 የሙሴ ሕግ ሊቀ ካህናት
አድርጎ የሚሾማቸው ደካሞች ሰዎችን ነው ፤
ከሕግ በኋላ የመጣው የመሐላ ቃል ግን ለዘላ
ለም ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ልጅ
ይሾማል ።

## ምዕራፍ 8

### ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ነው

1 እንግዲህ ከምንነጋገርባቸው ነገሮች ዋናው
ነገር ይህ ነው ፤ በሰማይ በልዑል እግዚአብሔር
ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት
አለን ፤ 2 እርሱ የሚያገለግለው እውነተኛ
ድንኳን በሆነችው መቅደስ ነው ፤ ይህች
ድንኳን የተተከለችው በሰው እጅ ሳይሆን በእግ
ዚአብሔር ነው ።
3 እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት የሚሾመው መባ
ንና መሥዋዕትን ለማቅረብ ነው ፤ ስለዚህ ይህም
ካህን የሚያቀርበው አንድ ነገር ሊኖረው ያስፈ
ልጋል ። 4 እርሱ በምድር ቢሆን ኖሮ ካህን ባል
ሆነም ነበር ፤ ምክንያቱም በሙሴ ሕግ መሠ
ረት መባን የሚያቀርቡ ካህናት አሉ ። 5 እነርሱ
የሚያገለግሉት ለሰማያዊ ነገሮች ምሳሌና ጥላ
በሆኑት ነገሮች ነው ፤ ይህም የሆነው ሙሴ
ድንኳኒቱን በሚሠራበት ጊዜ ፥ እግዚአብሔር
“በተራራው ላይ እንደተገለጠልህ ዐይነት
ሁሉን ነገር በጥንቃቄ አድርግ” ብሎ ባዘዘው
መሠረት ነው ። 6 አሁን ግን ኢየሱስ አማካይ

7፥5 ፦ ዘኍ. 18፥21 ። 7፥17 ፦ መዝ. 110፥4 ። 7፥21 ፦ መዝ. 110፥4 ። 7፥27 ፦ ዘሌ. 9፥7 ። 8፥1 ፦ መዝ. 110፥1 ።
8፥5 ፦ ዘጸ. 25፥40 ።



የሆነበት ኪዳን ከአሮጌው ኪዳን የበለጠና በተ
ሻለ ተስፋ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ
መጠን ፥ ለእርሱ የተሰጠው አገልግሎት የበለጠ
ነው ።
7 የመጀመሪያው ኪዳን ነቀፋ የሌለው ሆኖ
ቢገኝ ኖሮ ፥ ሁለተኛው ኪዳን ባላስፈለገ ነበር ።
8 ምክንያቱም እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ነቀፋ
መኖሩን በማመልከት እንዲህ ይላል ፥

“እነሆ ከእስራኤል ሕዝብና ከይሁዳ
ሕዝብ ጋር
አዲስ ኪዳን የምገባበት ጊዜ ይመጣል
ይላል ጌታ ።
9 ይህም ኪዳን እነርሱን ከግብጽ
ለማውጣት እጃቸውን በያዝሁ ጊዜ
ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ኪዳን
ያለ አይደለም ፤
እነርሱ በኪዳኔ ስላልጸኑ ፥
እኔም ችላ አልኩአቸው ይላል ጌታ ።
10 እነሆ! ከዚህ ጊዜ በኋላ ከእስራኤል
ሕዝብ ጋር
የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ ፥
እኔ ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ ፤
በአእምሮአቸውም እጽፈዋለሁ ፤
አምላካቸውም እሆናለሁ ፤
እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ ።
11 ‘እግዚአብሔርን ዕወቅ’ ብሎ የአገሩንም
ሰው ሆነ ፥
ወንድሙን የሚያስተምር ማንም
አይኖርም ፤
ምክንያቱም ከትንሹ ጀምሮ እስከ
ትልቁ ሁሉም ያውቀኛል ፤
12 በደላቸውን ይቅር እልላቸዋለሁ ፤
ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ
አላስታውስባቸውም ።”

13 እንግዲህ “አዲስ ኪዳን” ሲል የፊተኛ
ውን ኪዳን አሮጌ አድርጎታል ማለት ነው ፤ ስለ
ዚህ የተሠራበትና አሮጌው ነገር ሁሉ የሚጠፋ
በት ጊዜ ተቃርቧል ።

## ምዕራፍ 9

### ሰማያዊው መንፈሳዊ አገልግሎት ከምድራዊው መንፈሳዊ አገልግሎት የበለጠ ነው

1 የመጀመሪያው ኪዳን የመንፈሳዊ አገልግ
ሎት ሥርዓትና ምድራዊ መቅደስ ነበረው ፤
2 ሁለት ክፍሎች ያሉአት ድንኳን ተዘጋጅታ
ነበር ። መቅረዙና ጠረጴዛው ፥ የመሥዋዕቱም
ኅብስት የነበረባት መጀመሪያይቱ ክፍል “ቅድ
ስት” ትባል ነበር ። 3 ከሁለተኛው መጋረጃ
ወዲያ የምትገኘው ውስጠኛዋ ክፍል “ቅድስተ
ቅዱሳን” ትባል ነበር ። 4 በዚህችኛዋ ክፍል
ውስጥ የወርቅ ማዕጠንትና በወርቅ የተለበጠች
የኪዳን ታቦት ነበሩባት ፤ ከዚህችም የኪዳን
ታቦት ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብ ፥ የለ
መለመችው የአሮን በትር ፥ ኪዳኑ የተጻፈባት
ጽላት ነበሩ ። 5 በታቦትዋም ላይ ያለውን የስር
የት መክደኛ በክንፋቸው የሚጋርዱ የክብር
ኪሩቤል ነበሩ ፤ ነገር ግን ስለእነዚህ ነገሮች
ሁሉ አሁን በዝርዝር መናገር አንችልም ።
6 ሁሉ ነገር በዚህ ሁኔታ ከተዘጋጀ በኋላ
ካህናት አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ወደ
ድንኳኒቱ መጀመሪያ ክፍል ዘወትር ይገባሉ ።
7 ወደ ሁለተኛዋ ውስጠኛ ክፍል የሚገባው ግን
ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነው ፤ የሚገባውም በዓመት
አንድ ቀን ብቻ ነው ፤ እርሱም ስለ ራሱ ኃጢአ
ትና ሕዝቡ ባለማወቅ ስላደረገው ኃጢአት የሚ
ያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም ። 8 የመጀመሪ
ያይቱ ድንኳን እስካለች ድረስ ወደ ቅድስተ
ቅዱሳን የሚወስደው መንገድ ገና ያልተገለጠ
መሆኑን መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዐይነት ያሳያል ።
9 ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው ፤ በዚህ ዐይ
ነት የሚቀርቡት መባና መሥዋዕት የአቅራቢ
ውን ሰው ኅሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይች
ሉም ፤ 10 እነዚህ ነገሮች የመታደስ ጊዜ እስኪ
መጣ ድረስ በሥራ ላይ የዋሉ ዓለማዊ ሥርዓ
ቶች ናቸው ፤ እነርሱ ስለ መብልና ስለ
መጠጥ ፥ ስለ ልዩ ልዩ የመታጠብ ሥርዓቶችም
ብቻ የተደረጉ ናቸው ።
11 ነገር ግን ክርስቶስ አሁን ለሚሆኑት[1*]
መልካም ነገሮች ሊቀ ካህናት ሆኖ መጥቶአል ፤
እርሱ የገባባት ድንኳን ትልቅና ፍጹም ናት ፤
ይህች ድንኳን በሰው እጅ ያልተሠራችና ከዚህ
ፍጥረት ያልሆነች ናት ። 12 እርሱ ወደ ቅድስተ
ቅዱሳን በማያዳግም ሁኔታ የራሱን ደም ይዞ
ገባ እንጂ የፍየሎችንና የኮርማዎችን ደም ይዞ
አልገባም ፤ በዚህም ዐይነት የዘላለም ደኅንነትን
አስገኘልን ። 13 የፍየሎችና የኮርማዎች ደም ፥
ለመሥዋዕት የተቃጠለች ጊደር ዐመድ በረከሱ
ሰዎች ላይ ሲረጭ ከሥጋዊ ርኲሰት አንጽቶ
የሚቀድሳቸው ከሆነ ፥ 14 በዘላለም መንፈስ አማ
ካይነት ራሱን ነውር የሌለበት መሥዋዕት አድ
ርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክርስቶስ ደምማ
ሕያው እግዚአብሔርን እንድናገለግል ኅሊናች
ንን ከሞተ ሥራ እንዴት ይበልጥ ያነጻ!
15 የተጠሩት እግዚአብሔር በተስፋ የሰጠ
ውን ዘላለማዊ ርስት እንዲወርሱ ፥ ክርስቶስ የአ
ዲስ ኪዳን ማእከላዊ ሆኖአል ፤ ይህም የሆነው

1* 9፥11 አሁን ለሚሆኑት ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ወደፊት ለሚመጡት” ይላሉ ።
8፥8-12 ፦ ኤር. 31፥31-34 ። 9፥2 ፦ ዘጸ. 26፥1-30 ፤ 25፥31-40 ። 9፥3 ፦ ዘጸ. 26፥31-33 ።
9፥4 ፦ ዘጸ. 30፥1-6 ፤ 25፥10-16 ፤ 16፥33 ፤ ዘኍ. 17፥8-10 ፤ ዘጸ. 25፥16 ፤ ዘዳ. 10፥3-5 ። 9፥5 ፦ ዘጸ. 25፥18-22 ።
9፥6 ፦ ዘኍ. 18፥2-6 ። 9፥7 ፦ ዘሌ. 16፥2-34 ። 9፥13 ፦ ዘሌ. 16፥15-16 ፤ ዘኍ. 19፥9 ፣17-19 ።

ሰዎችን ከመጀመሪያው ኪዳን ሥር ሆነው ከሠ
ሩት ኃጢአት ለማዳን እርሱ በመሞቱ ነው።
16 ኑዛዜ ሲኖር የተናዛዡን ሞት ማረጋገጥ
ያስፈልጋል፤ 17 ምክንያቱም የኑዛዜ ቃል የሚጸ
ናው ተናዛዡ ከሞተ በኋላ ነው፤ ተናዛዡ በሕ
ይወት ካለ ግን የኑዛዜው ቃል ዋጋ የለውም።
18 በዚህ ምክንያት የመጀመሪያው ኪዳን እንኳ
ያለ ደም የጸና አይደለም። 19 በመጀመሪያ
ሙሴ የሕግን ትእዛዛት ለሕዝቡ ሁሉ ነገረ፤
ከዚህ በኋላ የኮርማዎችንና የፍየሎችን ደም
ከውሃ ጋር አድርጎ የሕጉን መጽሐፍና ሕዝቡን
ሁሉ በሂሶጵና በቀይ የበግ ጠጕር ረጨ፤ 20 የረ
ጨውም "እግዚአብሔር የደነገገላችሁ የኪዳን
ደም ይህ ነው" ብሎ ነው። 21 እንዲሁም
በድንኳኒቱና በማገልገያ ዕቃ ሁሉ ላይ ደምን
ረጨ። 22 በእርግጥም በሙሴ ሕግ መሠረት ከጥ
ቂት ነገር በቀር ሁሉም ነገር በደም ይነጻል፤
ደም ካልፈሰሰም የኃጢአት ስርየት አይገኝም።

የክርስቶስ መሥዋዕትነት ኃጢአትን ያስወግዳል

23 እንግዲህ እነዚህ የሰማያዊ ነገሮች ምሳሌ
የሆኑት ሁሉ በዚህ ዐይነት ሥርዓት መንጻት
ያስፈልጋቸው ነበር፤ የሰማይ ነገሮች ግን ከዚህ
በሚበልጥ መሥዋዕት መንጻት ያስፈልጋቸ
ዋል። 24 ምክንያቱም ክርስቶስ የእውነተኛይቱ
"ቅድስት" ምሳሌ ወደ ሆነችውና በሰው እጅ
ወደተሠራችው ቅድስተ ቅዱሳን አልገባም፤
እርሱ አሁን ስለእኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመ
ታየት ወደ ሰማይ ገባ። 25 የአይሁድ ሊቀ ካህ
ናት የራሱ ያልሆነውን ደም ይዞ በየዓመቱ ወደ
ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር፤ ክርስቶስ ግን
ራሱን ብዙ ጊዜ መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ
አልገባም። 26 እንዲህማ ቢሆን ኖሮ፥ ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ መቀበል ባስ
ፈለገው ነበር፤ አሁን ግን በዘመናት መጨረሻ
ኃጢአትን ለማስወገድ ራሱን መሥዋዕት በማድ
ረግ በማያዳግም ሁኔታ ተገልጦአል። 27 ለሰው
አንድ ጊዜ መሞት የተገባ ነው፤ ከሞት በኋ
ላም ፍርድ አለበት። 28 እንዲሁም ክርስቶስ
የብዙዎችን ኃጢአት ለማስወገድ አንድ ጊዜ
ተሠውቶአል፤ ደግሞም ኃጢአትን ለመሸከም
ሳይሆን፥ እርሱን የሚጠባበቁትን ለማዳን ሁለ
ተኛ ጊዜ ይገለጣል።

## ምዕራፍ 10

1 የሙሴ ሕግ ወደ ፊት ለሚመጣው መል
ካም ነገር ምሳሌ ነበር እንጂ እውነተኛ መልክ
አልነበረውም፤ ስለዚህ በየዓመቱ ዘወትር የሚ
ሠዉትን መሥዋዕቶች ይዘው ወደ እግዚአብ
ሔር የሚቀርቡትን ሰዎች ፍጹሞች ሊያደርጋ
ቸው ከቶ አይችልም። 2 ሕግ ፍጹሞች ሊያደር
ጋቸው ቢችልማ ኖሮ፥ እነርሱ መሥዋዕትን
ማቅረብ በተዉ ነበር፤ ምክንያቱም ለአምልኮ
የሚቀርቡት ሰዎች በማያዳግም ሁኔታ ከኃጢ
አት ስለነጹ፥ ኃጢአት እንደሌለባቸው በኅሊና
ቸው ይታወቃቸዋል። 3 እነዚያ መሥዋዕቶች
ግን በየዓመቱ ኃጢአትን የሚያስታውሱባቸው
ናቸው። 4 ምክንያቱም የኮርማዎችና የፍየሎች
ደም ኃጢአትን ለማስወገድ አይችልም።
5 ስለዚህ ክርስቶስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ
እንዲህ አለ፥

"መሥዋዕትንና መባን አልፈለግህም፥
ሰውነትን ግን አዘጋጀህልኝ፤
6 በሚቃጠል መሥዋዕትና
ስለ ኃጢአት ስርየት በሚሠዋ
መሥዋዕት አልተደሰትህም፤
7 በዚያን ጊዜ፥
'አምላኬ ሆይ! በመጽሐፍ ስለ እኔ
እንደተጻፈ
ፈቃድህን ለመፈጸም መጥቻለሁ'
አልሁ።"

8 በመጀመሪያ "እነዚያን በሕጉ መሠረት የሚቀ
ርቡትን መሥዋዕትንና መባን፥ የሚቃጠለውን
መሥዋዕትና ስለ ኃጢአት ስርየት የሚሠዋውን
መሥዋዕት አልፈለግህም፤ በእነርሱም አልተደ
ሰትህም" አለ። 9 ቀጥሎም "እነሆ! ፈቃድህን
ለመፈጸም መጥቻለሁ" አለ፤ በዚህ ሁኔታ ሁለ
ተኛውን ዐይነት መሥዋዕት በቦታው ለመተካት
የመጀመሪያውን ዐይነት መሥዋዕት ሽሮአል።
10 በዚህም "ፈቃድ" በሚለው ቃል መሠረት
ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በማያዳግም ሁኔታ
መሥዋዕት ሆኖ በመቅረቡ ምክንያት ተቀድሰ
ናል።
11 እያንዳንዱ ካህን ኃጢአትን ማስወገድ
የማይችሉትን እነዚያኑ መሥዋዕቶች ዘወትር
እያቀረበ በየቀኑ ቆሞ ያገለግላል። 12 ክርስቶስ
ግን ለዘላለም የሆነውን አንዱን መሥዋዕት ካቀ
ረበ በኋላ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ
አል። 13 ከእንግዲህ ወዲህ ጠላቶቹ በሥልጣኑ
ሥር እስኪሆኑ ድረስ ይጠባበቃል፤ 14 ምክንያ
ቱም እንደዚህ የተቀደሱትን በአንዱ መሥዋዕት
አማካይነት ለዘላለም ፍጹሞች ስለሚያደርጋ
ቸው ነው።
15 መንፈስ ቅዱስም በዚህ ነገር ይመሰክርል
ናል፤ በመጀመሪያ፥

16 "ከእነዚያ ቀኖች በኋላ
ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ
ነው ይላል ጌታ፥



ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ፤
በአእምሮአቸውም እጽፈዋለሁ።"

17 ቀጥሎም "ኃጢአታቸውንና ክፉ ሥራቸ
ውን ከእንግዲህ ወዲህ አላስታውስባቸውም"
ይላል።
18 ስለዚህ ኃጢአት ሁሉ ከተደመሰሰ በኋላ፥
ስለ ኃጢአት ስርየት የሚቀርብ መሥዋዕት ከእ
ንግዲህ ወዲህ አይኖርም።

ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይገባል

19 እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ! በኢየሱስ ደም
አማካይነት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት የሚ
ያስችለንን መተማመኛ አግኝተናል፤ 20 የምንገባ
ውም በመጋረጃው፥ ማለትም በሰውነቱ አማካይ
ነት በከፈተልን በአዲሱና ዘላለማዊ በሆነው መን
ገድ ነው። 21 በእግዚአብሔር ቤት ላይ ሥልጣን
ያለው ትልቅ ካህን አለን። 22 ስለዚህ ከክፉ
ኅሊና እንድንነጻ ልባችንን ተረጭተን፥ ሰውነታ
ችንንም በንጹሕ ውሃ ታጥበን፥ ቅን ልብና እው
ነተኛ እምነት ይዘን ወደ እግዚአብሔር እንቅ
ረብ። 23 የተስፋን ቃል የሰጠን ታማኝ ስለሆነ፥
አሁን እምነን የምንመሰክረውን ተስፋ ሳናወላ
ውል አጥብቀን እንያዝ። 24 በፍቅርና በመልካም
ሥራ ነቅተን እንድንኖር አንዱ ሌላውን ያሳስ
በው፥ 25 ዘወትር እየተገናኘን እርስ በርሳችን
እንበረታታ እንጂ አንዳንዶች ማድረግ እንደለመ
ዱት መሰብሰባችንን አንተው፤ ይልቁንም የጌታ
መምጫ ቀን መቃረቡን እያስታወሳችሁ ይህን
ነገር በይበልጥ አድርጉ።
26 እውነትን ካወቅን በኋላ ሆን ብለን ኃጢ
አት ብንሠራ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት
የሚቀርብ ምንም መሥዋዕት አይኖረንም።
27 አሁን የሚቀረው ግን ወደ ፊት የሚሆነው
አስፈሪ ፍርድና ተቃዋሚዎችን የሚያቃጥል
አስፈሪ እሳት ነው። 28 የሙሴን ሕግ የጣሰ
ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ከመሰከሩበት ያለ
ምሕረት በሞት ይቀጣል። 29 ታዲያ የእግዚአብ
ሔርን ልጅ የናቀ፥ የተቀደሰበትን የኪዳን ደም
ያረከሰ፥ የጸጋን መንፈስ የሰደበ፥ እንዴት ያለ
የባሰ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል! 30 ምክን
ያቱም "በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እከ
ፍላለሁ" ያለው ማን መሆኑን እናውቃለን፤
እንዲሁም "እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ይፈር
ዳል" ይላል። 31 ስለዚህ በሕያው እግዚአብሔር
እጅ መውደቅ እጅግ የሚያስፈራ ነው።
32 ብርሃን ከበራላችሁ በኋላ ብዙ መከራ
ተቀብላችሁ የታገሣችሁባቸውን እነዚያን የቀድ
ሞዎቹን ቀኖች አስታውሱ። 33 አንዳንድ ጊዜ
በሰው ፊት ተሰድባችኋል፤ ተንገላታችኋል፤
አንዳንድ ጊዜም ይህን ዐይነት ሥቃይ ከደረሰባ
ቸው ሰዎች ጋር በመተባበር አብራችሁ መከራ
ተቀብላችኋል። 34 እናንተ የተሻለና ለዘወትር
የሚኖር ሀብት በሰማይ እንዳላችሁ በማወቃችሁ
ለእስረኞች ራራችሁላቸው፤ ንብረታችሁም
ሲወሰድባችሁ ታግሣችሁ ሁኔታውን በደስታ
ተቀበላችሁ። 35 እንግዲህ ታላቅ ሽልማት የም
ታገኙበትን መተማመኛችሁን አትጣሉት።
36 የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽማችሁ፥ እግዚ
አብሔር ሊሰጣችሁ ቃል የገባላችሁን ነገር ለማ
ግኘት መጽናት ያስፈልጋችኋል። 37 ምክንያ
ቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፥

"መምጣት የሚገባው
ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይመጣል፤
አይዘገይምም፤
38 ጻድቅ ሰው ግን በእምነት ሕይወትን
ያገኛል፤
ወደ ኋላው ቢያፈገፍግ ግን ነፍሴ
በእርሱ አትደሰትም።"

39 እኛ ግን አምነው ከሚድኑት ወገን ነን እንጂ
ወደ ኋላ አፈግፍገው ከሚጠፉት ሰዎች ወገን
አይደለንም።

## ምዕራፍ 11

### እምነት

1 እምነት ማለት በተስፋ የምንጠባበቃቸውን
ነገሮች እንደምናገኝ የሚያረጋግጥ፥ የማናያቸ
ውም ነገሮች ስለመኖራቸው የሚያስረዳ ነው።
2 የቀድሞ ሰዎች የተመሰገኑት በእምነት ምክን
ያት ነው።
3 ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈ
ጠሩ የምንረዳው በእምነት ነው፤ ስለዚህ የሚ
ታየው ነገር ሁሉ ከማይታየው እንደተሠራ እና
ውቃለን።
4 አቤል ከቃየል መሥዋዕት የበለጠውን
መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቀረበው በእምነት
ነው፤ እግዚአብሔር የአቤልን መባ በደስታ
በተቀበለ ጊዜ አቤል በእምነቱ ጻድቅ መሆኑ
ተመሰከረለት፤ አቤል ከሞተ በኋላ በእምነቱ
አማካይነት አሁንም እየተናገረ ነው።
5 ሔኖክ ሞት እንዳይደርስበት ወደ ላይ የተ
ወሰደው በእምነት ነው፤ እግዚአብሔር ስለ
ወሰደውም አልተገኘም፤ ምክንያቱም ከመወ
ሰዱ በፊት እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስ
ክሮለታል። 6 ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ
ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአ
ብሔር የሚቀርብ ሰው፥ እግዚአብሔር መኖሩ
ንና እርሱን ለሚፈልጉት ሰዎችም ሽልማት
የሚሰጥ መሆኑን ማመን አለበት።

---

9፥19-20 ፦ ዘጸ. 24፥6-8።  9፥21 ፦ ዘሌ. 8፥15።  9፥22 ፦ ዘሌ. 17፥11።  9፥28 ፦ ኢሳ. 53፥12።
10፥5-7 ፦ መዝ. 40፥6-8።  10፥11 ፦ ዘጸ. 29፥38።  10፥12-13 ፦ መዝ. 110፥1።  10፥16 ፦ ኤር. 31፥33።

10፥17 ፦ ኤር. 31፥34።  10፥22 ፦ ዘሌ. 8፥30፤ ሕዝ. 36፥25።  10፥27 ፦ ኢሳ. 26፥11።
10፥28 ፦ ዘዳ. 17፥6፤ 19፥15።  10፥29 ፦ ዘጸ. 24፥8።  10፥30 ፦ ዘዳ. 32፥35-36።  10፥37-38 ፦ ዕን. 2፥3-4።
11፥3 ፦ ዘፍ. 1፥1፤ መዝ. 33፥6፡9፤ ዮሐ. 1፥3።  11፥4 ፦ ዘፍ. 4፥3-10።  11፥5 ፦ ዘፍ. 5፥21-24።

7 ገና ስለማይታየው ነገር እግዚአብሔር አስ
ጠንቅቆ በነገረው ጊዜ ኖኅ እግዚአብሔርን በመ
ፍራት ቤተ ሰቡን ለማዳን መርከብን የሠራው
በእምነት ነው ፤ በእምነቱም ዓለምን ኰነነ ፤
በእምነት የሚገኘውንም ጽድቅ ወረሰ ።
8 አብርሃም ርስት አድርጎ ወደሚቀበለው
ስፍራ እንዲሄድ በተጠራ ጊዜ ፥ ምንም እንኳ
ወዴት እንደሚሄድ ባያውቅም ለመሄድ እሺ
ብሎ የታዘዘው በእምነት ነው ። 9 እንደ እርሱ
የተስፋው ቃል ወራሾች ከሆኑት ከይስሐቅና
ከያዕቆብ ጋር በተስፋይቱ አገር መጻተኛ ሆኖ
በድንኳን የኖረው በእምነት ነው ። 10 ምክንያ
ቱም ጽኑ መሠረት ያላትን ፥ እግዚአብሔር ያቀ
ዳትንና የሠራትን ከተማ ይጠባበቅ ስለ ነበር
ነው ።
11 ሣራም ተስፋ ሰጪው እግዚአብሔር
ታማኝ መሆኑን ስላወቀች ፥ ምንም እንኳ በዕ
ድሜ በመግፋቷ ምክንያት መውለድ የማትችል
ብትሆንም የመፅነስን ኀይል ያገኘችው በእም
ነት ነው ። 12 ስለዚህ እንደ ሞተ ሰው ከሚቈጠ
ረው ከአብርሃም እንደ ሰማይ ከዋክብት የበዛና
እንደ ባሕር ዳር አሸዋ የማይቈጠር ዘር ተገኘ ።
13 እነዚህ ሁሉ የሞቱት በእምነት ሆነው
ነው ፤ እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ቃል የገባላቸ
ውንም ነገር አላገኙም ፤ ነገር ግን ከሩቅ አይ
ተው ልክ እንዳገኙት አድርገው ተደሰቱ ፤ በም
ድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች መሆናቸውንም
ተገነዘቡ ። 14 እንዲህ የሚናገሩ ሰዎች የራሳ
ቸው የሚሆነውን አገር እንደሚጠባበቁ ያመለክ
ታሉ ። 15 ያንን የወጡበትን አገር አስታውሰ
ውት ቢሆን ኖሮ ወደዚያ ለመመለስ በቻሉ
ነበር ። 16 አሁን ግን የሚበልጠውን ፥ በሰማይ
ያለውን አገር ይናፍቃሉ ፤ ስለዚህ እግዚአብ
ሔር ከተማን ስላዘጋጀላቸው "አምላካችን"
ብለው ቢጠሩት አያሳፍረውም ።
17 አብርሃም በተፈተነበት ጊዜ ይስሐቅን
መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው በእምነት ነው ፤
የተስፋን ቃል የተቀበለው አብርሃም አንድ
ልጁን ሊሠዋው ነበር ፤ 18 ታዲያ እኮ እግዚአብ
ሔር ፥ "በይስሐቅ ዘር ይወጣልሃል" ብሎት
ነበር ። 19 እግዚአብሔር ከሞት የማስነሣት
ችሎታ እንዳለው አብርሃም በማመኑ ፥ ልክ
ከሞት የመነሣት ያህል ይስሐቅን እንደገና አገ
ኘው ። 20 ይስሐቅ ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር
በማሰብ ያዕቆብንና ዔሳውን የባረካቸው በእም
ነት ነው ።
21 ያዕቆብ የሚሞትበት ጊዜ ሲቃረብ የዮሴ
ፍን ልጆች እያንዳንዳቸውን የባረካቸውና በብ
ትሩ ጫፍ ተደግፎ የሰገደው በእምነት ነው ።
22 ዮሴፍም የሚሞትበት ጊዜ ሲቃረብ እስራ
ኤላውያን ከግብጽ እንደሚወጡ የተናገረው ፥
ስለ ዐፅሙም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ትእ
ዛዝ የሰጠው በእምነት ነው ።
23 የሙሴ ወላጆች ሙሴ በተወለደ ጊዜ
መልከ መልካም መሆኑን ስላዩ የንጉሡን ትእ
ዛዝ ሳይፈሩ ሦስት ወር የሸሸጉት በእምነት
ነው ።
24 ሙሴ ካደገ በኋላ "የፈርዖን የልጅ ልጅ"
ተብሎ መጠራትን እምቢ ያለው በእምነት
ነው ፤ 25 ስለዚህም በኃጢአት ከሚገኘው ጊዜ
ያዊ ደስታ ይልቅ ፥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር
መከራ መቀበልን መረጠ ። 26 ወደፊት የሚቀበለ
ውን ሽልማት ስለ ተመለከተ ፥ ከግብጽ ሀብት
ይልቅ ስለ መሲሕ መዋረድ የበለጠ ሀብት መሆ
ኑን አሰበ ።
27 የንጉሡንም ቍጣ ሳይፈራ ከግብጽ የወ
ጣው በእምነት ነው ፤ የማይታየውንም አምላክ
እንዳየው ያህል ሆኖ በዓላማው ጸና ። 28 የበኵር
ልጆችን ለመግደል የታዘዘው መልአክ የእስራኤ
ላውያንን የበኵር ልጆች እንዳይገድል በማለት
የፋሲካንና የደም መርጨትን ሥርዓት ያደረ
ገው በእምነት ነው ።
29 እስራኤላውያን በደረቅ ምድር እንደሚሻ
ገሩ ሆነው ቀይ ባሕርን የተሻገሩት በእምነት
ነው ፤ ግብጻውያን ግን እንዲሁ ለማድረግ በሞ
ከሩ ጊዜ ሁሉም ሰጠሙ ።
30 እስራኤላውያን በኢያሪኮ ቅጽሮች ዙሪያ
ሰባት ቀን ከዞሩ በኋላ ቅጽሮቹን ያፈረሱት በእ
ምነት ነው ። 31 አመንዝራይቱ ረዓብ ሰላዮችን
በሰላም ስለተቀበለቻቸው ከማይታዘዙት ጋር
ከመሞት የተረፈችው በእምነት ነው ።
32 እንግዲህ ሌላ ምን እላለሁ! ስለ ጌዴ
ዎን ፥ ስለ ባራቅ ፥ ስለ ሳምሶን ፥ ስለ ዮፍ
ታሔ ፥ ስለ ዳዊት ፥ ስለ ሳሙኤል ፥ ስለ ነቢያ
ትም እንዳልተርክ ጊዜ ያጥረኛል ፤ 33 እነርሱ
በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ ፤ በትክክ
ለኛ ፍትሕ አስተዳደሩ ፤ የተሰጣቸውን ተስፋ
አገኙ ፤ የአንበሶችን አፍ ዘጉ ፤ 34 የእሳትን





ኀይል አጠፉ ፤ ከሰይፍ ስለት አመለጡ ፤ ከደካ
ማነት ወደ ብርቱነት ተለወጡ ፤ በጦርነት ኀይ
ለኞች ሆኑ ፤ የወራሪ ጠላትን ወታደሮች አባ
ረሩ ፤ 35 ሴቶች በሞት የተለዩአቸውን ዘመዶቻ
ቸውን ከሞት ተነሥተው አገኙዋቸው ። ሌሎ
ችም የበለጠ ትንሣኤ ለማግኘት አስበው ልዩ
ልዩ ሥቃይ ተቀበሉ ፤ ከእስራት ነፃ መሆንንም
እምቢ አሉ ። 36 ሌሎች መዘባበቻ ሆነው ተገ
ረፉ ፤ ሌሎች በእግር ብረት ታስረው ወደ ወህኒ
ቤት ተጣሉ ፤ 37 በድንጋይ ተወገሩ ፤ በመጋዝ
ተሰነጠቁ ፤ በሰይፍ ተገደሉ ፤ የበግና የፍየል
ቆዳ ለብሰው ተንከራተቱ ፤ ድኾችና ስደተኞች
ሆነው ተንገላቱ ፤ 38 በበረሓ ፥ በተራራ ፥ በም
ድር ውስጥ ባሉ ዋሻዎችና ፈፋዎች ዞሩ ። በዚ
ህም ዐይነት ዓለም ለእነርሱ ተገቢ ሥፍራ ሆና
አልተገኘችም ።
39 እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰገኑ
ቢሆኑም ፥ የተሰጣቸውን ተስፋ ገና አላገኙም ።
40 እግዚአብሔር ለእኛ የተሻለ ነገር ዐቅዶል
ናል ፤ ስለዚህ እነርሱ ከእኛ ጋር እንጂ ብቻቸ
ውን ፍጹሞች መሆን አይችሉም ።

## ምዕራፍ 12

### እግዚአብሔር አባታችን ነው

1 እንደ ደመና በዙሪያችን የከበቡን እነዚህ
ሁሉ ምስክሮች አሉልን ፤ እንግዲያውስ እኛም
እንደ ሸክም የሆነብንን ነገር ሁሉ በእኛ ላይ
የተጣበቀውን ኃጢአት አስወግደን ፥ በፊታች
ንም ያለውን ሩጫ በትዕግሥት በመጽናት እን
ሩጥ ። 2 የምንሮጠውም የእምነታችን አመን
ጪና ፈጻሚ የሆነውን ኢየሱስን በመመልከት
ነው ፤ ወደ ፊት በሚያገኘው ደስታ ምክንያት
በመስቀል ላይ የመሞትን ውርደት ከምንም
ሳይቈጥር ፥ የመስቀልን መከራና ሞት ታገሠ ፤
በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝም ተቀመጠ ።
3 እንግዲህ ችላ ሳትሉ እንድትሠሩና ተስፋ
እንዳትቈርጡ ፥ ይህን ሁሉ የኃጢአተኞችን
ተቃውሞ የታገሠውን ኢየሱስን ተመልከቱ ።
4 እናንተ ከኃጢአት ጋር በመታገል ገና ደም
እስከማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም ። 5 እግ
ዚአብሔር እንደ ልጆቹ አድርጎ እንዲህ ሲል
የመከራችሁን ረስታችኋል ፥

"ልጄ ሆይ! የእግዚአብሔርን ተግሣጽ
አታቃልል ፤
በቀጣህም ጊዜ ተስፋ አትቍረጥ ፤
6 ምክንያቱም እግዚአብሔር
የሚወድደውን ይገሥጻል ፤
እንደ ልጅ አድርጎ የሚያየውንም
ይቀጣል ።"

7 እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ስለሚቈጥራችሁ
ቅጣትን ታገሡ ፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን
ነው? 8 ልጆች የሆኑ ሁሉ የሚቀበሉትን ቅጣት
እናንተ ካልተቀበላችሁ ፥ ዲቃሎች እንጂ
ልጆች አይደላችሁም ። 9 ከዚህም በቀር እኛ
ሁላችን የሚቀጡን የሥጋ አባቶች ነበሩን ፤ እና
ከብራቸውም ነበር ፤ ታዲያ በሕይወት ለመኖር
ለመንፈሳዊ አባታችን በይበልጥ መታዘዝ እን
ዴት አይገባንም? 10 እነርሱ መልካም መስሎ
እንደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ቀጥተውናል ፤
እርሱ ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን
ለጥቅማችን ይቀጣናል ። 11 ቅጣት ሁሉ በወቅቱ
የሚያሳዝን እንጂ የሚያስደስት አይመስልም ፤
በኋላ ግን ለተለማመዱት ሰዎች ፥ ሰላም የሞላበ
ትን የጽድቅ ሕይወት ያስገኝላቸዋል ።

### ምክርና ማስጠንቀቂያ

12 ስለዚህ የዛሉትን እጆቻችሁንና የደከሙ
ትን ጕልበቶቻችሁን አበርቱ ። 13 አንካሳ የሆ
ነው እንዲፈወስ እንጂ ከቦታው ወጥቶ እንዳይ
ናጋ ለእግራችሁ የቀና መንገድ አድርጉ ።
14 ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ፤ በቅድስ
ናም ለመኖር ትጉ ፤ ምክንያቱም ያለ ቅድስና
ማንም እግዚአብሔርን ማየት አይችልም ።
15 ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እን
ዳይጐድልበት ተጠንቀቁ ፤ እንዲሁም ምንም
መራራ ሥር በመካከላችሁ እንዳይበቅልና እንዳ
ያስቸግራችሁ ፥ ብዙዎችንም እንዳያረክስ ተጠ
ንቀቁ ። 16 ሴሰኛ የሆነ ወይም ለአንድ ጊዜ
ምግብ ብሎ ብኵርናውን እንደሸጠ እንደ
ዔሳው ነውረኛ የሆነ ሰው እንዳይገኝ ተጠን
ቀቁ ። 17 በኋላም ዔሳው በረከትን እንደገና ለመ
ቀበል በፈለገ ጊዜ ይህን በረከት እንደተከለከለ
ታውቃላችሁ ፤ እያለቀሰ እንኳ ያንን በረከት
ተግቶ ቢፈልግም ሊያገኘው አልቻለም ። ምክን
ያቱም የቀድሞውን ስሕተት በምንም መንገድ
ሊያስተካክል አልቻለም ።
18 እናንተ በእጅ ወደሚዳሰሰው ወይም ወደ
ሚቃጠለው ወደ ሲና ተራራ አልደረሳችሁም ፤
ወደ ጭጋጉ ፥ ወደ ጨለማውም ፥ ወደ ዐውሎ
ነፋሱም ፥ 19 የመለከት ድምፅ ወይም የሚነገ
ረው ቃል ወደሚሰማበትም አልደረሳችሁም ፤
ያንን ቃል የሰሙ ሰዎች "ከእንግዲህ ወዲህ
ሌላ ቃል አይነገረን" በማለት እስከመለመን
ደርሰዋል ። 20 ምክንያቱም ፥

“እንስሳ እንኳ ተራራውን ቢነካ ፥
በድንጋይ ተወግሮ ይሙት”
የሚለው ትእዛዝ ስለከበደባቸው ሊሸከሙት
አልቻሉም ። 21 የታየው ድርጊት እጅግ አስፈሪ
ከመሆኑ የተነሣ ሙሴ እንኳ
“እኔ ፈራሁ ፥ ተንቀጠቀጥሁ” አለ ።
22 እናንተ ግን ወደ ጽዮን ተራራ ቀር
ባችኋል ፤ እርስዋ የሕያው እግዚአብሔር ከተማ
የሆነችው ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ናት ፤ በደስታ
ወደተሰበሰቡት ፥ በሚሊዮን ወደሚቈጠሩት
መላእክት ቀርባችኋል ። 23 ስማቸው በሰማይ
ወደተጻፈው ፥ የቤተ ክርስቲያን የበኵር ልጆች
ወደሆኑት ወደ አማኞች ጉባኤ ፥ የሁሉ ፈራጅ
ወደሆነው አምላክና ፍጹምነትን ወዳገኙት የጻ
ድቃን ነፍሳት ቀርባችኋል ። 24 የአዲስ ኪዳን
ማእከላዊ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ ፥ ከአቤል
ደም ይልቅ በተሻለ ሁኔታ ወደሚናገረውና ለማ
ንጻት ወደተረጨው ደሙም ቀርባችኋል ።
25 ያንን የሚናገረውን እምቢ እንዳትሉ ተጠ
ንቀቁ ፤ ምክንያቱም እነዚያ ከምድር ሲናገራ
ቸው እምቢ ያሉት ካላመለጡ ፥ ታዲያ ከሰማይ
ከሚናገረን ብንርቅ እንዴት እናመልጣለን!
26 በዚያን ጊዜ ቃሉ ምድርን አናውጦአል ፤
አሁን ግን “ምድርን ብቻ ሳይሆን አንድ ጊዜ
ደግሜ ሰማይን ጭምር አናውጣለሁ” በማለት
ቃል ገብቶአል ። 27 ይህ “አንድ ጊዜ ደግሜ”
የሚለው ቃል የሚያመለክተው የማይናወጡ ነገ
ሮች ጸንተው እንዲኖሩ ፥ የሚናወጡ ወይም
የተፈጠሩ ነገሮች መወገዳቸውን ነው ።
28 እንግዲህ እኛ የማትናወጠውን መንግሥት
ስለምንወርስ እግዚአብሔርን እናመስግን ፤ ደስ
በሚሰኝበት ሁኔታም በአክብሮትና በፍርሃት
እናገልግለው ። 29 ምክንያቱም አምላካችን የሚ
ያቃጥል እሳት ነው ።

## ምዕራፍ 13

### እግዚአብሔርን እንዴት ማስደሰት እንደሚገባ

1 ሁልጊዜ የወንድማማችነት ፍቅር ይኑራ
ችሁ ፤ 2 እንግዳ ተቀብሎ ማስተናገድን አት
ርሱ ፤ ምክንያቱም እንደዚህ እንግዶችን እየተቀ
በሉ በማስተናገድ አንዳንድ ሰዎች ሳያውቁ
መላእክትን ተቀብለው አስተናግደዋል ። 3 ከእነ
ርሱ ጋር አብራችሁ እንደ ታሰራችሁ ያህል
ሆናችሁ እስረኞችን አስታውሱ ፤ እናንተም
እንደ እነርሱ መከራ የምትቀበሉ ያህል ሆና
ችሁ መከራ የሚቀበሉትን አስቡ ።
4 ጋብቻ በሁሉ ዘንድ የተከበረ ይሁን ፤ ባልና
ሚስት ታማኝነትን በማጕደል ጋብቻን አያር
ክሱ ፤ ምክንያቱም ሴሰኞችንና አመንዝሮችን
እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል ።
5 ከገንዘብ ፍቅር ራቁ ፤ ያላችሁ ይብቃችሁ ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር “አልጥልህም ፥ አል
ተውህም” ብሎአል ። 6 ስለዚህ በመተማመን ፥
“እግዚአብሔር ረዳቴ ነው ፥ አልፈራም ፤
ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?”
እንላለን ።
7 የእግዚአብሔርን ቃል በመጀመሪያ የነገሩ
አችሁን መሪዎቻችሁን አትርሱ ፤ አኗኗራቸው
ንና ሥራቸውን በማስታወስ እምነታቸውን
ተከተሉ ። 8 ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም
ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው ፤ አይለወጥም ።
9 ባልተለመደ በልዩ ልዩ ዐይነት ትምህርት
አትማረኩ ፤ ልባችን የመብል ሥነ ሥርዓቶችን
በመጠበቅ ሳይሆን በጸጋ ቢጸና መልካም
ነው ፤ ምክንያቱም ይህን የምግብ ሥነ ሥር
ዓት የተከተሉ ሰዎች ምንም አልተጠቀ
ሙም ።
10 እኛ መሠዊያ አለን ፤ ሆኖም በድንኳኒቱ
ውስጥ የሚያገለግሉ ካህናት በመሠዊያው ላይ
ካለው ምግብ ወስደው መብላት አይፈቀድላቸ
ውም ። 11 የአይሁድ ሊቀ ካህናት የኃጢአት
ይቅርታን የሚያስገኘውን የእንስሳት ደም ይዞ
ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል ፤ የእንስሳቱ በድን
ግን ከሰፈሩ ውጭ ይቃጠላል ፤ 12 እንዲሁም
ኢየሱስ ሕዝቡን በገዛ ራሱ ደም ለመቀደስ ከከ
ተማው በር ውጭ መከራን ተቀበለ ። 13 እኛም
ከሰፈር ወጥተን ወደ እርሱ እንሂድ ፤ የውርደ
ቱም ተካፋዮች እንሁን ። 14 ምክንያቱም እኛ
ገና የምትመጣውን ከተማ እንጠባበቃለን እንጂ
ጸንታ የምትኖር ከተማ በዚህ ምድር የለች
ንም ። 15 እንግዲህ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይ
ነት የምስጋና መሥዋዕት ዘወትር ለእግዚአብ
ሔር እናቅርብ ፤ ይህም ስለ ስሙ በሚመሰክ
ሩት ከንፈሮች የሚቀርብ የምስጋና መሥዋዕት
ነው ። 16 መልካም ነገር ማድረግንና ያላችሁን
ነገር ለሌሎች ማካፈልን አትርሱ ፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው እንዲህ ያለው
መሥዋዕት ነው ።
17 ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ ፤ በሥልጣናቸውም
ሥር ሁኑ ፤ ምክንያቱም እነርሱ የሚጠየቁበት
ኀላፊነት ስላለባቸው ስለ ነፍሳችሁ ጉዳይ ይተ
ጋሉ ፤ እናንተ ብትታዘዙአቸው ፥ እነርሱ ሥራ
ቸውን በደስታ ያከናውናሉ ፤ ያለበለዚያ ሥራቸ
ውን በሐዘን ይሠራሉ ፤ ይህም እናንተን የሚጠ
ቅም አይሆንም ።
18 ጸልዩልን ፤ ንጹሕ ኅሊና እንዳለን እርግ
ጠኞች ነን ፤ በሁሉም መንገድ በመልካም

12፥21 ፦ ዘጸ. 9፥19 ። 12፥24 ፦ ዘፍ. 4፥10 ። 12፥25 ፦ ዘጸ. 20፥22 ። 12፥26 ፦ ሐጌ 2፥6 ። 12፥29 ፦ ዘዳ. 4፥24 ።
13፥2 ፦ ዘፍ. 18፥1-8 ፤ 19፥1-3 ። 13፥5 ፦ ዘዳ. 31፥6 ፥8 ፤ ኢያሱ 1፥5 ። 13፥6 ፦ መዝ. 118፥6 ። 13፥11 ፦ ዘሌ. 16፥27 ።



ለመኖር እንመኛለን ፤ 19 ይልቁንም ተግታችሁ
እንድትጸልዩ አጥብቄ የምለምናችሁ በፍጥነት
ወደ እናንተ እንድመለስ ነው ።

### ጸሎት

20 በዘላለማዊ ኪዳን ደም የበጎች ታላቅ
እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሞት ያስነ
ሣው የሰላም አምላክ ፥ 21 ፈቃዱን ለመፈጸም
እንድትበቁ በመልካም ነገር ሁሉ ያስታጥቃ
ችሁ ፤ ደስ የሚያሰኘውንም በኢየሱስ ክርስቶስ
አማካይነት በእኛ ያድርግ ፤ ለኢየሱስ ክርስቶ
ስም ለዘላለም ክብር ይሁን ፤ አሜን ።

### ማጠቃለያ

22 ወንድሞች ሆይ! ይህ የጻፍኩላችሁ መል
እክት አጭር ስለሆነ ፥ ይህን የምክር ቃሌን በት
ዕግሥት እንድትቀበሉ እለምናችኋለሁ ። 23 ወን
ድማችን ጢሞቴዎስ ከእስር ቤት እንደወጣ እን
ድታውቁ እወዳለሁ ፤ በቶሎ ወደዚህ ከመጣ
ከእርሱ ጋር ወደ እናንተ መጥቼ አያችኋለሁ ።
24 ለመሪዎቻችሁና ለቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ
አቅርቡልኝ ፤ ከኢጣሊያ መጥተው ከእኔ ጋር
ያሉ ክርስቲያኖች ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።
25 ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን ።

# የያዕቆብ መልእክት

## መግቢያ

ይህ የያዕቆብ መልእክት ለዕለታዊ ኑሮ መመሪያ የሚሆኑ አሳቦችን ያዘለ ሲሆን ፥ የተጻፈውም “በዓለም ሁሉ ለተበተኑ ሕዝበ እግዚአብሔር” ነው ፤ ጸሐፊው ጥበብን በተግባር ስለምናውልበት ዘዴና ለክርስቲያናዊ አቀባበልና ጠባይ መመሪያ የሚሆኑ ነገሮችን ግልጥ በሆኑ ሥዕላዊ አነጋገሮች ያቀርባል ፤ ስለ ድኽነትና ስለ ሀብት ፥ ስለ ፈተና ፥ ስለ መልካም ጠባይ ፥ ስለ ቅንዓት ፥ ስለ እምነትና በጎ ምግባር ፥ ስለ ምላስ ጠቃሚነትና ጐጂነት ፥ ስለ ጥበብ ፥ እርስ በርስ ስለ መጣላት ፥ ስለ ትዕቢትና ስለ ትሕትና ፥ በሌሎች ላይ ስለ መፍረድ ፥ ስለ ትምክሕት ወይም ስለ ጕራ ፥ ስለ ትዕግሥትና ስለ ጸሎት ክርስቲያኖች ሲኖራቸው ስለሚገባ አመለካከት በመዘርዘር ጽፎአል ።

መልእክቱ በክርስትና ሕይወት እምነት በተግባር ስለሚተረጐምበት ሁኔታ አጕልቶ ያሳያል ።

---

## ምዕራፍ 1

1 በዓለም ሁሉ ለተበተኑ ለዐሥራ ሁለቱ ነገ
ዶች ፥ የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስ
ቶስ አገልጋይ ከሆነው ከያዕቆብ የተላከ መልእ
ክት ፤
ሰላም ለእናንተ ይሁን ።

### ትዕግሥት ፥ እምነት ፥ ጥበብ

2 ወንድሞቼ ሆይ! ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባ
ችሁ በጣም ደስ ይበላችሁ ። 3 ምክንያቱም እም
ነታችሁ ሲፈተን በትዕግሥት ትጸናላችሁ ።
4 በትዕግሥት መጽናታችሁ ፥ ምንም ሳይጐድል
ባችሁ ፍጹምና ሙሉ እንድትሆኑ የሚያበቃ
ችሁ ይሁን ። 5 ከእናንተ መካከል ጥበብ ዩጐደ
ለው ሰው ቢኖር ፥ እግዚአብሔርን ይለምን ፤
እግዚአብሔርም ይሰጠዋል ፤ ምክንያቱም እርሱ
ምንም ሳይከለክል ለሁሉም በልግሥና የሚሰጥ
ቸር አምላክ ነው ። 6 ነገር ግን ሰው ምንም ሳይ
ጠራጠር በእምነት ይለምን ፤ የሚጠራጠር ሰው
በነፋስ የተገፋና የተናወጠ የባሕር ማዕበል
ይመስላል ። 7 እንዲህ ዐይነቱ ሰው ከእግዚአብ
ሔር ምንም ነገር የሚያገኝ አይምሰለው ።
8 ምክንያቱም ሁለት አሳብ ስላለውና በመንገ
ዱም ስለሚያወላውል ነው ።

### የድኻ ሰውና የሀብታም ሰው ደስታ

9 በኑሮው ዝቅተኛ የሆነ ወንድም እግዚአብ
ሔር ከፍ ስለሚያደርገው ደስ ይበለው ። 10 በኑ
ሮው ቁና ያለ ወንድም እግዚአብሔር በኑሮው
ዝቅ ቢያደርገውም ደስ ይበለው ፤ ምክንያቱም
የሰው ሀብት እንደ ሣር አበባ ይረግፋል ።

1፥1 ፦ ማቴ. 13፥55 ፤ ማር. 6፥3 ፤ ሐ.ሥ. 15፥13 ፤ ገላ. 1፥19 ። 1፥10-11 ፦ ኢሳ. 40፥6-7 ።

11 ፀሐይ ከሙቀቱ ጋር ሲወጣ ሣሩን ያደርቀ
ዋል፤ አበባውም ይረግፋል፤ ውበቱም ይጠ
ፋል፤ እንዲሁም ሀብታም ሰው በሥራው ሲባ
ክን ይጠፋል።

### በሰው ስለሚደርስ ፈተና

12 ፈተናን ታግሦ የሚጸና ሰው የተባረከ
ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ
መሠረት ለወዳጆቹ የሚሰጠውን የሕይወት አክ
ሊል ይቀበላል። 13 ሰው በሚፈተንበት ጊዜ
“እግዚአብሔር ፈተነኝ” አይበል፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔር በክፉ ነገር አይፈተንም፤ እንዲያ
ውም እርሱ ማንንም አይፈትንም፤ 14 ነገር ግን
እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በገዛ ራሱ ምኞት
ሲሳብና ሲታለል ነው። 15 ከዚህ በኋላ ምኞት
ስትፀንስ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም
ስታድግ ሞትን ትወልዳለች።
16 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ! አትታ
ለሉ! 17 መልካም ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ
ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህም የሚመጣው እንደ
ጥላ መዘዋወር ወይም መለዋወጥ ከሌለበት የብ
ርሃን ሁሉ አባት ከሆነው ከእግዚአብሔር
ነው። 18 እግዚአብሔር የፍጥረቱ ሁሉ መጀመ
ሪያ እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል ወለ
ደን።

### የሰሙትን በሥራ ላይ ማዋል

19 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ! ይህን አት
ርሱ፤ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገ
ርና ለቍጣም የዘገየ ይሁን። 20 ምክንያቱም
የሰው ቍጣ፤ የእግዚአብሔር ጽድቅ በሰው
ሕይወት ውስጥ ፍጹም እንዲሆን አያደርግም።
21 ስለዚህ ርኵሰትንና የክፋትንም ብዛት ሁሉ
አስወግዳችሁ፤ እግዚአብሔር በልባችሁ የተከለ
ውንና ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን ቃል በት
ሕትና ተቀበሉ።
22 ቃሉን በሥራ ላይ የምታውሉ ሁኑ እንጂ
ራሳችሁን እያታለላችሁ ሰሚዎች ብቻ አት
ሁኑ። 23 ቃሉን ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውለው
ሰው፣ የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት እንደሚያይ
ሰው ነው፤ 24 ምክንያቱም ይህ ሰው ፊቱን በመ
ስተዋት ካየ በኋላ ይሄዳል፤ እንዴት እንደሆ
ነም ወዲያውኑ ይረሳዋል። 25 ነገር ግን ነፃ
የሚያወጣውን ፍጹም ሕግ ተመልክቶ በእርሱ
የሚጸና፣ እርሱንም ሰምቶ መርሳት ሳይሆን፣
በሥራ ላይ የሚያውለው ሰው በሥራው የተባ
ረከ ነው።
26 ምላሱን ሳይቈጣጠር እግዚአብሔርን አመ
ልካለሁ የሚል ሰው ራሱን ያታልላል፤ ሃይማኖ
ቱም ከንቱ ነው። 27 በእግዚአብሔር አብ ፊት
ነውር የሌለበትና ንጹሕ ሃይማኖት “አባትና
እናት የሞቱባቸውን ልጆች፣ እንዲሁም ባሎቻ
ቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በችግራቸው መር
ዳት፣ ራስንም ከዓለም ርኵሰት መጠበቅ
ነው።”

## ምዕራፍ 2
### ድኻን መናቅ አይገባም

1 ወንድሞቼ ሆይ! በክብር ጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስ የምታምኑ ሆናችሁ፣ አንዱ ከሌላው
ይበልጣል በማለት በሰው መካከል አድልዎ
አታድርጉ። 2 ለምሳሌ ሁለት ሰዎች ወደምትሰ
በሰቡበት ቦታ ይመጣሉ፤ አንደኛው በጣቱ የወ
ርቅ ቀለበት ያደረገና የሚያምር ጌጠኛ ልብስ
የለበሰ ሀብታም ነው፤ ሌላው ያደፈ አሮጌ
ልብስ የለበሰ ድኻ ነው፤ 3 የሚያምር ጌጠኛ
ልብስ የለበሰውን ሰው በማክበር “በዚህ በመል
ካሙ ቦታ ተቀመጥ” ትሉታላችሁ። ድኻውን
ግን “አንተስ እዚያ ቁም፤ ወይም በእግሬ ሥር
ተቀመጥ” ትሉታላችሁ፤ 4 ታዲያ በዚህ ዐይነት
በመካከላችሁ ልዩነት እንደምታደርጉና የአድ
ልዎ ፍርድ እንደምትፈርዱ አይታያችሁምን?
5 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ! ስሙ፤ እግ
ዚአብሔር በእምነት ሀብታሞች እንዲሆኑና
ለሚወድዱት ተስፋ የሰጣቸውን መንግሥት እን
ዲወርሱ የዚህን ዓለም ድኾች አልመረጠምን?
6 እናንተ ግን ድኾችን ትንቃላችሁ፤
የሚጨቍኗችሁና ወደ ፍርድ ቤት የሚጐትቷ
ችሁስ ሀብታሞች አይደሉምን? 7 የምትጠሩበ
ትን ክቡር ስም የሚሰድቡስ እነርሱ አይደሉ
ምን?
8 “ሰውን እንደራስህ አድርገህ ውደድ”
ተብሎ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን መንግሥት
ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ።
9 በሰዎች መካከል ልዩነት ብታደርጉ ግን ኃጢ
አት ትሠራላችሁ፤ ሕግን በመተላለፋችሁም
ትወቀሳላችሁ። 10 ሰው ከትእዛዞች አንዱን አፍ
ርሶ የቀሩትን ሁሉ ቢፈጽም እንኳ ሁሉንም
እንዳፈረሰ ይቈጠራል። 11 ምክንያቱም “አታመ
ንዝር” ያለው ጌታ፣ እንዲሁም “አትግደል”
ብሎአል፤ ባታመነዝርም እንኳ ከገደልህ ሕግን
አፍርሰሃል። 12 ንግግራችሁም፣ ሥራችሁም በነ
ፃነት ሕግ የሚፈረድባችሁ መሆናችሁን በማ
ሰብ ይሁን። 13 ምክንያቱም የእግዚአብሔር
ፍርድ ምሕረት ለማያደርግ ሰው ምሕረት አያ
ደርግም፤ ሆኖም ምሕረት ፍርድን ያሸንፋል።

### እምነትና ሥራ

14 ወንድሞቼ ሆይ! ሰው እምነት አለኝ
ቢል፣ ነገር ግን እምነቱን በመልካም ሥራ ባይ
ገልጥ ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው

2፥8 ፦ ዘሌ. 19፥18። 2፥11 ፦ ዘጸ. 20፥13-14፤ ዘዳ. 5፥17-18።



ይችላልን? 15 ለምሳሌ የሚለብሱትና የሚመግ
ቡት የሌላቸው ወንድሞችና እኅቶች ቢኖሩ፣
16 እናንተ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር
ሳትሰጡአቸው “በሰላም ሂዱ! ይሙቃችሁ!
ጥገቡ!” ብትሉአቸው ምን ይጠቅማቸዋል?
17 ከመልካም ሥራ የተለየ እምነት የሞተ
ነው።
18 ነገር ግን “አንተ ‘እምነት አለኝ’ ብለህ
ብትመካ፣ እኔም መልካም ሥራ አለኝ” የሚል
ቢኖር፣ “እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፤
እኔም በሥራዬ እምነቴን አሳይሃለሁ” እለዋ
ለሁ። 19 አንተ “አንድ እግዚአብሔር አለ ብለህ
ታምናለህ፤” ይህም መልካም ነው፤ ማመንማ
አጋንንትም ያምናሉ፤ በፍርሃትም ይንቀጠቀ
ጣሉ። 20 አንተ ሞኝ! ከሥራ የተለየ እምነት
ፍሬቢስ[1*] መሆኑን ታያለህን? 21 አባታችን አብ
ርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ላይ ለእግ
ዚአብሔር መሥዋዕት እንዲሆን ባቀረበው
ጊዜ፣ በሥራ አልጸደቀምን? 22 ስለዚህ እምነቱ
ከሥራው ጋር አብሮ እንደነበርና እምነቱም
በሥራ ፍጹም እንደሆነ ታያለህን? 23 በመጽሐ
ፍም “አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ እምነ
ቱም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት” የተባለው ቃል
ተፈጸመ፤ በዚህ ሁኔታ አብርሃም የእግዚአብ
ሔር ወዳጅ ተባለ። 24 እንግዲህ ሰው የሚጸድ
ቀው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራም ጭምር
መሆኑን ታያለህ።
25 አመንዝራይቱ ረዓብ የእስራኤልን መልእ
ክተኞች በቤትዋ በተቀበለች ጊዜና በሌላም
መንገድ እንዲሄዱ ባደረገቻቸው ጊዜ እርስዋስ
በሥራዋ ጸድቃ የለምን?
26 ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ ነው፤ እንዲ
ሁም ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።

## ምዕራፍ 3
### ምላስን ስለመቈጣጠር

1 ወንድሞቼ ሆይ! እኛ አስተማሪዎች የሆ
ንን የባሰ ፍርድ እንደምንቀበል ታውቃላችሁና
ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ።
2 ምክንያቱም እኛ ሁላችን ብዙ ጊዜ እንሳሳታ
ለን፤ በንግግሩ የማይሳሳት፣ እርሱ ሰውነቱን
መቈጣጠር የሚችል ፍጹም ሰው ነው። 3 ፈረስ
እንዲታዘዝልን በአፉ ውስጥ ልጓም እናገባለን፤
ፈረሱንም ወደምንፈልገው ቦታ እንመራዋለን።
4 መርከብ ምንም ትልቅ ቢሆንና በትልቅ ነፋ
ስም የሚገፋ ቢሆን፣ የመርከቡ ነጂ በትንሽ
መሪ ወደ ፈለገው ቦታ ይነዳዋል። 5 እንዲሁም
ምላስ ትንሽ የአካል ክፍል ስትሆን በታላላቅ
ነገሮች ትመካለች፤ ትልቅ ጫካ የሚቃጠለው
በትንሽ እሳት ነው። 6 ምላስም እንደ እሳት
ናት፤ ምላስ በአካል ክፍሎቻችን መካከል የም
ትገኝ ክፉ ዓለም ናት፤ ሥጋችንንም ሁሉ ታረ
ክሳለች፤ እንደ ገሃነመ እሳት ሰውነታችንን
ሁሉ ታቃጥላለች። 7 የምድር አውሬዎችና
ወፎች፣ በመሬት የሚሳቡና በባሕር የሚንቀሳ
ቀሱ ፍጥረቶች ሁሉ በሰው ሊገሩ ይችላሉ፤
ደግሞም ተገርተዋል። 8 ነገር ግን ምላስን
ሊገራ የሚችል ማንም የለም፤ የሚገድል
መርዝ የሞላባትና ዕረፍት የሌላት ክፉ ነገር
ናት። 9 በእርስዋ አባታችንን እግዚአብሔርን
እናመሰግናለን፤ እንዲሁም በእርስዋ በእግዚአብ
ሔር አምሳል የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማ
ለን። 10 ከአንድ አፍ ምስጋናና እርግማን ይወ
ጣሉ፤ ወንድሞቼ ሆይ! ይህ ሊሆን አይገባም።
11 ከአንድ ምንጭ ጣፋጭ ውሃና መራራ ውሃ
ሊወጣ ይችላልን? 12 ወንድሞቼ ሆይ! የበለስ
ዛፍ የወይራ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን? ወይስ
የወይን ተክል የበለስ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን?
እንዲሁም ከመራራ ውሃ ጣፋጭ ውሃ ሊገኝ
ይችላልን?

### ሰማያዊና ምድራዊ ጥበብ

13 ከእናንተ መካከል ጥበበኛና አስተዋይ
ሰው ማንነው? በጥበብና በትሕትና የፈጸመውን
ሥራ በመልካም አኗኗሩ ያሳይ። 14 ነገር ግን
መራራ ቅንአትና ራስ ወዳድነት በልባችሁ
ቢኖር አትታበዩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ።
15 ምክንያቱም እንዲህ ዐይነቱ ጥበብ የሚገኘው
ከዓለም፣ ከሥጋ፣ ከሰይጣን ነው እንጂ ከእግዚ
አብሔር አይደለም። 16 ቅንአትና ራስ ወዳድ
ነት ባሉበት ስፍራ፣ ሁከትና ክፉ ሥራ ሁሉ
ይኖራሉ። 17 ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሚገ
ኘው ጥበብ በመጀመሪያ ንጹሕ ነው፤ ቀጥሎም
ሰላም ወዳድ፣ ደግ፣ ታዛዥ፣ ምሕረት አድ
ራጊ፣ ጥሩ ፍሬ የሞላበት፣ አድልዎና ግብዝ
ነት የሌለበት ነው። 18 ሰላም ወዳድ ሰዎች ሰላ
ምን ዘርተው የጽድቅን ፍሬ ይሰበስባሉ።

## ምዕራፍ 4
### የዓለምን ክፋት አለመውደድ

1 በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ
ከየት የመጣ ነው? በሰውነታችሁ ውስጥ ከሚዋ
ጋው ከሥጋዊ ምኞታችሁ አይደለምን? 2 የምት
ፈልጉትን ነገር ማግኘት ሲያቅታችሁ ሰውን
ትገድላላችሁ፤ በብርቱ ተመኝታችሁ ማግኘት
ሲያቅታችሁ ትጣላላችሁ፤ ትጋደላላችሁ። ስለ
ማትጸልዩ የምትፈልጉትን ነገር አታገኙም።

[1*] 2፥20 ፍሬቢስ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “የሞተ” ይላሉ።
2፥21 ፦ ዘፍ. 22፥1-14። 2፥23 ፦ ዘፍ. 15፥6፤ 2ዜ.መ. 20፥7፤ ኢሳ. 41፥8። 2፥25 ፦ ኢያሱ 2፥1-21። 3፥9 ፦ ዘፍ. 1፥26።

[3] ብትጸልዩም ፣ የጸሎታችሁን መልስ የማታገ
ኙት ፣ የለመናችሁትን ነገር በሥጋዊ ደስታ ላይ
ለማዋል በክፉ አሳብ ስለምትጸልዩ ነው ። [4] እና
ንተ ከዳተኞች! ዓለምን የሚወድድ የእግዚአብ
ሔር ጠላት መሆኑን አታውቁምን? እንግዲህ
ዓለምን የሚወድድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት
መሆኑ ነው ። [5] ደግሞስ መጽሐፍ "እግዚአብ
ሔር በውስጣችሁ ያሳደረው መንፈስ ለእርሱ
ብቻ እንድንሆን በብርቱ ይመኛል" ያለው በከ
ንቱ ነውን? [6] ሆኖም መጽሐፍ "እግዚአብሔር
ትዕቢተኞችን ይቃወማል ፤ ለትሑቶች ግን
ጸጋን ይሰጣል" ስለሚል ፣ እግዚአብሔር የሚሰ
ጠው ጸጋ ከሁሉም ይበልጣል ።
[7] ስለዚህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤ ዲያብሎ
ስን ግን ተቃወሙት ፤ ከእናንተም ይሸሻል ።
[8] ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ፤ እርሱም ወደ እና
ንተ ይቀርባል ፤ እናንተ ኃጢአተኞች እጆቻች
ሁን አጽዱ ፤ እናንተ ወላዋዮች ልባችሁን
አጥሩ ። [9] ተጨነቁ ፤ እዘኑ ፤ አልቅሱ ፤ ሳቃችሁ
ወደ ለቅሶ ፣ ደስታችሁ ወደ ሐዘን ይለወጥ ።
[10] በጌታ ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ ፤ እርሱም
ከፍ ያደርጋችኋል ።

### በሰው ላይ አለመፍረድ

[11] ወንድሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተ
ማሙ ፤ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚ
ፈርድ ሕግን ያማል ፤ በሕግም ላይ ይፈርዳል ፤
በሕግም ላይ ብትፈርድ ፣ ፈራጅ መሆንህ ነው
እንጂ ሕግን ፈጻሚ አይደለህም ። [12] ሕግን የሚ
ሰጥና የሚፈርድ አንድ እግዚአብሔር ብቻ
ነው ፤ ሊያድንም ሊያጠፋም የሚችል እርሱ
ብቻ ነው ፤ ታዲያ በሰው ላይ የምትፈርድ
አንተ ማን ነህ?

### ስለ ትምክሕት
### የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

[13] እናንተ "ዛሬ ወይም ነገ ወደ ሌላ አገር
ሄደን እዚያ አንድ ዓመት እንቀመጣለን ፤ ነግደ
ንም እናተርፋለን" የምትሉ ተጠንቀቁ ።
[14] ምክንያቱም ነገ የሚሆነውን አታውቁም ፤
ሕይወታችሁ ምንድን ነው? ለአንድ አፍታ
ታይቶ በኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ
እኮ ። [15] ይልቁንስ እናንተ ማለት የሚገባችሁ
"እግዚአብሔር ቢፈቅድና ብንኖር ይህን ወይም
ያን እናደርጋለን" ነው ። [16] እናንተ ግን ይህን
በማለት ፈንታ በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ ፤ እን
ዲህ ያለው ትምክሕት ሁሉ ክፉ ነው ።
[17] እንግዲህ መልካም ነገር ማድረግን እያ
ወቀ የማያደርግ ሰው ፣ አለማድረጉ ኃጢአት
ይሆንበታል ።

## ምዕራፍ 5
### ለሀብታሞች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

[1] አሁን ደግሞ እናንተ ሀብታሞች! ኑ አድ
ምጡ ፤ አሠቃቂ መከራ ስለሚመጣባችሁ እየጮ
ኻችሁ አልቅሱ ። [2] ሀብታችሁ ሁሉ በስብሶ ተበ
ላሽቶአል ፤ ልብሳችሁንም ብል በልቶታል ።
[3] ወርቃችሁና ብራችሁ ዝጐአል ፤ ዝገቱም ምስ
ክር ይሆንባችኋል ፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት
ይበላዋል ፤ ለእነዚህ የመጨረሻ ቀኖች ብዙ
ሀብት አከማችታችኋል ። [4] ይሁን እንጂ በእርሻ
ችሁ ሲያጭዱ ለዋሉት ሠራተኞች ዋጋቸውን
ስላልከፈላችሁ እነሆ የተቃውሞ ጩኸታቸው
ይሰማል ፤ የመከር ሰብሳቢዎቻችሁንም ጩኸት
ኀያሉ እግዚአብሔር ሰምቶአል ። [5] በምቾትና
በደስታ በመኖር ሰውነታችሁን ለዕርድ እንደተዘ
ጋጀ ሰንጋ አወፍራችኋል ። [6] ጻድቁን በሐሰት
ፈረዳችሁበት ፤ ገደላችሁትም ፤ እርሱም አይቃ
ወማችሁም ።

### የጌታን ዳግመኛ መምጣት
### በትዕግሥት መጠበቅ

[7] ወንድሞቼ ሆይ! እንግዲህ የጌታን መም
ጣት በትዕግሥት ጠብቁ ፤ ገበሬ የመጀመሪያው
ንና የኋለኛውን ዝናብ እስከሚያገኝ እየታገሠ
መልካሙን የመሬት ፍሬ ይጠባበቃል ። [8] እናን
ተም እንዲሁ ታገሡ ፤ የጌታ መምጫ ጊዜ ስለ
ተቃረበ በተስፋ ጽኑ ።
[9] ወንድሞቼ ሆይ! በእናንተ ላይ እንዳይፈረ
ድባችሁ እርስ በርሳችሁ አትጨቃጨቁ ፤ እነሆ
ፈራጁ የሚመጣበት ጊዜ ደርሶአል ። [10] ወንድ
ሞቼ ሆይ! በጌታ ስም የተናገሩት ነቢያት መከ
ራን በትዕግሥት በመቀበል ምሳሌ መሆናቸውን
ዕወቁ ። [11] ደግሞም በትዕግሥት የጸኑትን "የተ
ባረኩ ናቸው" እንላቸዋለን ፤ ኢዮብ እንዴት
እንደታገሠ ሰምታችኋል ። እግዚአብሔርም
በመጨረሻ ያደረገለትን መልካም ነገር አይ
ታችኋል ፤ በዚህም እግዚአብሔር መሐሪና ርኅ
ሩኅ መሆኑን ተመልክታችኋል ።
[12] ወንድሞቼ ሆይ! ከሁሉ በፊት በሰማይ
ወይም በምድር ወይም በሌላ በምንም ነገር
አትማሉ ፤ ንግግራችሁ አዎ ከሆነ በእውነት
አዎ ይሁን ፤ አይደለም ከሆነም በእውነት አይ
ደለም ይሁን ፤ እንዲህ ካልሆነ ግን ይፈረድ
ባችኋል ።
[13] ከእናንተ መካከል ችግር የደረሰበት ሰው
ቢኖር ይጸልይ ፤ ደስ ያለው ሰውም ቢኖር እግ
ዚአብሔርን በማመስገን ይዘምር ። [14] ከእናንተ
መካከል የታመመ ሰው ቢኖር የቤተ ክርስቲያን

4፥6 ፦ ምሳ. 3፥34 ። 4፥13-14 ፦ ምሳ. 27፥1 ። 5፥2-3 ፦ ማቴ. 6፥19 ። 5፥4 ፦ ዘዳ. 24፥14-15 ።
5፥11 ፦ ኢዮብ 1፥21-22 ፣ 2፥10 ፣ መዝ. 103፥8 ። 5፥12 ፦ ማቴ. 5፥34-37 ። 5፥14 ፦ ማር. 6፥13 ።



ሽማግሌዎችን ወደ እርሱ ይጥራ ፤ እነርሱም
በሽተኛውን በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩ
ለት ። [15] እንዲህ ዐይነቱ በእምነት የተመሠረተ
ጸሎት በሽተኛውን ያድነዋል ፤ ጌታም ከበሽ
ታው ይፈውሰዋል ፤ የሠራው ኃጢአትም ቢኖር
ይቅር ይባልለታል ። [16] ስለዚህ እንድትፈወሱ
ኃጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ ፤ እያን
ዳንዱም ለሌላው ይጸልይ ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት
ብዙ ውጤት የሚያስገኝ ታላቅ ኀይል አለው ፤
[17] ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ ፤ ነገር ግን
ዝናም እንዳይዘንም በጸለየ ጊዜ ለሦስት ዓመት
ተኩል በምድር ላይ ምንም ዝናም አልዘነ
መም ። [18] እንደገና በጸለየም ጊዜ ሰማይ ዝናም
ሰጠ ፤ ምድርም እንደገና ፍሬ ሰጠች ።
[19] ወንድሞቼ ሆይ! ከእናንተ አንዱ ከእው
ነት መንገድ ቢወጣና ሌላው ወደ እውነት መን
ገድ ቢመልሰው ፤ [20] ኃጢአተኛውን ከተሳሳተ
በት መንገድ የሚመልስ ፣ የኃጢአተኛውን
ነፍስ ከሞት እንደሚያድንና የብዙ ኃጢአቱ
ንም ይቅርታ እንደሚያስገኝለት ይወቅ ።

# የመጀመሪያው
# የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት

## መግቢያ

መጀመሪያው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት የተጻፈው በመልእክቱ ውስጥ "የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ" በመባል ለሚጠሩትና በታናሽቱ እስያ ሰሜናዊ ክፍል ለተበተኑት ክርስቲያኖች ነው ፤ የመልእክቱ ዋና ዓላማ በእምነታቸው ምክንያት ስደትና መከራ ደርሶባቸው የነበሩትን አንባቢዎች ለማበረታታትና ለማጽናናት ነው ፤ ጸሐፊው ይህን የሚያደርገው የሞቱን ፣ የትንሣኤውን ፣ ተመልሶ የመምጣቱን ተስፋ የሚያበሥረውን የኢየሱስ ክርስቶስን የምሥራች ቃል ለአንባቢዎቹ በማስታወስ ነው ፤ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት በምሳሌነት በመመልከት መከራን በትዕግሥት መቀበል እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል ፤ ከዚህም ጋር በማያያዝ መከራ የእምነታቸውን ጥራት እንደሚፈትንና "ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ቀን" ተገቢ ሽልማታቸውን እንደሚቀበሉ ያስገነዝባቸዋል ።

ጸሐፊው በመከራ እንዲታገሡ ከማደፋፈሩም ባሻገር አንባቢዎቹ የክርስቶስ ተከታዮች መኖር እንደሚገባቸው እንዲኖሩ ያሳስባቸዋል ።

---

## ምዕራፍ 1

[1] የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከሆነው ከጴጥ
ሮስ ፣
መጻተኞች ሆናችሁ በጳንጦስ ፣ በገላትያ ፣
በቀጰዶቅያ ፣ በእስያ ፣ በቢትኒያ ተበታትናችሁ
ለምትኖሩት ፤ [2] በእግዚአብሔር አብ አስቀድሞ
ለተወሰናችሁትና ለተመረጣችሁት ፣ ለኢየሱስ
ክርስቶስ ለመታዘዝና በደሙ ተረጭታችሁ ለመ
ንጻት በመንፈስ ቅዱስ ለተቀደሳችሁት ፣
ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ ።

### ሕያው ተስፋ

[3] በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያት
ሕያው የሆነውን ተስፋ የሰጠን ፣ በታላቅ ምሕ
ረቱ በአዲስ ልደት ልጆቹ ያደረገን ፣ የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነ አምላክ* ይመስ
ገን ፤ [4] እርሱ በሰማይ ያለውን የማይጠፋና የማ
ይበላሽ ፣ የማያረጅም ርስት እንድንወርስ አድር
ጎናል ። [5] እናንተም በመጨረሻው ቀን ለሚገለ
ጠው ደኅንነት በእምነት አማካይነት በእግዚአ
ብሔር ኀይል ተጠብቃችኋል ። [6] አስፈላጊ ሆኖ
ከተገኘ በልዩ ልዩ ፈተና ምንም እንኳ ብታዝ
ኑም በዚህ ነገር ደስ ይላችኋል ። [7] ይህ ፈተና
የደረሰባችሁ የእምነታችሁን እውነተኛነት ለማ
ረጋገጥ ነው ፤ የሚጠፋ ወርቅ እንኳ በእሳት
ይፈተናል ፤ ከወርቅ ይልቅ የከበረ እምነታችሁ
እንደዚሁ መፈተን አለበት ፤ ይህም የተፈተነ
እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት
ጊዜ ምስጋናን ፣ ክብርንና ውዳሴን ያስገኝ
ላችኋል ። [8] ኢየሱስ ክርስቶስን ያላያችሁትም
እንኳ ቢሆን ትወዱታላችሁ ፤ ያላያችሁት ቢሆ
ንም በእርሱ አምናችሁ በቃላት ሊገለጥ በማይቻ
ልና በከበረ ደስታ ደስ ይላችኋል ። [9] ምክንያቱም

5፥17 ፦ 1ነገ. 17፥1 ፣ 18፥1 ። 5፥18 ፦ 1ነገ. 18፥42-45 ። 5፥20 ፦ ምሳ. 10፥12 ፣ 1ጴጥ. 4፥8 ።
* 1፥3 አዲስ ኪዳን መጀመሪያ በተጻፈበት በግሪክኛው ቋንቋ "የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይመስገን" ይላል ።

የእምነታችሁ ዓላማ የሆነውን የነፍሳችሁን ደኅ
ንነት ስለምታገኙ ነው ።
10 የዚህን ደኅንነት ነገር ነቢያት በጥንቃቄ
ፈልገውና መርምረው ነበር ፤ ስለዚህ እነዚህ
ነቢያት እግዚአብሔር ስለሚሰጣችሁ ጸጋ አስቀ
ድመው በትንቢት ተናገሩ ። 11 ከእነርሱ ውስጥ
የነበረውም የክርስቶስ መንፈስ ፥ ክርስቶስ ስለ
ሚደርስበት መከራና ከመከራውም በኋላ ስለሚ
ያገኘው ክብር አስቀድሞ አመልክቶ ነበር ፤ እነ
ርሱም ይህን ሁሉ በምን ጊዜና በእንዴት ያለ
ሁኔታ እንደሚሆን መርምረው ነበር ፤ 12 እነዚህ
ነቢያት ያገለግሉ የነበሩት እናንተን እንጂ ራሳ
ቸውን እንዳልነበር ተገልጦላቸዋል ፤ ያገለገሉአ
ችሁም ከሰማይ በተላከው በመንፈስ ቅዱስ አማ
ካይነት አሁን ወንጌልን ያበሠሩአችሁ ሰዎች
የነገሩአችሁን በመግለጥ ነው ፤ ይህን ነገር መላ
እክት እንኳ ለማየት ይመኙት ነበር ።

በቅድስና ስለመኖር

13 ስለዚህ ልቦናችሁን አንቅታችሁ ለሥራ
ተዘጋጁ ፤ በመጠን ኑሩ ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚ
ገለጥበት ጊዜ ለምታገኙት ጸጋ ሙሉ ተስፋ
ይኑራችሁ ። 14 ታዛዦች ልጆች ሆናችሁ ባለማ
ወቅ ቀድሞ የነበራችሁን ክፉ ምኞት አትከ
ተሉ ፤ 15 ነገር ግን የጠራችሁ እግዚአብሔር
ቅዱስ እንደሆነ እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ
ቅዱሳን ሁኑ ፤ 16 ምክንያቱም "እኔ ቅዱስ ስለ
ሆንሁ ፥ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ተብሎ ተጽ
ፎአል ።
17 ለማንም ሳያዳላ በእያንዳንዱ ላይ እንደየ
ሥራው የሚፈርደውን እግዚአብሔርን "አባታ
ችን" ብላችሁ የምትጠሩት ከሆነ ፥ በዚህ ዓለም
በእንግድነት መጻተኞች ሆናችሁ ስትኖሩ እር
ሱን በመፍራት ኑሩ ። 18 እንደምታውቁት ፥ እና
ንተ የተዋጃችሁት ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት
ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚጠፋ ነገር ፥ በብር
ወይም በወርቅ አይደለም ፤ 19 እናንተ የተዋጃች
ሁት ነውር እንደሌለው ንጹሕ በግ በሆነው በክ
ርስቶስ ክቡር ደም ነው ። 20 እርሱ የተመረ
ጠው ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ሲሆን ፥ አሁን
በመጨረሻው ዘመን ስለ እናንተ ተገልጦአል ።
21 በእርሱም አማካይነት እርሱን ከሞት ባስነሣ
ውና ክብርን በሰጠው በእግዚአብሔር ታምናላ
ችሁ ፤ ስለዚህ እምነታችሁና ተስፋችሁ በእግዚ
አብሔር ነው ።
22 ግብዝነት የሌለበት ፍቅር ለአማኞች ወን
ድሞች እንዲኖራችሁ ለእውነት በመታዘዝ ነፍ
ሳችሁን አንጽታችኋል ፤ ስለዚህ በሙሉ[2*] ልባ
ችሁ እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ ።
23 ዳግመኛ የተወለዳችሁት ሕያው በሆነውና
ለዘላለም ጸንቶ በሚኖረው በእግዚአብሔር ቃል
ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ ከሚጠፋ ዘር አይደ
ለም ፤ 24 ምክንያቱም መጽሐፍ እንደሚለው ፥

"ሥጋ ለባሽ ሁሉ እንደ ሣር ነው ፤
ክብሩም ሁሉ እንደ ዱር አበባ ነው ፤
ሣሩም ይደርቃል ፥ አበባውም
ይረግፋል ፤
25 የእግዚአብሔር ቃል ግን
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል ።"

የምሥራች ሆኖ የታወጀላችሁም ቃል ይኸው
ነው ።

## ምዕራፍ 2

### ሕያው ድንጋይና ቅዱስ ሕዝብ

1 እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ፥ ማታለልን ሁሉ ፤
ግብዝነትን ፥ ቅንአትን ፥ ማንኛውንም ዐይነት
ሐሜት አስወግዱ ፤ 2 አዲስ የተወለዱ ሕፃናት
ወተት እንደሚመኙ ፤ እናንተም በደኅንነታችሁ
እያደጋችሁ የምትሄዱበትን ንጹሑን መንፈሳዊ
ትምህርት ተመኙ ። 3 ልትመኙ የምትችሉትም
"እግዚአብሔር ደግ መሆኑን ቀምሳችሁ በውቃ
ችሁ እንደሆን ነው ።"
4 ስለዚህ ሕያው ድንጋይ ወደሆነው ወደ
ጌታ ኢየሱስ ቅረቡ ፤ ይህ ድንጋይ ሰዎች ንቀው
የጣሉት ፥ እግዚአብሔር ግን የመረጠውና ያከበ
ረው ነው ። 5 ወደ ጌታ ኢየሱስ የምትቀርቡ
ትም እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት
ሆናችሁ ለመታነጽ ነው ፤ በዚህ ዐይነት በኢየ
ሱስ ክርስቶስ አማካይነት ደስ የሚያሰኝ መንፈ
ሳዊ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ
ቅዱሳን ካህናት ትሆናላችሁ ። 6 ምክንያቱም
በመጽሐፍ ፥

"እነሆ የተመረጠና ክቡር የሆነ
የማእዘን ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ ፤
በእርሱም የሚያምን አያፍርም"

የሚል ቃል ተጽፎ ይገኛል ። 7 እንግዲህ ለእና
ንተ ለምታምኑት ይህ ድንጋይ ክቡር ነው ፤
ለማያምኑት ግን ፥

"ግንበኞች ንቀው የጣሉት ድንጋይ
ዋና የማእዘን ድንጋይ ሆነ ።"

8 ደግሞም ፥

"እነሆ! ሰዎችን የሚያሰናክል ድንጋይ ፤
እነሆ! ሰዎችን አደናቅፎ የሚጥል
አለት"

እንደተባለው ነው ። ምክንያቱም እነርሱ ቃሉን
ባለማመናቸው ተሰናከሉ ። እነርሱ የተወሰኑ
ትም ለዚህ ነው ።

[2*] 1፡22 በሙሉ ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "በንጹሕ" ይላሉ ።

1፡16 ፦ ዘሌ. 11፡44-45 ፤ 19፡2 ። 1፡24-25 ፦ ኢሳ. 40፡6-8 ። 2፡3 ፦ መዝ. 34፡8 ። 2፡6 ፦ ኢሳ. 28፡16 ።
2፡7 ፦ መዝ. 118፡22 ። 2፡8 ፦ ኢሳ. 8፡14-15 ።



9 እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚያስደንቅ ብር
ሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን አስደናቂ
ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ ፥ የን
ጉሥ ካህናት ፥ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋ
ችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ ። 10 እናንተ ቀድሞ
የእግዚአብሔር ሕዝብ አልነበራችሁም ፤ አሁን
ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ናችሁ ፤ ቀድሞ
ምሕረት አላገኛችሁም ነበር ፤ አሁን ግን ምሕ
ረት አግኝታችኋል ።

የእግዚአብሔር አገልጋዮች

11 ወዳጆቼ ሆይ! በዚህ ዓለም እንግዶችና
መጻተኞች ስለሆናችሁ ከነፍስ ጋር ከሚዋጉት
ከሥጋ ፍትወቶች እንድትርቁ ዐደራ እላችኋ
ለሁ ። 12 ምንም እንኳ "ክፉ አድራጊዎች
ናቸው" ብለው ቢያሙአችሁም እግዚአብሔር
እኛን ለመጐብኘት በሚመጣበት ቀን ፥ አረማ
ውያን መልካም ሥራችሁን በማየታቸው ምክን
ያት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ፥ በእነርሱ
መካከል ስትኖሩ መልካም ጠባይ ይኑራችሁ ።
13 ስለ ጌታ ኢየሱስ ብላችሁ ሥልጣን ላላ
ቸው ሰዎች ታዘዙ ፤ የበላይ ባለሥልጣን ስለሆነ
ለንጉሠ ነገሥቱ ታዘዙ ። 14 ለአገር አስተዳዳሪዎ
ችም ታዘዙ ፤ ምክንያቱም እነርሱ ክፉ አድራጊ
ዎችን ለመቅጣት ፥ መልካም አድራጊዎችን
ለማመስገን ከንጉሠ ነገሥቱ የሚላኩ ናቸው ።
15 መልካም በማድረግ የሞኞችን አላዋቂ ንግ
ግር ዝም እንድታሰኙ የእግዚአብሔር ፈቃድ
ነው ። 16 እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ሆና
ችሁ በነፃነት ኑሩ እንጂ ነፃነታችሁን የክፋት
መሸፈኛ አታድርጉት ። 17 ሰውን ሁሉ አክ
ብሩ ፤ አማኞችን ውደዱ ፤ እግዚአብሔርን
ፍሩ ፤ ንጉሥን አክብሩ ።

የክርስቶስ መከራ ምሳሌነት

18 እናንተ አገልጋዮች ለጌቶቻችሁ በአክብ
ሮት ታዘዙ ፤ የምትታዘዙትም ለደጎቹና ለገሮቹ
ብቻ ሳይሆን ለክፉዎችም ነው ። 19 ምክንያቱም
ሰው የሚመሰገነው በግፍ መከራ ሲቀበል ስለ
እግዚአብሔር ብሎ ቢታገሥ ነው ። 20 ክፉ አድ
ርጋችሁ ቅጣት ስትቀበሉ ብትታገሡ ምን ምስ
ጋና ይኖራችኋል? ነገር ግን መልካም አድርጋ
ችሁ መከራ ስትቀበሉ ብትታገሡ ከእግዚአብ
ሔር ምስጋና ታገኛላችሁ ። 21 የተጠራችሁትም
ለዚሁ ነው ፤ ምክንያቱም የእርሱን አርአያነት
እንድትከተሉ ክርስቶስ መከራ በመቀበል ምሳሌ
ሆኖላችኋል ። 22 እርሱ ምንም ኃጢአት አላደረ
ገም ፤ በአፉ ተንኰል አልተገኘበትም ። 23 ሲሰ
ድቡት መልሶ አልተሳደበም ፤ መከራን ሲቀበል
ጻድቅ ፈራጅ በሆነው አምላክ ተስፋ አደረገ
እንጂ አልዛተም ። 24 እኛ በሞት የመለየትን
ያህል ከኃጢአት ተለይተን በጽድቅ እንድን
ኖር ፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በመ
ስቀል ላይ ተሸከመ ፤ በእርሱ ቍስል እናንተ
ተፈውሳችኋል ። 25 ምክንያቱም እናንተ እንደ
ጠፉ በጎች ትቅበዘበዙ ነበር ፤ አሁን ግን ወደ
ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል ።

## ምዕራፍ 3

### ስለባልና ሚስት

1 እንዲሁም እናንተ ሚስቶች ለባሎቻችሁ
ታዘዙ ፤ በዚህ ዐይነት ገና በእግዚአብሔር ቃል
የማያምኑ ባሎች ቢኖሩም በቃል ምስክርነት
ብቻ ሳይሆን በሚስቶቻቸው የሕይወት ምስክር
ነት ሊመለሱ ይችላሉ ። 2 ይህንንም የሚያደር
ጉት ንጹሕ የሆነውንና ሰው አክባሪ የሆነውን
ሕይወታችሁን ሲመለከቱ ነው ። 3 የእናንተ
ውበት ጠጕርን በመሠራት ፥ የወርቅ ጕትቻን
በማንጠልጠል ፥ የከበረ ልብስ በመልበስ በውጭ
ከተገኘ ጌጥ አይሁን ። 4 ነገር ግን ውበታችሁ
በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ በሆ
ነና በማይጠፋው ጌጥ በገርነትና በጭምትነት
መንፈስ ያጌጠው ፥ በልብ ተሰውሮ የሚገኘው ፥
ውስጣዊ ሰውነት ይሁን ። 5 ምክንያቱም በቀ
ድሞ ጊዜ ተስፋቸውን በእግዚአብሔር ላይ
የጣሉ ፥ የተቀደሱ ሴቶች ያጌጡት በዚህ ዐይ
ነት ነበር ፤ ለባሎቻቸውም ይታዘዙ ነበር ።
6 የታዘዙትም ሣራ አብርሃምን "ጌታዬ" እያ
ለች ትታዘዝለት እንደነበረው ዐይነት ነው ፤ እና
ንተም መልካም የሆነውን ነገር ብታደርጉና
የፍርሃት ተገዦዎች ባትሆኑ የእርስዋ ልጆች
ናችሁ ።
7 እናንተም ባሎች ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስ
ተዋል አብራችሁ ኑሩ ፤ ከእናንተ ይልቅ ደካማ
ፍጥረት ስለሆኑና ከእናንተም ጋር የሕይወትን
ጸጋ ስለሚወርሱ አክብሩአቸው ፤ በዚህ ዐይነት
ለጸሎታችሁ መሰናክል የሚሆን ነገር አይኖ
ርም ።

መልካም በማድረግ መከራ መቀበል

8 በቀረውስ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ በመ
ስማማት ኑሩ ፤ የሌላውን ሰው ችግር እንደ ራሳ
ችሁ አድርጋችሁ አስቡ ፤ በወንድማማችነት
ፍቅር ተዋደዱ ፤ ደጎችና ትሑቶች ሁኑ ።
9 መርቁ እንጂ ክፉውን በክፉ ፈንታ ፥ ስድብ
ንም በስድብ ፈንታ አትመልሱ ፤ ምክንያቱም

2፡9 ፦ ዘጸ. 19፡5-6 ፤ ኢሳ. 43፡20-21 ፤ ሆሴ. 4፡20 ፤ 7፡6 ፤ 14፡2 ፤ ቲቶ 2፡14 ፤ ኢሳ. 9፡2 ። 2፡10 ፦ ሆሴዕ 2፡23 ።
2፡22 ፦ ኢሳ. 53፡9 ። 2፡23 ፦ ኢሳ. 53፡7 ። 2፡24 ፦ ኢሳ. 53፡5 ። 2፡25 ፦ ኢሳ. 53፡6 ። 3፡1 ፦ ኤፌ. 5፡22 ፤
ቆላ. 3፡18 ። 3፡3 ፦ 1ጢሞ. 2፡9 ። 3፡6 ፦ ዘፍ. 18፡12 ። 3፡7 ፦ ኤፌ. 5፡25 ፤ ቆላ. 3፡19 ።

እናንተ የተጠራችሁት ይህን በማድረግ በረከትን
ለመውረስ ነው ፤ [10] መጽሐፍ እንደሚል ፤

“ሕይወትን የሚወድድና መልካም
ቀኖችን ማየት የሚፈልግ ፣
ምላሱ ክፉ ነገር እንዳይናገር ፣
ከንፈሮቹ ተንኰልን እንዳይናገሩ
ይከልክል ።
[11] ከክፉ ነገር ይራቅ ፤ መልካምን ነገር
ያድርግ ፤
ሰላምን ይፈልግ ፤ ይከተላትም ፤
[12] ምክንያቱም የእግዚአብሔር ዐይኖች
ወደ ጻድቃን ይመለከታሉ ፤
ጆሮዎቹም ጸሎታቸውን ለመስማት
ተከፍተዋል ፤
በክፉ አድራጊዎች ላይ ግን
እግዚአብሔር የቍጣ ፊቱን
ያሳያል ።”

[13] መልካም ነገር ለማድረግ ብትተጉ ጕዳት
የሚያደርስባችሁ ማን ነው? [14] መልካም ነገር
በማድረግ መከራን ብትቀበሉ እንኳ በረከትን
ታገኛላችሁ ፤ የሰዎችን ዛቻ አትፍሩ ፣ አትጨነ
ቁም ። [15] ጌታ የሆነውን ክርስቶስን በልባችሁ
አክብሩት ፤ በእናንተ ስላለው ተስፋ ምክንያት
ለሚጠይቃችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዝግጁ
ዎች ሁኑ ። [16] ነገር ግን መልሳችሁ በገርነትና
በአክብሮት ይሁን ፤ የክርስቶስ በመሆናችሁ ባላ
ችሁ መልካም ጠባይ ላይ ክፉ የሚናገሩ ሰዎች
በክፉ ንግግራቸው እንዲያፍሩ መልካም ኅሊና
ይኑራችሁ ። [17] ምክንያቱም የእግዚአብሔር
ፈቃድ ከሆነ ለእናንተ የሚሻለው መልካም
ነገር በማድረግ መከራ ብትቀበሉ እንጂ ክፉ
ነገር በማድረግ መከራ ብትቀበሉ አይደለም ።
[18] ክርስቶስም ራሱ ወደ እግዚአብሔር ያቀርበን
ዘንድ እርሱ ጻድቅ ሆኖ ሳለ ፣ ጽድቅ ለሌለን
ለእኛ በኃጢያታችን ምክንያት በማያዳግም
ሁኔታ አንድ ጊዜ መከራን በመቀበል ሞቶአል ፤
እርሱ በሥጋ ሞተ ፣ በመንፈስ ግን ሕያው
ሆነ ። [19] በሲኦል ወደታሰሩት በመንፈስ ሄደ ፤
እዚያ ለነበሩትም ነፍሶች የምሥራቹን ቃል
አበሠራቸው ። [20] እነዚህ በወህኒ ቤት የነበሩ
ነፍሶች ቀድሞ በኖኅ ጊዜ መርከብ ሲዘጋጅ እግ
ዚአብሔር በትዕግሥት ሲጠብቃቸው ሳለ አንታ
ዘዝም ያሉ ናቸው ። በመርከብ ውስጥ ገብተው
በውሃ አማካይነት የዳኑት ቍጥራቸው ስምንት
የሆነ ጥቂት ሰዎች ናቸው ። [21] ይህም ውሃ
አሁን እናንተን የሚያድን የጥምቀት ምሳሌ
ነው ፤ ይህ ጥምቀት የሰውነትን ዕድፍ ማስወ
ገድ ሳይሆን በመልካም ኅሊና ለእግዚአብሔር
የሚቀርብ ልመና ነው ፤ የሚያድናችሁም በኢየ
ሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ አማካይነት ነው ፤
[22] እርሱ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር አብ
ቀኝ አለ ፤ መላእክትና ሥልጣናት ኀይላትም
ተገዝተውለታል ።

## ምዕራፍ 4

### በቅድስና መኖር

[1] ክርስቶስ በሥጋው መከራ የተቀበለ ስለ
ሆነ ፣ እናንተንም ይህ አሳብ እንደ ጦር ዕቃ
ሆኖ ያበርታችሁ ፤ ምክንያቱም በሥጋው
መከራ የተቀበለ ኃጢአት መሥራትን ትቶአል ።
[2] ከእንግዲህ ወዲህም በምድራዊ ኑሮው የሚኖ
ረው የሥጋን ክፉ ምኞት በማድረግ ሳይሆን ፣
የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ነው ።
[3] ምክንያቱም አረማውያን እንደሚያደርጉት
በመዳራት ፣ በፍትወት ፣ በስካር ፣ በዘፈን ፣ ያለ
ልክ ጠጥቶ በመጨፈር ፣ አስጸያፊ በሆነ የጣ
ዖት አምልኮ ያሳለፋችሁት ዘመን ይበቃል ።
[4] አሁን ግን በዚህ ነገር አለመጠን ከእነርሱ ጋር
በመቅበጥ ባለመሳተፋችሁ ይደነቃሉ ፤ ይሰድቡ
አችኋልም ። [5] ነገር ግን በሕይወት ባሉትና በሞ
ቱት ላይ ሊፈርድ ለተዘጋጀው ለእርሱ መልስ
ይሰጡበታል ። [6] ለሙታን ሳይቀር ወንጌል የተሰ
በከውም በዚህ ምክንያት ነው ፤ በዚህ ዐይነት
በሥጋቸው እንደ ሰው ይፈረድባቸዋል ፤ በመን
ፈሳቸው ግን እግዚአብሔር በሚኖረው ዐይነት
በሕይወት ይኖራሉ ።

### የእግዚአብሔር ስጦታዎችን በመልካም ማስተዳደር

[7] እንግዲህ የሁሉ ነገር መጨረሻ ቀርቦአል ፤
በትጋት መጸለይ እንድትችሉ የረጋ አእምሮ
ይኑራችሁ ፤ በመጠንም ኑሩ ። [8] ፍቅር ብዙ
ኃጢአትን ስለሚደመስስ ከሁሉ በላይ እርስ በር
ሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ ። [9] ያለ ማጕረም
ረም እርስ በርሳችሁ በእንግድነት ተቀባበሉ ።
[10] የተለያዩትን የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ
ዎች በታማኝነት በማስተዳደር ከእናንተ እያንዳ
ንዱ በተሰጠው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገል
ግል ። [11] የሚያስተምር ፣ እግዚአብሔር በእርሱ
እንደሚናገር አድርጎ ይናገር ፤ የሚያገለግል ፣
እግዚአብሔር በሚሰጠው ኀይል ያገልግል ፤
በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ
አማካይነት በሁሉ ነገር ይመሰገናል ፤ ክብርና
ሥልጣን ለዘላለም ለእርሱ ይሁን ፤ አሜን ።

### በመከራ ጊዜ መጽናት

[12] ወዳጆች ሆይ! እንደ እሳት በሚፈትን
መከራ ውስጥ ስትገኙ ያልተለመደ እንግዳ ነገር
እንደ ደረሰባችሁ አድርጋችሁ አትደነቁ ፤
[13] ይልቅስ እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እጅግ ደስ

3፥10-12 ፡- መዝ. 34፥12-16 ። 3፥14-15 ፡- ማቴ. 5፥10 ፤ ኢሳ. 8፥12-13 ። 3፥20 ፡- ዘፍ. 6፥1-7፥24 ።
4፥8 ፡- ምሳ. 10፥12 ።



እንዲላችሁ የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በሆና
ችሁበት መጠን ደስ ይበላችሁ ። [14] ስለ ክርስ
ቶስ ስም ብትሰደቡ ክቡር የሆነው የእግዚአብ
ሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ስለሚያርፍ ደስ
ይበላችሁ ። [15] ከእናንተ ማንም መከራ ሲቀበል
እንደ ነፍሰ ገዳይ ፣ እንደ ሌባ ፣ እንደ ወንጀ
ለኛ ፣ በሰው ጕዳይ ጣልቃ እንደሚገባ አይ
ሁን ። [16] ክርስቲያን በመሆኑ መከራ የሚደርስ
በት ቢኖር ግን ስለ ክርስቶስ ስም እግዚአብሔ
ርን ያመስግን እንጂ አይፈር ።

[17] ፍርድ የሚጀመርበት ጊዜ ቀርቦአል ፤
ፍርዱ የሚጀመረውም በእግዚአብሔር ሰዎች
ላይ ነው ፤ ታዲያ ፍርድ የሚጀመረው በእኛ
ከሆነ ፣ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ
ሰዎች መጨረሻቸው ምን ይሆን? [18] መጽሐፍ
እንደሚል ፣

“ጻድቅ እንኳ መዳን የሚችለው በጭንቅ
ከሆነ
ዐመፀኛውና ኃጢአተኛው እንዴት
ሊሆን ነው?”

[19] ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራ
የሚቀበሉ ሰዎች ሁለንተናቸውን ለታማኙ
ፈጣሪ ዐደራ ሰጥተው መልካም ነገርን ከማድ
ረግ አይቈጠቡ ።

## ምዕራፍ 5

### የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማስተዳደር የተሰጠ መመሪያ

[1] እንግዲህ እኔ ከእነርሱ ጋር አብሬ የቤተ
ክርስቲያን ሽማግሌ የሆንሁ ፣ የክርስቶስም
መከራ ምስክር የሆንሁ ፣ እንዲሁም ወደፊት
የሚገለጠው ክብር ተካፋይ የምሆን ፣ በመካከላ
ችሁ ያሉትን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች
እመክራቸዋለሁ ። [2] በዐደራ የተሰጣችሁን የእግ
ዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ ፤ መንጋውን የምት
ጠብቁትም በግድ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚፈ
ልገው ዐይነት ፣ በፈቃደኝነት ይሁን ፤ ለገንዘብ
በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባለችሁ ፍላ
ጎት ይሁን ። [3] እንዲሁም በእናንተ ኀላፊነት
ሥር ያሉትን ጨቍኖ በመግዛት ሳይሆን ፣ ለመ
ንጋው መልካም ምሳሌነትን በማሳየት ይሁን ።
[4] ይህን ብታደርጉ ዋናው እረኛ በሚገለጥበት
ጊዜ የማይበላሸውን የክብር አክሊል ትቀበላላ
ችሁ ።

[5] እንዲሁም እናንተ ጕልማሶች ፤ ለሽማግሌ
ዎች ታዘዙ ፤ ሁላችሁም ትሕትናን እንደ
ልብስ ለብሳችሁ አንዱ ሌላውን ያገልግል ፤
ምክንያቱም

“እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል
ለትሑቶች ግን ጸጋን ይሰጣል ።”

[6] እንግዲህ እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ ከፍ
እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ
ሥር ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ ። [7] እርሱ ለእናንተ
ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን አሳብ ሁሉ
በእርሱ ላይ ጣሉት ።

[8] በመጠን ኑሩ ፤ ንቁም ፤ ምክንያቱም ጠላታ
ችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደ
ሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችሁ ያደባል ። [9] በዓለም
ሁሉ ያሉ ወንድሞቻችሁ ይህን ዐይነት መከራ
እንደሚቀበሉ በማወቅ በእምነት ጸንታችሁ
ተቃወሙት ። [10] የክርስቶስ በመሆናችሁ ወደ
ዘላለማዊ ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ
ራሱ ፣ ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ
ፍጹሞች ያደርጋችኋል ፤ ያጸናችኋል ፤ ያበረ
ታችኋልም ። [11] ለእርሱ ለዘላለም ኀይል ይሁን!
አሜን ።

### የመጨረሻ ሰላምታ

[12] ታማኝ ወንድም ነው ብዬ በማስበው በሲ
ላስ አማካይነት ይህን መልእክት ባጭሩ ጽፌ
ላችኋለሁ ፤ የጻፍሁላችሁም ልመክራችሁና ይህ
እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑን ልመሰ
ክርላችሁ ብዬ ነው ፤ ስለዚህ በዚህ በእግዚአብ
ሔር ጸጋ ጸንታችሁ ቁሙ ።

[13] እንደ እናንተ የተመረጠችው ፣ በባቢሎን
ያለችው እኅት ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ታቀር
ብላችኋለች ፤ ልጄ ማርቆስም ሰላምታ ያቀርብ
ላችኋል ። [14] በክርስቲያናዊ ፍቅር እርስ በርስ
በመሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ ።

የክርስቶስ ለሆናችሁት ለሁላችሁም ሰላም
ይሁን ።

4፥18 ፡- ምሳ. 11፥31 ። 5፥2 ፡- ዮሐ. 21፥15-17 ። 5፥5 ፡- ምሳ. 3፥34 ። 5፥6 ፡- ማቴ. 23፥12 ፤ ሉቃ. 14፥11 ፤ 18፥14 ።
5፥12 ፡- ሐ.ሥ. 15፥22 ፥40 ። 5፥13 ፡- ሐ.ሥ. 12፥12 ፥25 ፤ 13፥13 ፤ 15፥37-39 ፤ ቆላ. 4፥10 ፤ ፊልሞና 24 ።

## ሁለተኛው

# የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት

### መግቢያ

ሁለተኛው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት የተጻፈው በልዩ ልዩ ስፍራ ለሚገኙ የጥንት ክርስቲያኖች ነው ። የመልእክቱ ዋና ዓላማ የሐሰተኞች መምህራንን ክፉ ሥራና የእነርሱንም ትምህርት አስመልክቶ የተፈጠረውን የብልግና ሕይወት መቃወም ነው ። ለተፈጠሩት ችግሮች መፍትሔ የሚሆነው ኢየሱስን በዐይናቸው ያዩትና ሲያስተምርም በጆሮአቸው የሰሙት ሰዎች ባስተላለፉት ትምህርት አማካይነት ስለ እግዚአብሔርና ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጨባጭ ዕውቀት ማግኘት ነው ። ጸሐፊው በተለይ ጥንቃቄ ያደረገው "ክርስቶስ ተመልሶ አይመጣም" ስለሚለው የሐሰት ትምህርት ነው ፤ ይህንኑ አስመልክቶ ሲናገር "ክርስቶስ ተመልሶ ከመምጣት የሚዘገየው ፥ እግዚአብሔር ፤ ሰው ሁሉ ከኃጢአቱ እንዲመለስ እንጂ ማንም ሰው እንዲጠፋ ስለማይፈልግ ነው" ይላል ።

## ምዕራፍ 1

1የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ ከሆ
ነው ከስምዖን ጴጥሮስ ፥
በአምላካችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ጽድቅ አማካይነት እኛ እንዳገኘነው እም
ነት የሆነ ክቡር እምነት ላገኛችሁት ፤
2እግዚአብሔርንና ጌታችንን ኢየሱስን በማ
ወቅ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ ።

### የእግዚአብሔር ጥሪና ምርጫ

3በገዛ ራሱ ክብር ፥ በቸርነቱም የጠራንን
በማወቃችን ምክንያት ለሕይወትና ለእውነተኛ
መንፈሳዊነት የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ
በመለኮታዊ ኀይሉ ሰጥቶናል ። 4በእነዚህም
በተሰጡን ነገሮች አማካይነት በክፉ ምኞት
ምክንያት በዓለም ላይ ካለው የሞራል ውድቀት
አምልጣችሁ ፥ የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች
እንድትሆኑ ፥ ክቡርና እጅግ ታላቅ የሆነውን
ተስፋ ሰጥቶናል ። 5በዚህ ምክንያት የሚከተ
ሉት ነገሮች እንዲጨመሩላችሁ ትጉ ፦ በእም
ነት ላይ ደግነትን ፥ በደግነት ላይ ዕውቀትን ፥
6በዕውቀት ላይ ራስ መቈጣጠርን ፥ በራስ መቈ
ጣጠር ላይ በትዕግሥት መጽናትን ፥ በትዕግ
ሥት በመጽናት ላይ መንፈሳዊነትን ፥ 7በመንፈ
ሳዊነት ላይ ወንድማማችነትን ፤ በወንድማማች
ነት ላይ ፍቅርን ጨምሩ ። 8እነዚህ ነገሮች በብ
ዛት ቢኖሩአችሁ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን
ወደማወቅ ትደርሳላችሁ ፤ ሥራ ፈቶችና ፍሬ
ቢሶችም አትሆኑም ። 9እነዚህ ነገሮች የሌሉት
ግን የሩቁን ነገር ማየት የማይችል ዕውር ነው ፤
ያለፉት ኃጢአቶቹ መደምሰሳቸውን ረስቶአል ።
10ስለዚህ ወንድሞች ሆይ! መጠራታችሁ
ንና መመረጣችሁን ለማረጋገጥ በይበልጥ ትጉ ፤
ይህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም ። 11በዚህ
ዐይነት ዘላለማዊት ወደሆነችው ወደ ጌታችንና
አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ለመግ
ባት ሙሉ መብት ይሰጣችኋል ።
12ምንም እንኳ እነዚህን ነገሮች ብታውቁአ
ቸውና በያዛችሁት እውነት ጸንታችሁ ብትኖ
ሩም ፥ እነርሱን ለእናንተ ከማሳሰብ ቸል አል
ልም ። 13በዚህ ሕይወት እስካለሁበት ጊዜ
ድረስ ፥ እናንተን ዘወትር ማንቃቃት የሚገባኝ
መሆኑን አስባለሁ ። 14ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
እንደገለጠልኝ በቶሎ ከዚህ ዓለም በሞት እንደ
ምለይ ዐውቃለሁ ። 15እኔ አሁን የምተጋው ፥
በሞት ከተለየኋችሁ በኋላ እንኳ እነዚህን ነገሮች
ዘወትር ማስታወስ እንድትችሉ ነው ።

### የክርስቶስ ክብር የዐይን ምስክሮች

16ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኀይልና ስለ
መምጣቱም በነገርናችሁ ጊዜ ራሳችን ግርማ
ውን አይተን እንጂ በሰው ብልኀት የተፈጠረ
ውን ተረት ተከትለን አይደለም ። 17"በእርሱ
ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" የሚል
ድምፅ ከታላቁ ክብር በመጣለት ጊዜ ከእግዚአ
ብሔር አብ ምስጋናንና ክብርን ተቀብሎአል ።
18ከእርሱ ጋር በተቀደሰው ተራራ ላይ በነበርን
በት ጊዜ ይህን ከሰማይ የመጣውን ድምፅ እኛ
ራሳችን ሰምተናል ።

1፥17-18 ፦ ማቴ. 17፥1-5 ፤ ማር. 9፥2-7 ፤ ሉቃ. 9፥28-35 ።





19ይህንንም በይበልጥ የሚያረጋግጥልን የነቢ
ያት ቃል አለን ፤ ይህን ቃል ሌሊቱ እስኪነጋና
የንጋት ኮከብ በልባችሁ እስኪበራ ድረስ ፥ በጨ
ለማ እንደሚያበራ መብራት አድርጋችሁ ብት
ጠነቀቁለት መልካም ነው ። 20ከሁሉ በፊት
ማስተዋል የሚገባችሁ ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚ
ገኘውን ማንኛውንም ትንቢት ማንም ሰው
በራሱ ግላዊ አስተሳሰብ ሊተረጉም አለመቻሉን
ነው ። 21ምክንያቱም ማንኛውም ትንቢት
በሰው ፈቃድ ከቶ አልመጣም ፤ ነገር ግን ትን
ቢት ፥ በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሰዎች ከእግዚ
አብሔር ተቀብለው የተናገሩት ነው ።

## ምዕራፍ 2

### ሐሰተኞች መምህራን

1ነገር ግን በቀድሞ ዘመን በሕዝቡ መካከል
ሐሰተኞች ነቢያት እንደነበሩ ፥ እንዲሁም በእ
ናንተ መካከል ሐሰተኞች መምህራን ይኖራሉ ፤
እነርሱ ጥፋት የሚያስከትል ሐሰተኛ ትምህርት
በስውር ያስገባሉ ፤ የዋጃቸውንም ጌታ እስከ
መካድ ደርሰው በፍጥነት ጥፋት ይመጣባቸ
ዋል ፤ 2በዚህ ዐይነት ብዙዎች የእነርሱን አሳ
ፋሪ መንገድ ይከተላሉ ፤ ከእነርሱም አድራጎት
የተነሣ የእውነት መንገድ ይሰደባል ። 3እነዚህ
ሐሰተኞች መምህራን ለገንዘብ ከመስገብገባቸው
የተነሣ ራሳቸው የፈጠሩትን ታሪክ እያወሩ ይበ
ዘብዙአችኋል ። ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምሮ
ፍርድ ተዘጋጅቶላቸዋል ፤ ጥፋትም ነቅቶ ይጠ
ብቃቸዋል ።
4እግዚአብሔር ኃጢአት የሠሩትን መላእ
ክት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በሰንሰለት ታስ
ረው የፍርድን ቀን እንዲጠባበቁ ወደ ገሃነም
ጣላቸው እንጂ አልራራላቸውም ። 5እንዲሁም
እግዚአብሔር ኃጢአተኞች በሚኖሩበት ዓለም
ላይ የጥፋትን ውሃ ሲያመጣ የጽድቅ ሰባኪ የነ
በረውን ኖኅን ከሌሎች ሰባት ሰዎች ጋር አዳነ
እንጂ ለቀድሞው ዓለም አልራራም ። 6ደግሞም
ኃጢአት ለሚሠሩ ሁሉ የመቀጣጫ ምሳሌ እን
ዲሆኑ የሰዶምንና የገሞራን ከተሞች ዐመድ
እስኪሆኑ ድረስ አቃጥሎ እንዲጠፉ ፈረደባ
ቸው ። 7በዐመፀኞች አሳፋሪ ድርጊት እየተሠ
ቀቀ ይኖር የነበረውን ጻድቁን ሎጥን ግን
አዳነ ። 8ምክንያቱም ያ ጻድቅ ሰው በመካከላ
ቸው ሲኖር በየቀኑ በሚያየውና በሚሰማው
ክፉ ሥራቸው ምክንያት ጻድቅ ነፍሱ ትጨነቅ
ነበር ። 9እንግዲህ ይህ ሁሉ እንዲህ ከሆነ እግዚ
አብሔር መንፈሳውያን ሰዎችን ከፈተና እንደ
ሚያድናቸው ፥ ኃጢአተኞችንም እንዴት እንደ
ሚቀጣና ለፍርድ ቀንም እንዴት ጠብቆ እንደ
ሚያቆያቸው ያውቃል ማለት ነው ። 10በተለይ
እነዚያን ርኩስ የሆነውን የሥጋ ፍትወታቸውን
የሚከተሉትንና የእግዚአብሔርን ሥልጣን የሚ
ንቁትን ለፍርድ ጠብቆ ያቆያቸዋል ።
እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን ደፋሮችና ትዕ
ቢተኞች ስለሆኑ ፥ የሰማይ ሥልጣናትን እንኳ
ሲሳደቡ አይፈሩም ። 11መላእክት እንኳ ከእነ
ርሱ በኀይልና በሥልጣን የሚበልጡ ቢሆኑም ፥
በእግዚአብሔር ፊት የሰማይ ሥልጣናትን ሲከ
ስሱ አይሳደቡም ። 12እነዚህ ሐሰተኞች መምህ
ራን ግን ለማስተዋል ያቃታቸውን ነገር ይሳደ
ባሉ ፤ እነርሱ ለመያዝና ለመጥፋት እንደ ተወ
ለዱ ፥ በተፈጥሮ ስሜት እንደሚኖሩ ፥ አእምሮ
እንደሌላቸው እንስሳት ናቸው ፤ እንስሳት እንደ
ሚጠፉ እነርሱም ይጠፋሉ ። 13የሀመፀኝነታ
ቸው ዋጋ የሆነውንም ቅጣት ይቀበላሉ ፤ የእነ
ርሱ ደስታ ቀኑን ሙሉ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን
ማርካት ነው ፤ አታላይ በሆነ ሥጋዊ ፍላጎታ
ቸው ዘወትር የሚደሰቱ ሆነው ሳሉ ፥ ከእናንተ
ጋር በፍቅር ግብዣ ላይ በመገኘታቸው አስነዋ
ሪዎችና አሳፋሪዎች ናቸው ። 14ኃጢአት ከማ
ድረግ የማይቈጠብ ቅንዝረኛ ዐይን አላቸው ፤
የማይጸኑትንም ሰዎች ያታልላሉ ፤ ለገንዘብ
መስገብገብ የለመደ ልብ አላቸው ፤ የተረገሙ
ሰዎች ናቸው ። 15እነርሱ የቀናውን መንገድ
ትተዋል ። ለክፉ ሥራው ዋጋ የሆነውን ገንዘብ
የወደደውን የቦሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ
ተከትለው ተሳስተዋል ። 16በለዓም ግን ስለ
ኃጢአቱ ተገሥጾአል ፤ መናገር የማትችል አህያ
በሰው ቃል ተናግራ የነቢዩን የእብደት ሥራ
ተቃውማለች ።
17እነዚህ ሰዎች ውሃ እንደሌለባቸው ምን
ጮች ናቸው ፤ በዐውሎ ነፋስ እንደሚወሰዱ
ደመናዎች ናቸው ፤ ድቅድቅ ጨለማም ይጠብ
ቃቸዋል ። 18ምክንያቱም በስሕተት ከሚኖሩት
ሰዎች መካከል ወጥተው ከመጡ ገና ብዙ ያል
ቆዩትን ሰዎች ከንቱ የሆነ ታላቅ ቃል በመና
ገር ፥ በሥጋዊ ፍትወትና በሴሰኛነት በማባበል
ያታልሉአቸዋል ። 19"ነፃ ትወጣላችሁ" እያሉ
ተስፋ ይሰጡአቸዋል ። እነርሱ ራሳቸው ግን
የኃጢአት ባሪያዎች ናቸው ፤ ምክንያቱም ሰው
ሲሸነፍ ላሸናፊው ባሪያ ሆኖ ይገዛል ። 20ጌታ
ችንንና አዳኛችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ
ከዓለም ርኵሰት ካመለጡ በኋላ ተመልሰው በዚ
ያው ርኵሰት ተይዘው ቢሸነፉ ከፊተኛው
ይልቅ የኋለኛው ሁኔታቸው የባሰ ይሆንባቸ
ዋል ፤ 21ምክንያቱም የጽድቅን መንገድ ካወቁ
በኋላ ከተሰጣቸው ቅዱስ ትእዛዝ ወደ ኋላ ከሚ
መለሱ ይልቅ የጽድቅን መንገድ ሳያውቁ ቀር
ተው ቢሆን ኖሮ በተሻላቸው ነበር ። 22"የተፋ
ውን ለመዋጥ ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል ።"

2፥5 ፦ ዘፍ. 6፥1-7፥24 ። 2፥6 ፦ ዘፍ. 19፥24 ። 2፥7 ፦ ዘፍ. 19፥1-16 ። 2፥15-16 ፦ ዘኁ. 22፥4-35 ።
2፥22 ፦ ምሳ. 26፥11 ።

እንዲሁም “ሀማማ ከታጠበ በኋላ ተመልሶ
በጭቃ ላይ ይንከባለላል” የሚለው ምሳሌ እው
ነት ሆኖ ደርሶባቸዋል ።

## ምዕራፍ 3
### የጌታ ኢየሱስ የመምጣት ተስፋ

1 ወዳጆች ሆይ! ይህ የምጽፍላችሁ ሁለተ
ኛው መልእክት ነው ፤ ሁለቱንም መልእክቶች
የጻፍሁላችሁ እነዚህን ነገሮች በማስታወስ ቅን
አስተሳሰብ እንዲኖራችሁ ላነቃቃችሁ ብዬ
ነው ። 2 ከዚህ በፊት ቅዱሳን ነቢያት የተናገሩ
ትን ቃልና በሐዋርያቶቻችሁ አማካይነት ያገኛ
ችሁትን የጌታችንንና የአዳኛችንን ትእዛዝ እን
ድታስታውሱ እፈልጋለሁ ። 3 ከሁሉ በፊት
ይህን አስተውሉ ፤ በመጨረሻዎቹ ቀኖች የሚያ
ፌዙና ክፉ ምኞታቸውን የሚከተሉ ዘባቾች
ይመጣሉ ፤ 4 እነርሱ “ጌታ ኢየሱስ ይመጣል
ተብሎ ተስፋ ተሰጥቶ አልነበረምን? ታዲያ የት
አለ? የቀድሞ አባቶቻችን ከሞቱበት ጊዜ አን
ሥቶ ሁሉ ነገር ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ
እንደነበረው ነው” ይላሉ ። 5 እነዚህ ሰዎች
ከብዙ ጊዜ በፊት ሰማይና ምድር በእግዚአብ
ሔር ቃል መፈጠራቸውን ሆን ብለው “አናው
ቅም” ይላሉ ፤ ምድርም የተሠራችው ከውሃና
በውሃ መሆኑን ይክዳሉ ። 6 በዚያን ጊዜ የነበረ
ውም ዓለም በውሃ ተጥለቅልቆ ጠፋ ። 7 አሁን
ያሉትም ሰማይና ምድር ፥ ዐመፀኞች ሰዎች
እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በዚሁ
በእግዚአብሔር ቃል ለእሳት ተጠብቀው ይቆ
ያሉ ።
8 ወዳጆቼ ሆይ! እናንተ ግን በጌታ ዘንድ
አንድ ቀን እንደ ሺ ዓመት ፥ ሺ ዓመት እንደ
አንድ ቀን መሆኑን ይህን አንድ ነገር አትርሱ ።
9 አንዳንድ ሰዎች እንደሚመስላቸው ጌታ ኢየ
ሱስ የተናገረውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም አይዘ
ገይም ፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ
እንጂ ማንም ሰው እንዳይጠፋ ፈልጎ ስለ እና
ንተ ይታገሣል ።
10 የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ በድንገት ይመ
ጣል ፤ በዚያን ቀን ሰማይ በታላቅ ድምፅ ያል
ፋል ፤ ፍጥረት ሁሉ በእሳት ተቃጥሎ ይጠ
ፋል ። ምድርና በእርስዋም ላይ ያለው ነገር
ሁሉ ይቃጠላል ፤ 11 እንግዲህ ሁሉ ነገር በዚህ
ሁኔታ የሚጠፋ ከሆነ ፥ ታዲያ እናንተ በቅድስ
ናና በመንፈሳዊነት ኑሮ መኖር እንዴት አይገባ
ችሁም! 12 እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቀን
መምጣት በናፍቆት የምትጠባበቁና በቶሎም
እንዲመጣ የምትሠሩ ሁኑ ፤ በዚያን ቀን ሰማይ
በእሳት ተቃጥሎ ይጠፋል ፤ ፍጥረቶችም በእ
ሳት ግለት ይቀልጣሉ ፤ 13 ነገር ግን እኛ ጽድቅ
የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተ
ስፋ ቃሉ መሠረት እንጠባበቃለን ።
14 ስለዚህ ወዳጆች ሆይ! ይህ ሁሉ የሚሆን
በትን ቀን በመጠባበቅ ላይ ካላችሁ ፥ ጌታ ያለ
ነውር ወይም ያለ ነቀፋ ሆናችሁ በሰላም እንዲ
ያገኛችሁ በትጋት ሥሩ ፤ 15 ጌታችን መታገ
ሡም እናንተ እንድትድኑ ብሎ መሆኑን አትዘ
ንጉ ፤ የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስም በተ
ሰጠው ጥበብ መጠን የጻፈላችሁ ይህንኑ ነው ።
16 እርሱ ስለዚህ ጉዳይ በመልእክቶቹ ሁሉ
በዚሁ ዐይነት ጽፎአል ፤ በመልእክቶቹ ውስጥ
አንዳንድ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ነገሮች አሉ ።
ዕውቀት የጐደላቸውና ወላዋዮች ሌሎችን ቅዱ
ሳት መጽሐፍት እንደሚያጣምሙ ፥ እነዚህንም
ነገሮች ያጣምማሉ ፤ ይህንንም በማድረጋቸው
ይጠፋሉ ፤
17 እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ! ይህን አስቀድ
ማችሁ ዐውቃችኋል ፤ ስለዚህ በዐመፀኞች ስሕ
ተት ተስባችሁ ከጽኑ አቋማችሁ እንዳትወድቁ
ተጠንቀቁ ፤ 18 ይልቅስ በጌታችንና በአዳኛችን
በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እርሱንም በማወቅ
እደጉ ፤ ለእርሱ አሁንም ለዘላለምም ክብር
ይሁን! አሜን ።

3፥3 ፦ ይሁዳ 18 ። 3፥5 ፦ ዘፍ. 1፥6-9 ። 3፥6 ፦ ዘፍ. 7፥11 ። 3፥8 ፦ መዝ. 90፥4 ። 3፥10 ፦ ማቴ. 24፥43 ፤
ሉቃ. 12፥39 ፤ 1ተሰ. 5፥2 ፤ ራእ. 16፥15 ። 3፥13 ፦ ኢሳ. 65፥17 ፤ 66፥22 ፤ ራእ. 21፥1 ።

### የመጀመሪያው
# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት

### መግቢያ

መጀመሪያው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት ፦ እነር
ሱም አንባቢዎቹ ከእግዚአብሔርና ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው ለማ
በረታታትና ይህንንም ኅብረት ሊያጠፋ ከሚችል ሐሰተኛ ትምህርት እንዲርቁ ለማስጠንቀቅ
ነው ። በዚያን ጊዜ የተከሰተው ሐሰተኛ ትምህርት “ክፋት የሚመነጨው ከግዙፉ ዓለም ጋር
በሚደረገው ግንኙነት ስለሆነ ፥ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ከቶ ሰው ሊሆን ወይም የሰብአዊ
ነት ባሕርይ ሊኖረው አይችልም” የሚል ነበር ። እነዚያ መምህራን “ደኅንነት ማለት ለዓለማዊ
ኑሮ ከመጨነቅ ነፃ መውጣት ነው” ይሉ ነበር ፤ ከዚህም ጋር “የሞራል አቋምም ሆነ ለሌላው
ሰው ፍቅር ማሳየት ከደኅንነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም” ይሉ ነበር ።
ጸሐፊው ይህን ትምህርት በመቃወም “ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ነው ፤ በኢየሱስ የሚያ
ምኑና እግዚአብሔርን የሚወዱ ሁሉ እርስ በርሳቸውም መዋደድ ይኖርባቸዋል” በማለት አስረ
ድቶአል ።

## ምዕራፍ 1
### የሕይወት ቃል

1 ከመጀመሪያው ስለነበረው ስለ ሕይወት
ቃል እንጽፍላችኋለን ፤ ይህ የሕይወት ቃል የሰ
ማነውና በዐይኖቻችን ያየነው ፥ የተመለከትነ
ውና በእጆቻችን የዳሰስነው ነው ። 2 ይህ ሕይ
ወት ተገልጦአል ፤ እኛም አይተነዋል ፤ እንመሰ
ክራለንም ። በአብ ዘንድ የነበረውንና ለእኛም
የተገለጠውን የዘላለም ሕይወት እንነግራችኋ
ለን ። 3 ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነ
ውንና የሰማነውን ለእናንተም እንነግራችኋለን ።
ኅብረታችንም ከአብና ከልጁም ከኢየሱስ ክርስ
ቶስ ጋር ነው ። 4 ደስታችን[1*] ሙሉ እንዲሆን
ይህን እንጽፍላችኋለን ።

### እግዚአብሔር ብርሃን ነው

5 ከእርሱ የሰማነውና ለእናንተም የምንነግራ
ችሁ መልእክት “እግዚአብሔር ብርሃን ነው ፤
ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም” የሚል
ነው ። 6 ስለዚህ “ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት
አለን” እያልን ፥ በጨለማ የምንኖር ከሆንን እን
ዋሻለን ፤ በቃላችንም ሆነ በሥራችን እውነት
የለም ማለት ነው ። 7 ነገር ግን እርሱ በብርሃን
እንዳለ ፥ እኛም በብርሃን ብንኖር እርስ በርሳ
ችን ኅብረት ይኖረናል ። ደግሞም የልጁ የኢየ
ሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል ።
8 “ኃጢአት የለብንም” ብንል ራሳችንን እና
ታልላለን ። እውነትም በእኛ ውስጥ የለም ።
9 ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር ብንናዘዝ ፥
እርሱ ታማኝና ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአታችንን
ሁሉ ይቅር ይልልናል ፤ ከበደላችንም ሁሉ ያነ
ጻናል ። 10 “ኃጢአት አልሠራንም” ብንል ፥
እግዚአብሔርን ሐሰተኛ እናደርገዋለን ፤ ቃሉም
በእኛ ውስጥ የለም ።

## ምዕራፍ 2
### ክርስቶስ ጠበቃችን ነው

1 ልጆቼ ሆይ! ይህን የምጽፍላችሁ ኃጢአት
እንዳትሠሩ ብዬ ነው ። ነገር ግን ማንም ሰው
ኃጢአት ቢሠራ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን ፤ እር
ሱም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።
2 ኃጢአታችንም የሚደመሰሰው በእርሱ ነው ፤
የእኛ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን የዓለሙም ሁሉ
ኃጢአት የሚደመሰሰው በእርሱ ነው ።
3 የእግዚአብሔርን ትእዛዞች የምንፈጽም
ከሆንን እርሱን የምናውቅ መሆናችንን እናረጋ
ግጣለን ። 4 “እግዚአብሔርን ዐውቀዋለሁ”
እያለ የእርሱን ትእዛዞች የማይፈጽም ቢኖር
ሐሰተኛ ነው ፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ
የለም ። 5 ነገር ግን ለእግዚአብሔር ቃል የሚ
ታዘዝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር
ፍጹም ነው ፤ በእውነት የእግዚአብሔር ሰዎች
መሆናችንንም የሚታወቀው በዚሁ ነው ፤

[1*] 1፥4 ደስታችን ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ደስታችሁ” ይላሉ ።
1፥1 ፦ ዮሐ. 1፥1 ። 1፥2 ፦ ዮሐ. 1፥14 ።

6 “በእግዚአብሔር እኖራለሁ” የሚል ሰው ፥
ክርስቶስ እንደኖረው መኖር አለበት ።

### አዲሱ ትእዛዝ

7 ወዳጆቼ ሆይ! ይህ የምጽፍላችሁ ትእዛዝ
ከመጀመሪያው አንሥቶ የምታውቁትና የቆየ
ትእዛዝ ነው እንጂ አዲስ አይደለም ፤ ይህም
የቆየ ትእዛዝ በመጀመሪያ የሰማችሁት ቃል
ነው ። 8 ይሁን እንጂ በክርስቶስ ሕይወትና በእ
ናንተ ሕይወት ፥ እውነት ሆኖ የታየውን አዲስ
ትእዛዝ እጽፍላችኋለሁ ፤ ምክንያቱም ጨለ
ማው ተወግዶ እውነተኛው ብርሃን እያበራ
ነው ።

9 “በብርሃን እኖራለሁ” እያለ ወንድሙን
የሚጠላ ገና በጨለማ ነው ። 10 ወንድሙን የሚ
ወድድ ሁሉ በብርሃን ይኖራል ፤ በእርሱም ምክ
ንያት ሰዎች በኀጢአት አይሰናከሉም ። 11 ወን
ድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ ይኖራል ፤ በጨለ
ማም ይመላለሳል ፤ ጨለማም ሀይኑን ስላሳወ
ረው የሚሄድበትን አያውቅም ።

12 ልጆቼ ሆይ! ኀጢአታችሁ በእርሱ ስም
ይቅር ስለተባለላችሁ እጽፍላችኋለሁ ። 13 አባ
ቶች ሆይ! ከመጀመሪያ የነበረውን ስላወቃች
ሁት እጽፍላችኋለሁ ። ወጣቶች ሆይ! ሰይጣንን
ስላሸነፋችሁ እጽፍላችኋለሁ ።

14 ልጆች ሆይ! አብን ስላወቃችሁት እጽፍ
ላችኋለሁ ። አባቶች ሆይ! ከመጀመሪያው የነበ
ረውን ስላወቃችሁት ጻፍሁላችሁ ። ወጣቶች
ሆይ! ብርቱዎች ስለሆናችሁ ፥ በእግዚአብሔር
ቃል ስለጸናችሁ ፥ ሰይጣንን ስላሸነፋችሁ ጻፍ
ሁላችሁ ።

15 ዓለምን ወይም የዓለምን ነገር አትው
ደዱ ። ዓለምን የሚወድድ እግዚአብሔር አብን
አይወድድም ። 16 ምክንያቱም የሥጋ ምኞት ፥
የዐይን አምሮት ፥ የኑሮ ትምክሕት ከዓለም ነው
እንጂ ከእግዚአብሔር አብ አይደለም ። 17 ዓለ
ምና ምኞቱም ያልፋሉ ። የእግዚአብሔርን
ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል ።

### የክርስቶስ ተቃዋሚ ከሆነው መጠንቀቅ

18 ልጆቼ ሆይ! ይህ የመጨረሻው ሰዓት
ነው ፤ “የክርስቶስ ተቃዋሚ ይመጣል” ሲባል
ሰምታችኋል ። እነሆ አሁን እንኳ ብዙ የክርስ
ቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል ። በዚህ ምክን
ያት የመጨረሻው ሰዓት መሆኑን እናውቃለን ።
19 እነርሱ የወጡት ከእኛ መካከል ነው ። ይሁን
እንጂ ድሮውንም ከእኛ ወገን አልነበሩም ።
ከእኛ ወገን ቢሆኑማ ኖሮ ከእኛ ጋር ጸንተው
በኖሩ ነበር ። ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን አለመ
ሆናቸው እንዲታወቅ ከእኛ መካከል ተለይተው
ወጥተዋል ።

20 እናንተ ግን ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ
ቀብቶአችኋል ። ስለዚህ ሁላችሁም እውነትን
ታውቃላችሁ ። 21 ለእናንተ የምጽፍላችሁ እው
ነትን ስለማታውቁ አይደለም ፤ እናንተስ እውነ
ትን ታውቃላችሁ ፤ በእውነትም ሐሰት እንደማ
ይገኝ ታውቃላችሁ ።

22 እንግዲህ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ከሚ
ክድ በቀር ሐሰተኛ ማን ነው? አብንና ወልድን
የሚክድ ሁሉ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው ።
23 ወልድን የሚክድ አብ የለውም ። በወልድ
የሚያምን ፥ በአብ ያምናል ።

24 እናንተ ግን ከመጀመሪያው የሰማችሁት
ቃል በልባችሁ ጸንቶ ከኖረ ፤ ከወልድና ከአብ
ጋር ኅብረት ይኖራችኋል ። 25 ይህም ክርስቶስ
የሰጠን ተስፋ ፥ የዘላለም ሕይወት ነው ።

26 ስለሚያታልሉአችሁ ሰዎች ይህን ጻፍሁላ
ችሁ ፤ 27 ነገር ግን ከክርስቶስ የተቀበላችሁት
መንፈስ በውስጣችሁ ስለሚኖር ፥ ሌላ አስተማሪ
አያስፈልጋችሁም ፤ እርሱ ሁሉን ነገር ያስተም
ራችኋል ። የሚያስተምራችሁም እውነት ነው
እንጂ ሐሰት አይደለም ። ስለዚህ እርሱ በሚያስ
ተምራችሁ መሠረት በክርስቶስ ኑሩ ።

28 እንግዲህ ልጆቼ ሆይ! እርሱ በሚገለጥ
በት ጊዜ ሳንፈራ በድፍረት እንድናየውና በሚ
መጣበት ቀን እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ ፤ 29 እርሱ
ጻድቅ መሆኑን ካወቃችሁ ጽድቅን የሚያደርግ
ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ማወቅ አለባ
ችሁ ።

## ምዕራፍ 3
### የእግዚአብሔር ልጆች

1 “የእግዚአብሔር ልጆች” ተብለን እንድን
ጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን
እዩ! በእርግጥም የእግዚአብሔር ልጆች ነን ፤
ዓለም እግዚአብሔርን ስላላወቀ እኛንም አያው
ቀንም ። 2 ወዳጆቼ ሆይ! አሁን የእግዚአብሔር
ልጆች ነን ፤ ወደፊት ምን እንደምንሆንም ገና
አልታወቀም ፤ ነገር ግን ክርስቶስ በሚገለጥበት
ጊዜ እውነተኛ መልኩን ስለምናይ እርሱን እን
ደምንመስል እናውቃለን ። 3 ይህ እንደሚሆን
በክርስቶስ ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ ፥ ክርስቶስ
ንጹሕ እንደሆነ እርሱም ራሱን ንጹሕ ያደር
ጋል ።

4 ኀጢአት የሚሠራ ሁሉ የእግዚአብሔርን
ሕግ ያፈርሳል ፤ ምክንያቱም ኀጢአት ማለት
የእግዚአብሔርን ሕግ ማፍረስ ነው ። 5 ክርስቶስ
የሰዎችን ኀጢአት ለመደምሰስ እንደተገለጠና
እርሱም ኀጢአት እንደሌለበት ታውቃላችሁ ።
6 ስለዚህ በክርስቶስ የሚኖር ሰው ሁሉ ኀጢ
አት አይሠራም ። ኀጢአት የሚሠራም ሰው ክር
ስቶስን አላየውም ወይም አላወቀውም ።

2፡7 ፦ ዮሐ. 13፡34 ። 3፡1 ፦ ዮሐ. 1፡12 ። 3፡5 ፦ ዮሐ. 1፡29 ።



7 ልጆቼ ሆይ! ማንም እንዳያታልላችሁ!
ክርስቶስ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ
ሁሉ ጻድቅ ነው ። 8 ዲያብሎስ ከመጀመሪያው
አንሥቶ ኀጢአት ስለሚሠራ ፥ ኀጢአትን የሚ
ሠራ ሁሉ የዲያብሎስ ልጅ ነው ። የእግዚአብ
ሔር ልጅ የተገለጠውም የዲያብሎስን ሥራ
ለማፍረስ ነው ።

9 የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ኀጢአት አይሠ
ራም ፤ ሊሠራም አይችልም ፤ ምክንያቱም የእግ
ዚአብሔር ባሕርይ በውስጡ ስለሚኖርና ከእግ
ዚአብሔርም ስለተወለደ ነው ። 10 የእግዚአብ
ሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች ተለይተው
የሚታወቁት እነሆ በዚህ ነው ፤ ጽድቅን የማያ
ደርግና ወንድሙን የማይወድድ ሁሉ የእግዚአ
ብሔር ልጅ አይደለም ።

### እርስ በርስ ስለመፋቀር

11 ከመጀመሪያው የሰማችሁት መልእክት
“እርስ በርሳችን እንፋቀር” የሚል ነው ።
12 የሰይጣን ወገን እንደነበረውና ወንድሙን እን
ደገደለው እንደ ቃየል መሆን አይገባንም ፤
እርሱ ወንድሙን ስለምን ገደለው? የእርሱ
ሥራ ክፉ ስለነበረና የወንድሙ ሥራ ግን ትክ
ክል ስለነበረ ነው ።

13 ወንድሞቼ ሆይ! ዓለም ቢጠላችሁ አትደ
ነቁ ። 14 እኛ ወንድሞቻችንን ስለምንወድ
ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገራችንን እናውቃ
ለን ። ፍቅር የሌለው ሰው በሞት ይኖራል ።
15 ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው ፤
ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይወት እንደሌለው
ታውቃላችሁ ። 16 ፍቅር ምን እንደሆነ የምናው
ቀው ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ለእኛ አሳልፎ
ስለሰጠን ነው ፤ እኛም ሕይወታችንን ስለ ወንድ
ሞቻችን አሳልፈን መስጠት ይገባናል ። 17 ሰው
በዚህ ዓለም ሀብት እያለው ችግረኛውን አይቶ
ባይራራለት “እግዚአብሔርን እወዳለሁ” ማለት
እንዴት ይችላል? 18 ልጆቼ ሆይ! ፍቅራችን
እውነተኛና በሥራ የሚገለጥ ይሁን እንጂ ፥
በቃል ወይም በንግግር ብቻ አይሁን ።

### በእግዚአብሔር ፊት ያለን መተማመን

19 በዚህም እውነተኞች መሆናችንንና በእግ
ዚአብሔር ፊት ያለ ስጋት በመተማመን ለመቅ
ረብ መቻላችንን እናውቃለን ። 20 ኅሊናችን
በክፉ ሥራችን ቢወቅሰንም ፥ እግዚአብሔር ከኅ
ሊናችን በላይ እንደሆነና ሁሉንም ነገር እንደ
ሚያውቅ እርግጠኞች ነን ። 21 ወዳጆቼ ሆይ!
ኅሊናችን የማይወቅሰን ከሆነ ፥ በእግዚአብሔር
ፊት ሙሉ መተማመን ይኖረናል ። 22 የእግዚአ
ብሔርን ትእዛዞች የምንፈጽምና እርሱን ደስ
የሚያሰኘውንም የምናደርግ ስለሆንን ፤ የምንለ
ምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን ። 23 የእግዚአ
ብሔር ትእዛዝ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
እንድናምንና ክርስቶስ ባዘዘንም መሠረት እርስ
በርሳችን እንድንዋደድ ነው ። 24 የእግዚአብሔ
ርን ትእዛዝ የሚፈጽም ሁሉ በእግዚአብሔር
ይኖራል ፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል ።
እግዚአብሔር በእኛ መኖሩን የምናውቀው ፥
እርሱ በሰጠን መንፈስ ነው ።

## ምዕራፍ 4
### እውነተኛ መንፈስና ሐሰተኛ መንፈስ

1 ወዳጆች ሆይ! በዓለም ላይ ብዙ ሐሰተ
ኞች ነቢያት ስለተነሡ መንፈስን ሁሉ አት
መኑ ፤ ይልቅስ መንፈሶች የእግዚአብሔር መሆ
ናቸውንና አለመሆናቸውን መርምሩ ። 2 የእግዚ
አብሔርን መንፈስ ለይታችሁ የምታውቁት
እነሆ በዚህ ነው ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ
በሥጋ መገለጡን የሚመሰክር መንፈስ ሁሉ የእ
ግዚአብሔር መንፈስ ነው ፤ 3 ኢየሱስ ክርስቶስ
ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡን የማይመሰክር መን
ፈስ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም ፤
ይህም መንፈስ ይመጣል ሲባል የሰማችሁት የክ
ርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው ፤ እርሱ አሁን
እንኳን በዓለም ላይ አለ ።

4 ልጆቼ ሆይ! እናንተ የእግዚአብሔር
ናችሁ ፤ በእናንተ ያለው መንፈስ በዓለም ካለው
መንፈስ ይበልጣል ። ስለዚህ ሐሰተኞች ነቢያ
ትን አሸንፋችኋል ። 5 እነርሱ የዓለም ናቸው ፤
የሚናገሩትም የዓለምን ነገር ነው ። ዓለምም
እነርሱን ይሰማቸዋል ። 6 እኛ የእግዚአብሔር
ነን ፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሁሉ ይሰማ
ናል ፤ የእግዚአብሔር ያልሆነ ግን አይሰማ
ንም ። እውነተኛን መንፈስና ሐሰተኛን መንፈስ
ለይተን የምናውቀው በዚህ ነው ።

### እግዚአብሔር ፍቅር ነው

7 ወዳጆቼ ሆይ! ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ
ሆነ እርስ በርሳችን እንፋቀር ፤ እግዚአብሔር
ንና ሰውን የሚያፈቅር ሁሉ የእግዚአብሔር
ልጅ ነው ። እግዚአብሔርንም ያውቃል ። 8 እግ
ዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ፥ እግዚአብሔርንና
ሰውን የማያፈቅር ሁሉ እግዚአብሔርን አያው
ቅም ። 9 በልጁ አማካይነት ሕይወት እንድናገኝ
እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮ
ታል ፤ በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር ምን
ያህል እንደሆነ ለእኛ ተገልጦአል ። 10 ፍቅር
ማለት እንዲህ ነው ፥ እኛ እግዚአብሔርን ስለወ
ደድነው ሳይሆን ፥ እርሱ ስለወደደንና ኃጢአታ
ችንን እንዲደመስስ ልጁን ስለላከልን ነው ።
11 ወዳጆቼ ሆይ! እግዚአብሔር ይህን ያህል
ካፈቀረን ፥ እኛም እርስ በርሳችን መፋቀር

3፡11 ፦ ዮሐ. 13፡34 ። 3፡12 ፦ ዘፍ. 4፡8 ። 3፡14 ፦ ዮሐ. 5፡24 ። 3፡23 ፦ ዮሐ. 13፡34 ፤ 15፡12 ፡17 ።

ይገባናል ። [12]እግዚአብሔርን ያየው ማንም
ሰው የለም ። እኛ እርስ በርሳችን ብንፋቀር እግ
ዚአብሔር በእኛ ይኖራል ፤ ፍቅሩም በእኛ
ፍጹም ይሆናል ።
[13]እግዚአብሔር መንፈሱን ስለ ሰጠን ፥ በእ
ርሱ እንደምንኖርና እርሱም በእኛ እንደሚኖር
እናውቃለን ። [14]አብ የዓለም አዳኝ አድርጎ ወል
ድን እንደላከው አይተናል ፤ እንመሰክራለንም ።
[15]ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በሚመ
ሰክር ሰው ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ይኖራል ፥
እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል ። [16]ስለዚህ
እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እናውቃ
ለን ፤ እናምናለንም ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው ፤
በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል ፤ እግ
ዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል ። [17]በዚህ ዓለም
እኛ የምንኖረው ልክ ክርስቶስ እንደሚኖረው
እንደመሆኑ መጠን ፥ ፍቅራችን ፍጹም ቢሆን ፥
በፍርድ ቀን ያለፍርሃት በፊቱ ለመቅረብ ሙሉ
ሙተማመን ይኖረናል ። [18]ፍጹም ፍቅር ፍርሃ
ትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት
የለም ፤ ፍርሃት ከቅጣት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ፥
የሚፈራ ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም ።
[19]እግዚአብሔር አስቀድሞ ስላፈቀረን
እኛም እናፈቅራለን ። [20]“እግዚአብሔርን እወ
ድዳለሁ” እያለ ወንድሙን የሚጠላ ሐሰተኛ
ነው ፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድድ ከሆነ ፥
ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወድድ አይችልም ።
[21]ስለዚህ ክርስቶስ የሰጠን ትእዛዝ “እግዚአብ
ሔርን የሚወድድ ፥ ወንድሙንም ይውደድ”
የሚል ነው ።

## ምዕራፍ 5

### ዓለምን ስለማሸነፍ

[1]ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን የሚያምን ሁሉ
የእግዚአብሔር ልጅ ነው ፤ አባቱን የሚወድድ
ሁሉ ልጁንም ይወድዳል ። [2]የእግዚአብሔርን
ልጆች የምንወድድ መሆናችንን የምናውቀው ፥
እግዚአብሔርን ስንወድድና ትእዛዞቹንም ስንፈ
ጽም ነው ። [3]እግዚአብሔርንም መውደድ
ማለት ትእዛዞቹንም መፈጸም ነው ፤ ትእዛዞቹም
አስቸጋሪዎች አይደሉም ። [4]ምክንያቱም የእግ
ዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል ፤
ዓለምን የምናሸንፈውም በእምነታችን ነው ።
[5]ዓለምን የሚያሸንፈው ፥ ኢየሱስ የእግዚአብ
ሔር ልጅ መሆኑን የሚያምን ብቻ ነው ።

### ስለ ክርስቶስ የተሰጠ ምስክርነት

[6]ጥምቀቱን በሚያመለክት ውሃና ሞቱን
በሚያመለክት ደም የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ
ነው ። እርሱ የመጣው በውሃ ብቻ ሳይሆን ፥
በውሃና በደም ነው ። ይህ ነገር እውነት መሆኑን
መንፈስ ቅዱስ ይመሰክራል ፤ ምክንያቱም መን
ፈስ ቅዱስ እውነት ነው ። [7]ሦስት ምስክሮች
አሉ ፤ [8]እነርሱም መንፈስ ፥ ውሃ ፥ ደም
ናቸው ። እነዚህም ሦስቱ በምስክርነት ይስማ
ማሉ ። [9]ሰዎች የሚሰጡትን ምስክርነት እንቀበ
ላለን ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ምስክርነት
ከሁሉ ይበልጣል ። እግዚአብሔር ስለ ልጁ የሰ
ጠውም ምስክርነት ይህ ነው ። [10]በእግዚአብ
ሔር ልጅ የሚያምን ይህ ምስክርነት በልቡ
አለው ። እግዚአብሔርን የማያምን ግን እግዚአብ
ሔር ስለ ልጁ የሰጠውን ምስክርነት ባለማመኑ
ሐሰተኛ አድርጎታል ። [11]ምስክርነቱም ፥ እግዚ
አብሔር የዘላለም ሕይወት እንደሰጠንና ይህም
ሕይወት በልጁ እንዳለ የሚመሰክር ነው ።
[12]የእግዚአብሔር ልጅ ያለው ሕይወት አለው ።
የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ግን ሕይወት የለ
ውም ።

### የዘላለም ሕይወት

[13]እናንተ በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታ
ምኑ ሁሉ ፥ የዘላለም ሕይወት ያላችሁ መሆኑን
እንድታውቁ ይህን ሁሉ ጽፌላችኋለሁ ። [14]ማን
ኛውንም ነገር እንደ እርሱ ፈቃድ ብንለምን እን
ደሚሰማን እርግጠኞች ነን ፤ ስለዚህ በእግዚአብ
ሔር ፊት ድፍረት አለን ። [15]የምንለምነውን
ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን ፥ ከእርሱ የምንለምነ
ውን ሁሉ አሁኑኑ እንደምንቀበል እናውቃለን ።
[16]ማንም ሰው ወንድሙ ለሞት የማያደርስ
ኃጢአት ሲሠራ ቢያየው ይጸልይለት ፤ የሰውየው
ኃጢአት ለሞት የማያደርስ ከሆነ እግዚአብሔር
ሕይወትን ይሰጠዋል ። ነገር ግን ለሞት የሚያደ
ርስ ኃጢአት አለ ። ለእንዲህ ዐይነቱ ኃጢአት
ይጸልይ አልልም ። [17]ክፉ ሥራ ሁሉ ኃጢአት
ነው ። ይሁን እንጂ ለሞት የማያደርስ ኃጢአት
አለ ።
[18]የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ኃጢአት
የመሥራት ልማድ እንደማይኖረው እናውቃ
ለን ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ
ክርስቶስ ይጠብቀዋል ፤ ሰይጣንም አይነካውም ።
[19]እኛ የእግዚአብሔር መሆናችንን እናውቃ
ለን ። ዓለም ግን በሞላው የሰይጣን ተገዥ ሆኖ
አለ ።
[20]የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣና እውነት
የሆነውን እርሱን እንድናውቅ አስተዋይ ልቡና
እንደሰጠን እናውቃለን ፤ እኛም በዚህ እውነት
በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ እንኖራለን ። እርሱ
እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው ።
[21]ልጆቼ ሆይ! ሐሰተኞች አማልክትን ከማ
ምለክ ራሳችሁን ጠብቁ ።

4፡12 ፦ ዮሐ. 1፡18 ። 5፡3 ፦ ዮሐ. 14፡15 ። 5፡11 ፦ ዮሐ. 3፡36 ።

ሁለተኛው

# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት

### መግቢያ

ሁለተኛው የዮሐንስ መልእክት የተጻፈው “በሽማግሌው ሐዋርያ በዮሐንስ” ሲሆን ፥ የተጻፈውም “ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆችዋ” ነው ። ምናልባትም ለአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና ለአባሎችዋ ሳይሆን አይቀርም ፤ ይህ አጭር መልእክት የተጻፈው እርስ በርስ እንዲዋደዱ ለማሳሰብና ከሐሰተኞች መምህራንና ከትምህርታቸውም ለማስጠንቀቅ ነው ።

[1]ለተመረጠችው እመቤትና[1*] ለልጆችዋ ፤
ከእኔ ከሽማግሌው የተላከ መልእክት ፤ እኔ
በእውነት እወዳችኋለሁ ፤ እኔ ብቻ ሳልሆን
እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ይወዱአችኋል ፤
[2]ይህም እውነት በመካከላችን ያለና ወደ
ፊትም ለዘላለም የሚኖር ነው ።
[3]የእግዚአብሔር አብና የልጁ የኢየሱስ ክር
ስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም በእውነትና በፍ
ቅር ከእኛ ጋር ይሁን ።

### ስለ እውነትና ስለ ፍቅር

[4]ከልጆችሽ አንዳንዶቹ ፥ አብ ባዘዘን መሠ
ረት በእምነት ጸንተው በማግኘቴ በጣም ደስ
ብሎኛል ። [5]እመቤት ሆይ! አሁንም ዐደራ
ሽን! ይህ የምጽፍልሽ አዲስ ትእዛዝ አይምሰ
ልሽ ፤ አሁን የምጽፍልሽ “እርስ በርሳችን እን
ዋደድ” የሚለውን ከመጀመሪያ አንሥቶ በእኛ
ዘንድ የነበረውን ትእዛዝ ነው ። [6]እውነተኛ
ፍቅር ማለት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም
ነው ። ይህም ትእዛዝ በመጀመሪያ እንደሰማች
ሁት “በፍቅር ኑሩ” የሚል ነው ።
[7]ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሥጋ መገለ
ጡን የማያምኑ ብዙ አሳሳቾዎች በዓለም ተነሥ
ተዋል ። [8]እናንተ ግን ሙሉ ደመወዛችሁን
ለመቀበል ትጉ ፤ የሠራችሁትም እንዳይጠፋባ
ችሁ ተጠንቀቁ ።
[9]በክርስቶስ ትምህርት ጸንቶ የማይኖርና ከእ
ርሱም ርቆ የሚሄድ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
የለም ፤ በክርስቶስ ትምህርት ጸንቶ የሚኖር
ሰው ግን አብና ወልድ ከእርሱ ጋር አሉ ።
[10]ይህን ትምህርት ሳይዝ ማንም ወደ እናንተ
ቢመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ፤ ሰላምታም
እንኳ አትስጡት ። [11]ምክንያቱም ሰላምታ የሚ
ሰጠው ሰው የክፉ ሥራው ተካፋይ ይሆናል ።

### የመጨረሻ ሰላምታ

[12]ልጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበ
ረኝ ፤ ነገር ግን ሁሉንም በደብዳቤ ልገልጸው
አልፈልግም ፤ ይልቅስ ደስታችን ፍጹም እንዲ
ሆን ወደ እናንተ መጥቼ ዐይን ለዐይን ተያይ
ተን ላነጋግራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ።
[13]የተመረጠችው የእኅትሽ ልጆች ሰላምታ
ያቀርቡልሻል ።

[1*] 1፡1 እመቤትና ልጆችዋ ፦ ቤተ ክርስቲያንንና አባሎችዋን ያመለክታል (በቍ. 4 እና 5 ላይም ይገኛል) ።
5 ፦ ዮሐ. 13፡34 ፤ 15፡12፡17 ።

### ሦስተኛው
# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት

## መግቢያ

ሦስተኛው የዮሐንስ መልእክት የተጻፈው “በሽማግሌው ሐዋርያ በዮሐንስ” ሲሆን ፥ የተጻፈ ውም ጋይዮስ ለተባለ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር ፤ ጸሐፊው በአንድ በኩል ሌሎችን ክርስቲያ ኖች በመርዳቱ ጋይዮስን ያመሰግነዋል ፤ በሌላ በኩል ዲዮጥራጢስ ከተባለ ተንኰለኛ ሰው እን ዲጠነቀቅ ያሳስበዋል ።

---

1 በእውነት ለማፈቅረው ፥ ለተወደደው ጋይ
ዮስ ፤
ከእኔ ከሽማግሌው የተላከ መልእክት ።
2 ወዳጄ ሆይ! በነፍስህ ደኅና እንደሆንህ
ዐውቃለሁ ፤ እንዲሁም ኑሮህ ሁሉ እንዲሳካል
ህና ጤንነትም እንዲኖርህ እጸልይልሃለሁ ።
3 አንዳንድ ወንድሞች መጥተው ለእውነት
ታማኝ መሆንህንና እውነትን ይዘህ መኖርህን
ሲመሰክሩ በመስማቴ በጣም ደስ አለኝ ። 4 ምክ
ንያቱም ልጆቼ እውነትን ይዘው መኖራቸውን
ከመስማት ይልቅ ፥ ሌላ ይበልጥ የሚያስደስተኝ
ነገር የለም ።

### ጋይዮስ ተመሰከረለት

5 ወዳጄ ሆይ! ምንም እንኳ እንግዶች
ቢሆኑ ለወንድሞች በታማኝነት ትሠራለህ ።
6 እነርሱም ስለ አደረግህላቸው የፍቅር ሥራ
በአማኞች ማኅበር ፊት መስክረዋል ፤ አሁንም
እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ በጕዞአ
ቸው ብትረዳቸው መልካም ነው ። 7 እነርሱ
ክርስቶስን ለማገልገል ሲወጡ ከአረማውያን
ምንም ዕርዳታ አላገኙም ። 8 የእውነት ሥራ
ተካፋዮች እንድንሆን ፥ እንደእነዚህ ያሉትን
ሰዎች መርዳት አለብን ።

### ዲዮትሬፌስ ተወቀሰ ፥ ድሜጥሮስ ተመሰገነ

9 ከዚህ በፊት ለቤተ ክርስቲያን ደብዳቤ
ጽፌአለሁ ፤ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪ
መሆን የሚፈልገው ዲዮትሬፌስ አሳቤን አልተ
ቀበለም ። 10 ስለዚህ ወደ እናንተ ስመጣ እርሱ
እየሰደበንና እያዋረደን ያደረገውን ክፉ ሥራ
ሁሉ ፥ ለሁሉም እናገራለሁ ፤ እርሱ የሚያደር
ገው ይህን ብቻ አይደለም ። እርሱ ራሱ ወንድ
ሞችን አይቀበልም ። ሌሎችም እንዳይቀበሉአ
ቸው ይከለክላል ። ከቤተ ክርስቲያንም ያስወጣ
ቸዋል ።
11 ወዳጄ ሆይ! ደጉን ምሰል እንጂ ክፉውን
አትምሰል ። ደግ ሥራ የሚሠራ ሁሉ የእግዚአ
ብሔር ነው ። ክፉ ሥራ የሚሠራ ግን እግዚአብ
ሔርን አላየውም ።
12 ለድሜጥሮስ ሰው ሁሉ በመልካም ይመሰ
ክርለታል ። እውነት ራሰዋም ትመሰክርለታ
ለች ። እኛም እንመሰክርለታለን ፤ የእኛም ምስ
ክርነት እውነት መሆኑን ታውቃለህ ።

### የመጨረሻ ሰላምታ

13 ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበ
ረኝ ፤ ነገር ግን በደብዳቤ ልገልጽልህ አልፈል
ግም ። 14 በቅርቡ ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ ፤
በዚያን ጊዜ ዐይን ለዐይን ተያይተን እንነጋገራ
ለን ።
15 ሰላም ለአንተ ይሁን ።
ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል ። አንተም
ለወዳጆቻችን አንድ በአንድ ሰላምታ አቅርብ
ልን ።

---

1 ፦ ሐ.ሥ. 19፥29 ፤ ሮም 16፥23 ፤ 1ቆሮ. 1፥14 ።



# የይሁዳ መልእክት

## መግቢያ

የይሁዳ መልእክት የተጻፈው ፥ አማኞች ሳይሆኑ አማኞች መስለው የሐሰት ትምህርት ከሚ ያሰራጩ ሰዎች ክርስቲያኖችን ለማስጠንቀቅ ነው ፤ በይዘቱ ሁለተኛ ጴጥሮስን በሚመስለው በዚህ አጭር መልእክት ጸሐፊው “በማያዳግም ሁኔታ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠው እምነት በብርቱ እንዲጋደሉ” አንባቢዎቹን በጥብቅ ያሳስባል ።

---

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕቆብ
ወንድም ከሆነው ከይሁዳ ፥
ለተጠራችሁት ፤ በእግዚአብሔር አብ ለተወ
ደዳችሁት ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቃችሁት
ሁሉ ፤
2 ምሕረትና ሰላም ፍቅርም ይብዛላችሁ ።

### ሐሰተኞች መምህራን

3 ወዳጆች ሆይ! ስለ ጋራ ደኅንነታችን ልጽ
ፍላችሁ በብርቱ ፈልጌ ነበር ፤ አሁንም በማያዳ
ግም ሁኔታ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠው
እምነት በብርቱ እንድትጋደሉ ለመምከር ልጽ
ፍላችሁ ግድ ሆነብኝ ። 4 የሚፈረድባቸው
መሆኑ ከብዙ ጊዜ በፊት የተጻፈባቸው አንዳ
ንድ ሰዎች ወደ እናንተ ሾልከው ገብተዋል ፤
እነርሱ የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኛነት የሚለ
ውጡ ኃጢአተኞች ናቸው ፤ እርሱ ብቻ ገዥያ
ችንና ጌታችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስንም
ይክዳሉ ።
5 ምንም እንኳ ይህን ሁሉ አስቀድማችሁ
የምታውቁት ቢሆንም ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን
ከግብጽ አገር አውጥቶ እንዳዳነና ያላመኑትንም
በኋላ እንዳጠፋቸው ላስታውሳችሁ እወዳለሁ ።
6 እንዲሁም ማዕርጋቸውን ባለመጠበቅ ስፍራቸ
ውን የተዉትን መላእክት አስታውሱ ፤ እነርሱን
እግዚአብሔር እስከ ታላቁ የፍርድ ቀን ድረስ
በዘላለም እስራት ፥ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ
ጠብቆ አቆይቷቸዋል ። 7 በዚሁ ዐይነት ሰዶምና
ገሞራ በዙሪያቸው ያሉ ከተሞችም የዝሙት
ኃጢአት ፈጸሙ ፤ የተፈጥሮ ሥርዓትንም በመለ
ወጥ በግብረ ሥጋ ተገናኙ ። ስለዚህ እነርሱ በዘ
ላለም እሳት ለሚቀጡት ምሳሌ ሆነዋል ።
8 እንዲሁም እነዚሀ ሰዎች በሕልም እየተ
መሩ ሥጋቸውን ያረክሳሉ ፤ የእግዚአብሔርንም
ሥልጣን ይንቃሉ ፤ በሰማይ ክብር ያላቸውንም
ይነቅፋሉ ። 9 የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ
ስለ ሙሴ አስከሬን ከዲያብሎስ ጋር በብርቱ በተ
ከራከረ ጊዜ “እግዚአብሔር ይገሥጽህ!” አለው
እንጂ የስድብ ቃል በመናገር ሊፈርድበት አልደ
ፈረም ። 10 እነዚህ ሰዎች ግን ለማስተዋል ያቃታ
ቸውን ነገር ሁሉ ይሳደባሉ ፤ አእምሮ እንደሌላ
ቸው እንስሶች በተፈጥሮ ስሜት የሚያውቁት
ነገር ቢኖር እንኳ በእርሱ ይጠፋሉ ። 11 በቃየል
መንገድ ስለሄዱ ፥ ለገንዘብ ብለው በበለዓም ስሕ
ተት ስለ ወደቁ ፥ ቆራሕ እንደተቃወመ በመቃ
ወማቸው ስለ ጠፉ ወዮላቸው! 12 እነዚህ ሰዎች
ያለ ሐፍረት እየተዳሩ በፍቅር ግብዣችሁ ላይ
ሲገኙ እንቅፋት ይሆኑባችኋል ፤ እነርሱ የሚያስ
ቡት ስለ ራሳቸው ብቻ ነው ፤ በነፋስ እንደሚ
ገፋ ፥ ዝናብ እንደሌለው ደመና ናቸው ። በፍሬ
ወራት እንኳ ፍሬ እንደማይገኝበት ፥ ከሥሩ እን
ደተነቀለና ሁለት ጊዜ እንደሞተ ዛፍ ናቸው ።
13 የአሳፋሪ ድርጊታቸውን ዐረፋ የሚደፍቁ ፥
እንደ ተቈጣ የባሕር ማዕበል ናቸው ፤ ድቅድቅ
ጨለማ ለዘላለም የሚጠብቃቸው ፥ እንደሚንከራ
ተቱ ኮከቦች ናቸው ።
14 ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ ትውልድ የሆነው
ሔኖክ ስለነዚህ ሰዎች እንዲህ ሲል ትንቢት
ተናግሮአል ፥ “እነሆ ጌታ ከብዙ ሺ ቅዱሳን
ጋር ይመጣል ። 15 የሚመጣውም በሰው ሁሉ
ላይ ሊፈርድ ዐመፀኞችንና ኃጢአተኞችን ሁሉ
በዐመፃ ሥራቸው ሁሉና በእግዚአብሔር ላይ
በተናገሩት የስድብ ቃል ሁሉ ሊወቅስ ነው ።”
16 እነዚህ ሰዎች ሁልጊዜ የሚያጕረመር
ሙና በምንም ነገር የማይደሰቱ ናቸው ፤ የራሳ
ቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ናቸው ፤ አፋ
ቸው በትዕቢት ቃል የተሞላ ነው ፤ የራሳቸውን
ጥቅም በመፈለግ ሰውን ይለማመጣሉ ።

---

1 ፦ ማቴ. 13፥55 ፤ ማር. 6፥3 ። 5 ፦ ዘጸ. 12፥51 ፤ ዘኍ. 14፥29-30 ። 7 ፦ ዘፍ. 19፥1-24 ። 9 ፦ ዳን. 10፥13 ፥21 ፤ 12፥1 ፤ ራእ. 12፥7 ፤ ዘዳ. 34፥6 ፤ ዘካ. 3፥2 ። 11 ፦ ዘፍ. 4፥3-8 ፤ ዘኍ. 22፥1-35 ፤ 16፥1-35 ። 14 ፦ ዘፍ. 5፥18 ፥21-24 ።